


Info

t.me/BookAlem

Invite Link

@BOOKALEM

በድጋሚ
የታተመ

# ወበቡ

## ፩



ከዲሳጠከ

(ጎይለጊዮርጊስ ማሞ)

@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ጥበብ

## ፩



*«እኔም ብርሃን ከጨለማ*
*እንደሚበልጥ እንዲሁ*
*ጥበብ ከስንፍና እንዲበልጥ አየሁ»*
*መክ. 2:13*

# ሶቅራጥስ

(ኃ/ጊ.ማ)

@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved
1997 E.C.

አሣታሚ:-
ሻላ ፕሮሞሽን ሰርቪስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር
☎ 634736 ✉ 110377
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

## መታሰቢያነቱ

ለሲስተር አሰገደች ጥጋቡ
ለእዚብ ፋንታሁን
በተሰይ ለሳሌም ኃይለጊዮርጊስ
ይሁንልኝ::

## መፅሐፉ ተበረከተ

ፅሁፎቼን መፅሐፍ ለማድረግ የነበረኝን ሕልም ለፈታልኝ
ውድ ወንድሜ አባይ ወርቅዬ፣ አስቀድማ ሕልሙን
በውስጤ ለጫረችው ውድ እህቴ ስንዱ አበበ፣
በተፈታው ሕልም ሳይ የበኩሉን ሳበረከተው
በዕውቀቱ ስዩም፣ እንዲሁም የተፈታውን ሕልም
ሳሰማመረችው አሰገደች ጥላሁን ምስጋና ያንስባችኋል::

@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# መግቢያ

ይኽ መፅሐፍ እንደ«ሰው» ማሰብ ለሚፈልጉ ሁሉ ተፅፏልና መግቢያም ሆነ አጥር አልተበጀለትም፡፡

ጂላጠስ

@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# ማሰብ ባትችል፤ ማሰብ እንደምትችል እወቅ

*ሰውን እንዲያስብ ልታደርገው ባትችልም፤ ማሰብ እንደሚችል ልትነግረው ግን ትችላለህ የሚለው የጥንታውያን ፈላስፎች አባባል* የዚህ ፀሐፊ እምነትና መሠረት ነው:: እነሆም የፍልስፍናውን ዓለም ጉዞ አሃዱ ብለን ለመጀመር ማሰብ እንጀምራለን:: ማሰብ ለመጀመር ስንነሣ ደግሞ «ማሰብ አስጀምሮ ያላስጨረሰንን » ሰው ሕይወት ማየት የግድ ይሆናል::

ስለ መልኩ አስቀያሚነት በዘመኑ የነበሩ ሰዎች እንደፃፉት ከሆነ እሱን አይቶ የማይስቅ አልነበረም፤ ትልቅ መላጣ ጭንቅላት፣ በላዩ ላይ ትንሽ ፊት፣ ረኸርምና ቅጥ ያጣ ፂም... ወዘተ የእሱ «ውበት» መገላጫዎች ነበሩ:: የጓደኞቹ የቀልድ ምንጭ የእሱ ፊት ቢሆንም እሱም ስለራሱ ፊት ተጨማሪ ቀልድ እየፈጠረ አብሮ ይስቅ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን::

አባቱ ድንጋይ ጠራቢ፣ እናቱ ደግሞ የልምድ አዋላጅ ነበሩ:: ይኸ ሰው ከድህነቱም በላይ ሥራ ፈት ነበር:: የሚስቱንና የሦስት ልጆቹን ሕይወት ለማኖር ይበቃል የሚለውን ያህል ከሰራ በኋላ ቀሪ ጊዜውን የሚያሳልፈው «በማውራት» ነበር:: ሁለተኛ ሚስቱ የነበረችው የዛንታፔ አስቸጋሪ ባህርይ ሰውየው አብዛኛውን ጊዜ ከቤቱ ርቆ እንዲውልና እንዲያመሽም የራሱን ድርሻ አበርክቷል:: ሰውየው በሚስቱ ላይ የነበረው



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ትዕግስት የሚገርማቸው ጓደኞቹ «ምነው ትዕግስትህ በዛ?» በማለት ሲጠይቁት «ትዕግስት ጥሩ ነው! እሳትን መታገስ የቻለ በብርድ ውስጥ መኖር ይችላል» ይላቸው ነበር::

ከእንቅልፉ በማለዳ ተነስቶ ቁርሱን በፍጥነት ይበላና ወጥቶ ይሄዳል... የሚሄደው በየአደባባዩ ከሚሰበሰቡት ሰዎች ጋር ለማውራት አሊያም ከመሰሎቹ ጋር ለመከራከር ነበር:: የሰውዬው ክርክር አስቀድሞ ሌሎቹ ጠቢባን ስላላነሱት ብሎም ፈፅሞ ስላላሰቡት ነገር ነበር::... ስለሰው::

አንድ ወቅት የአቴና ጠባቂና ገዢ ከፍተኛ «ሹመት» ሰጠ ... ይኸ ሹመት የአቴናን ሰዎች በሙሉ ያስገረመና ያስደነገጠም ነበር:: «ከአቴና ሁሉ ካሉ ጠቢብ» የሚል ሹመት የተሰጠው ሰው በዚያች ከተማ የሚታወቀው በሥራ ፈትነቱና በክርክር ወዳድነቱ ነበር:: «በሹመቱ» የተገረመው የአቴና ሕዝብ ገዢው እንዴት ይህን ከፍተኛ ሹመት ሊሰጠው እንደቻለ ሲጠይቁት... «እኔን ከአቴና ሰዎች ሁሉ ጠቢብ የሚል ሹመት ያሰጠኝ ጠቢብነቴ ሳይሆን የገዢውን አላዋቂነት ያወቅኩ ብቸኛው ሰው በመሆኔ ነው» በማለት መልሷል:: ይህ የአቴና ብቻ ሳይሆን የምድራችን ጠቢብ ሰው ሶቅራጥስ ነው::

ዕውቀትን ሰባኪ የነበረው ጠቢቡ ሶቅራጥስ የናዝሬቱ እየሱስ ከአራት መቶ ዓመት በኋላ መጥቶ በየመንደሩና በየአደባባዩ እየዞረ ፍቅርን እንደሰበከ ሁሉ እሱም በየዞረበት ስለሎጂክ ሰበከ:: ሶቅራጥስ በሚያስተምርበት አደባባይ ተገኝቶ የሰማ ማሰብ ባይችል ማሰብ እንደሚችል አውቆ ይሄድ ነበር ይላሉ የታሪክ ፀሐፊዎች::

አንድ ወቅት ሶቅራጥስ በአቴና ከተማ ሲዘዋወር በአንዱ አደባባይ ጠቢብ ሰው ቆሞ ስለ ፅናት (courage) ሲያስተምር ቁጥሩም የበዛ ሕዝብ ሲሰማው አስተዋለ:: ከሕዝቡም ጋር ተቀላቅሎ የጠቢቡን ሰው ንግግር ማዳመጥ ጀመረ:: ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮህ ጠቢቡን በጥያቄ አቋረጠው::

«ንግግርህን በማቋረጤ ይቅርታ ይደረግልኝና ፅናት ስትል ምን



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ማለት እንደሆነ ብትነግረኝ» አለው::

«ዕናትማ ጠላት እየቀረበህ ቢመጣም አንተ ግን ከቦታህ ላትነቃነቅ መጠበቅ ነው...» በማለት ጠቢቡ መለሰ::

«ነገር ግን እቅድህ ከሽፎ መሸሽ ቢኖርብህስ?» አለ ሶቅራጥስ::

«በእርግጥ በዚያን ጊዜ ዕናት ሌላ ይሆናል:: ቦታህን ይዘህ አትቆይምና» ጠቢቡ መለሰ::

«ስለዚህ ዕናት ከቦታህ አለመነቃነቅ ወይንም ከቦታህ መሸሽ ማለት ካልሆነ ታዲያ ዕናት ምንድን ነው?» ሶቅራጥስ ጠየቀ::

ያ ጠቢብ ሰው በሕዝቡ ፊት እግሩ መንቀጥቀጥ ጀመረ... «ሶቅራጥስ ሆይ ፈተንከኝ፤ አሁን ሳስበው በትክክል ዕናትን የማውቀው አልመሰለኝም» አለ::

«እኔም አላውቀውም» አለ ሶቅራጥስ:: «ነገር ግን ዕናት አዕምሮህን ከመጠቀም የተለየ ነገር አይመስለኝም፤ የተለየ ቢሆን ደግሞ ይደንቀኛል:: ይህም ማለት በማንኛውም አደጋ ውስጥ ብትሆን ትክክለኛውን ነገር ብቻ ማድረግ ከቻልክ ያ ዕናት ነው» በማለት በንግግሩ ላይ አከለበት::

«እንዲያውም የዕናት ትክክለኛ ትርጉሙ እሱ ነው» በማለት በአደባባዩ ከተሰበሰቡት አንዱ ጮኸ:: ሶቅራጥስ ወደዚያ ሰው ዞሮ ተራመደና እንዲህ አለ...

«እንግዲያውስ ዕናት *ማሰብ እንደሚገባህ ማሰብ ነው* በሚለው ትርጉም ለጊዜውም ቢሆን ብንስማማስ... የፅናት ተቃራኒው ደግሞ አዕምሮን በስሜት እያስገደዱ መንዳት ነው ብንልስ?» በማለት ጠየቀ::

ወደ ሶቅራጥስ ፊቱንም ልቡንም አዞሮ ይሰማ የነበረው ሕዝብ መስማማቱን ገለፀ:: ሶቅራጥስ ጠቢቡም ተስማምቶ እንደሆነ ለማወቅ ቆሞበት ወደነበረው ከፍታ ፊቱን አዞረ... ጠቢቡ ግን አልነበረም::

ከሶቅራጥስ በፊት የነበረው የፍልስፍና ዓለም አትኩሮትና እምነት በተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ነበር:: በቴለስ መሪነት በጥንታዊቷ የግሪክ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ከተማ ማልተስ ላይ ያቆጠቆጠው ፍልስፍና «የማንኛውም እውነት ምንጩ ውኃ ነው» ብሎ ተነሣ:: ሌላው ነገር ሁሉ ከውኃ መጣ ነው ነገሩ:: በመቀጠል የቴለስ ተማሪ የነበረው አኔክስማንደር ደግሞ «የእውነት ሁሉ ምንጭ አፔሮን ነው» አለን:: አፔሮን ምንድነው ሲባል «እኔም አላውቀው» ሆነ መልስ:: የእሱ ተማሪ አኔክስማነስ ደግሞ «እውነት የመጣው ከአየር ነው፤ አየር ባይኖር አሁን ለዓይናችን እውነት ሆነው የምናያቸው (ዛፍ፣ ድንጋይ፣ ሰው...) ባልኖሩ ነበር» አለ:: እንዲህ እያለ ብዙዎችም እያመኑበት የሄራክሊተስ ዘመን ላይ ደረሱና እሱም «የእውነታ ሁሉ ምንጭ እሣት ነው» አለን:: እነዚህና መሰል እምነቶች ለዘመናት ሲታመኑባቸው ኖሩና ሶቅራጥስ ላይ ደረሰ:: እንግዲህ ለዘመናት የሰው ልጅ ስለ እውነታ የነበረውን እሳቤና እምነት የገለበጠ ይህ ሰው ነው:: ለሶቅራጥስ እውነታ «የሰው ልጅ አዕምሮ» ሆነ::

«የእኔ ጉዳይ ሰው እንጂ ድንጋይ፣ አየር፣ አፈር፣ ዛፍ፣ ወይም ውኃ አይደለም» የሚለው ሶቅራጥስ እሱን የሚያስጨንቁ ጥያቄዎች «ሰው ምንድነው?» «መልካምና መጥፎ ሰውስ ማነው?» «ሰው በራሱስ ምን መሆን ይችላል? ... ወዘተ» የሚሉት ነበሩ::

«የመልካምነት መሠረቱ ዕውቀት፣ የክፋት መሠረቱ ደግሞ አለማወቅ ናቸው» የሚለን ሶቅራጥስ «የእውቀት መጀመሪያ አለማወቅን ማወቅ ነው... ማወቅ ደግሞ ከማሰብ ይጀምራል» ብሏል:: ለዚህም ነው የግሪክ ጠቢባንንና አዋቂዎችን በጥያቄው ሲፈታተናቸው መልስም እያሳጣ ሲያሳፍራቸው የኖረው:: ሶቅራጥስ ሲናገር «ከብዙ ጠቢባን ጋር ስነጋገር የሚገርመኝና የሚያሳዝነኝ እናውቃለን በሚል ሃሣብ የመከፈሳቸው ሳይሆን አላዋቂነታቸውን አለማወቃቸው ነው... እኔ አለማወቄን የማውቅ ሰው በመሆኔ በእነሱ መካከል እንደ ታላቅ ጠቢብ ተከበርኩ» ብሏል:: እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ዕለት ዕለት በጥያቄው ሲፈታተናቸው ይውል ነበር:: ስለዚህ ሰው ስብህናና እውቀት ተቀንጭቦ ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት ታትመው ከወጡ *ሪደርስ ዳይጀስት* መጽሔቶች ላይ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

የቃረምኩትን ልበትን::

አንድ ቀን አንድ መምህር ወደ እሱ ሊተዋወቀው መጣ:: ሶትራጥስም ሰውየው መምህር መሆኑን ሲረዳ:- «ለመሆኑ ለተማሪዎችህ አንዳች እውቀትህን ከማካፈልህ በፊት የራስህን አላዋቂነት ተገንዝበሃል?» በማለት ጠየቀው:: ከፍ ያለ ከበሬታ ለሶቅራጥስ የነበረው መምህርም:- «በእርግጥ ምንም እንደማላውቅ አውቃለሁ» በማለት መለሰ::

«እንግዲያስ ለተማሪዎችህ ሂድና ይህንኑ ንገር» አለው::

«አለማወቄን ስነግራቸው ጥለውኝ ቢሄዱስ?» በማለት ጠየቀው::

«ያን ጊዜ ነፃ ስለምትሆን እዚህ መጥተህ ትማራለህ» በማለት መለሰለት::

በሌላ ጊዜ ደግሞ በዘመኑ ከሚከበሩትና ከሚፈሩት የግሪክ ባለስልጣናት ከአንዱ ጋር በመንገድ ተገናኝተው «ባለስልጣን ሆኜ ሳለ ባለስልጣን የመሆን ትርጉሙ ግን እስከአሁን አልገባኝም» በማለት ሶቅራጥስን ለጠየቀው ጥያቄ እንዲህ በማለት መለሰለት:- «ባለስልጣን ማለት የራሱን ፍላጎት መቆጣጠር የማይችል ነገር ግን የሕዝቡን ፍላጎት መቆጣጠር የሚፈልግ ሰው ማለት ነው»::

ለሶቅራጥስ «የዚህ ዓለም ችግር ሁሉ ምንጭ አላዋቂነት (ignorance) ነው:: ስለዚህም ብቸኛው መፍትሄ ደግሞ እውቀት ነው» ይለናል::

«ችግሩ ግን እውቀት እንዴት ይገኛል? የተገኘው እውቀት ትክክለኛ እውቀት መሆኑንስ እንዴት እናውቃለን? ለመሆኑ እውቀት ሰጪውስ ማነው?» በማለት ይጠይቃል:: «አንድ ቀን በመንገድ ላይ እየተዘዋወርኩ ጠቢብ ሰው መፈለግ ጀመርኩ፤ እግሬ እስኪነቃ በአቴና ጎዳና ሙሉ ቀን ዞሬ ያገኘኋቸውን ሰዎች ብጠይቃቸው «ሁሉን እናውቃለን» ነበር:: አለማወቁን የሚያውቅ አንድ ሰው ሳላገኝ ወደ ቤቴ ተመለስኩ» በማለት ሶቅራጥስ ሃዘኑን ይገልፃል::

«የግሪክ ሰዎች እኔን እጅግ ጠቢብ ቢያደርጉም እኔ ደግሞ የማውቀው አለማወቄን ነው፤ አለማወቄን ማወቅ ብቻም ሳይሆን አውቃለሁ ብዬም



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

እስቤ አላውቅም» በማለት ስለ እራሱ ይናገራል::

የብዙዎችን ጠቢባን ምንም አለማወቅ ለማሳወቅ የሞከረው ደፀ ሰው ከወዳጆቹ በላይ ያተረፋቸው ጠላቶች እጅግ የበዙ ነበሩ:: ለመሆኑ ጠላቶቹ ለምን በዙ? እንዴትስ አጠፉት? ሃሣብ አስጀምሮ ላላስጨረሰን ሶቅራጥስ ምስጋና ይግባውና የዚህን ጠቢብና ፈላስፋ ቀሪ ታሪክ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለስበታለን::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# «ሳያስቡ ከመኖር እያሰቡ መሞት ይሻላል»

*አንድ ቀን ሶቅራጥስ ዘወትር ወደሚያስተምርበት አደባባይ በማለዳ ወጥቶ ቆመ::* የአቴና ሕዝብ እንደልማዱ የሶቅራጥስን ትምህርት ለመስማት በዙሪያው ከበበው:: እሱ ግን ዓይኑን አንድ ቦታ መሬት ላይ ተክሎ በሐሣብ ሄዷል:: ሕዝቡ መጠበቅ ጀመረ:: አንድ ሰዓት... ሁለት ሰዓት... ስድስት ሰዓት... ግማሹ ለምሳው መበተን ጀመረ:: የሶቅራጥስ ዓይኖች ግን ከተተከሉበት፣ አካሉም ከቆመበት አልተነቃነቀም::

መጨረሻው ምን ይሆን? ብሎ በዙሪያው ተሰብስቦ የሚጠብቀው ሕዝብ በጉጉት ማማጥ ጀመረ፤ ለምሳው የሄደውም ተመልሶ በዙሪያው ክምችቱ በዛና መጨረሻውን የሚጠብቀው ቁጥር ጨመረ:: መምሸት ሲጀምርና ግማሹ ወደ ማደሪያው መበተን ሲይዝ መጨረሻውን ሳላይ አልሄድም ያለው ደግሞ በአዳሩ ቆርጦ መጠበቁን ያዘ:: ታሪኩን ለማሳጠር ሶቅራጥስ በዚያ ሁኔታ ሃያ አራት ሰዓት ሞላው:: በዙሪያው የተሰበሰበው ሕዝብ አብዛኛው ቆሞ በዋለበት ቦታ እየተቀመጠ እንቅልፍ ይዞት ሄዷል::

መጨረሻውን ለማየት እጅግ ጓጉተው ያደሩት ጥቂቶች ደግሞ በንቃት አፍጥጠው ሲከታተሉ ሶቅራጥስ ከጭንቅላቱ ነቅነቅ አለና አንድ ነገር እንዳገኘና እንደተረዳ ፈገግ ብሎ መራመድ ጀመረ:: በሁኔታው



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ከተገረሙት አንዱ ተከተለውና «አንድ ቀንና አንድ ሌሊት የምንጠብቀው አንተን ነበር:: ለመሆኑ ምን ስታደርግ እንደነበር ልትነግረን ትችላለህ?» በማለት ጠየቀው:: የሶቅራጥስ መልስ አጭር ነበር:: «እያሰብኩ!»::

ለዚህም ይመስላል አብርሃም ኮፕላን "The New World of Philosophy" በሚለው መጽሐፉ «ሶቅራጥስ ፍልስፍናን ከተሰቀለችበት ደመና አውርዶ ገበያ መሀል ጣላት፣ ገበያተኛው ግን አሁንም የሚፈልጋት ከደመናው ውስጥ ነው» ብሏል::

«ሰው ከእንስሳ የሚለየው በማሰቡ ነው» የሚለው ሕግ ለሶቅራጥስ ቦታ የለውም፤ ምነው ቢሉ «ማሰብ የለየው ሰውን ከእንስሳ ሳይሆን ሰውን ከሰው ነው» ይለናል:: «ለግሪክ አማልክት ሕዝቡ የሚሰግደው ስለሚያምንባቸው ሳይሆን ማሰብ ስለማይችል ነው» ይል ነበር:: በተለይም ከፕሌቶ ጀምሮ ተከታዮቹ የነበሩትን በሙሉ በዚህ እውቀት ሊያጠምቃቸው ተነሣ::

«ሰው በውስጡ ያለውን ብቃት ቢረዳ አሁን ያለበት ቦታ ባላፈረው ነበር... ማሰብ የሚችለው ፍጡር ማሰብ ለማይችሉት አማልክት እንዴት ይሰግዳል?» በማለት ጠይቆ ለመሰዋት ያበቃውን ሎጂክ በተከታዮቹ ልብ ውስጥ ዘራ::

ይህ ትምህርቱና አስተሳሰቡ በአቴና ወጣቶች ዘንድ መወደድና መከበርን ቢያተርፍለትም በአቴና ሽማግሌዎች ግን ከመጠላት ብሎም ከመጥፋት አላተረፈውም:: «አማልክቶቻችንን ተሳደበ፣ አዋረደን፣ የወጣቶቹን ልብ በከንቱ ትምህርቱ በከለ... ወዘተ» የሶቅራጥስ ወንጀሎች ሆኑ:: በተለይም ደግሞ በሶፊስቶች ዘንድ (ስለ ሶፊስቶች የፍልስፍና እምነት ወደፊት እናያለን) ከፍተኛ ጥላቻን አተረፈ:: ለሶፊስቶች መልካም ወይም መጥፎ፤ ሐሰት ወይም እውነት የለም:: በምድር ላይ ከተሳካለ አንተ እውነተኛና መልካም ሰው ነህ:: ስኬትህ በማንኛውም ወንጀል ላይ የተመሠረተም ቢሆን ለሶፊስቶች ቁም ነገሩ «መጨረሻ ላይ ተሳክቶልሃ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ወይ?» ነው:: ይልቁንም ሶፊስቶች አስተማሪነታቸው ለሀብታሞች ብቻ ስለነበር የአቴና ሀብታሞችና አዛውንቶች በሶቅራጥስ ላይ ውንጀላ ሲጀምሩ ከፍተኛ እገዛ ማድረጋቸው ይታወቃል::

ለምሳሌ የአቴና አማልክት ስለ ቅድስና የነበራቸውን አሳቤ አስመልክቶ ከጊዜው ጠቢባን ጋር ሶቅራጥስ ያደረገውን ምልልስ የእሱ ደቀመዝሙር ፕሌቶ ከፃፈው በኋላ Lane Cooper; Plato: The Collected Dialogues (ፕሌቶ ሄራሊተስ በማለት ይጠራቸው ነበር::) በማለት ያስፈረውን እንመልከት::

ሄራሊተስ:- «እግዚአብሔር ቅድስናን ይወዳል፤ ተቃራኒውን ደግሞ ይጠላል::»

ሶቅራጥስ:- «ይህን አባባላችሁን ራሱን እንፈትነው:: አንድ «አምላክ» ወይም ሰው ይሄን ብያለሁ ስላለ እንቀበለዋለን? ወይስ እንፈትነዋለን?»

ሄራሊተስ:- «ብንፈትነውም ይህ ቃል ዘላለማዊና ትክክል ነው»

ሶቅራጥስ:- «አንድ ነገር ቅዱስ ነው የምንለው አማልክት ፈትነውት ቅዱስ ስለሆነ ነው? ወይስ ቅዱስ ነው ስላሉ?»

ሄራሊተስ:- «አባባልህን አብራራው::»

ሶቅራጥስ:- «ቅድስናውና እሱን የሚሸከመው የተቀደሰው ሁለት አካል ናቸው፤ የሚታየውና የሚያየው አካል አሁንም ሁለት ነገሮች ናቸው፤ እንዲሁም የሚመራውና የሚመራ ሁለት ናቸው፤ በነዚህ ሁሉ ሁለቱ ነገሮች እንዴት እንደሚለያዩና፤ ልዩነታቸውም ይገባችኋል?»

ሄራሊተስ:- «አዎን ይገባናል::»

ሶቅራጥስ:- «በዚሁ መንገድ ማፍቀር አንድ ነገር ሲሆን መፈቀርም እንዲሁ ሌላ ነው::»

ሄራሊተስ:- «ትክክል::»

ሶቅራጥስ:- «አንድ ነገር የሚታየው በሌላ አካል ለመታየት ስለሚችል ሳይሆን ነገር ግን ሌላ አካል ስላየው ነገሩ ሊታይ ቻለ:: ወይም አንድ ነገር ተመሪ የሆነው ነገሩ በራሱ ተመሪ ስለሆነ አይደለም፤



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ግዛብ

ነገር ግን መራ ስላለው ነገሩ ተመራ ሆነ:: ወይም አንድ አካል ሸክም የሆነው በራሱ ሸክም ስለሆነ አይደለም፤ ነገር ግን ተሸካሚ ስላለው ነገር ሸክም ሆነ:: ይህ ማለት አንድ ውጤት በራሱ ላይ የመጣበት አካል ውጤቱ የራሱ ሳይሆን ምክንያት ስላለው ነው:: ውጤት የሆነ ነገር በራሱ ውጤት አያመጣምና...»

ሄራሊተስ:- «ትክክል::»

ሶቅራጥስ:- «በዚህ ከተስማማን አንድ ነገር ሲፈቀር የተፈቀረው አካል ወደ ሌላ ነገር ይለወጣል?»

ሄራሊተስ:- «አይለወጥም::»

ሶቅራጥስ:- «እንግዲህ አንድን ነገር የሚያፈቅሩት ሰዎች ያፈቀሩት በራሱ የሚፈቀር ስለሆነ አይደለም፤ ነገር ግን ተፈቃሪ ያደረገው በሌሎች መፈቀሩ ነው?»

ሄራሊተስ:- «የግድ ነው::»

ሶቅራጥስ:- «ስለ ቅድስናስ ምን ትላላችሁ? እንደ እናንተ ክርክር ቅድስና በአማልክት ሁሉ ዘንድ የተፈቀረ ነው::»

ሄራሊተስ:- «ትክክል::»

ሶቅራጥስ:- «በራሱ ቅዱስ ስለሆነ ወይስ በአማልክት ስለተፈቀረ?»

ሄራሊተስ:- «በራሱ ቅዱስ ስለሆነ::»

ሶቅራጥስ:- «እንግዲያውስ ቅዱስ ስለሆነ እንጂ የተፈቀረው፤ ስለተፈቀረ አይደለም ቅዱስ የሆነው?»

ሄራሊተስ:- «ይመስላል::»

ሶቅራጥስ:- «ወይስ ቅድስና በአማልክት ዘንድ ተወዳጅና አስደሳች ስለሆነ ተፈቀረ ማለት ነው?»

ሄራሊተስ:- «እሱም ጥርጥር የለውም::»

ሶቅራጥስ:- «ስለዚህ ቅዱስ ነገር ቅዱስ የሚሆነው አማልክት ስለሚወዱት እንጂ በራሱ ቅዱስ ስለሆነ አይደለም፤ አልያም በአማልክት የተፈቀረው ቅዱስ አካል እና ቅድስና ሁለት የተለያዩ አካል ናቸው



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ማለት ነው?»

ሄራሊተስ፡- «ይኸማ እንዴት ሊሆን ይችላል?»

ሶቅራጥስ፡- «መጀመሪያ በተስማማነው መሠረት ቅዱስ የሆነው ነገር የተፈቀረው በራሱ ቅዱስ ስለሆነ እንጂ ስለተፈቀረ ቅዱስ አልሆነማ?»

ሄራሊተስ፡- «ትክክል፡፡»

ሶቅራጥስ፡- «ነገር ግን አሁን የማየው አማልክት በቅድስና ደስ የሚላቸው ስለአፈቀሩት ነው፤ ወይስ ቅድስና በራሱ ተፈቃሪ ስለሆነ?»

ሄራሊተስ፡- «ሁለተኛው ትክክል ይመስላል፡፡»

ሶቅራጥስ፡- «እንዲህ ከሆነ ቅድስና በራሱ ምክንያትም ውጤትም ነው ማለት ነዋ?»

ሄራሊተስ፡- «ትክክል፡፡»

ሶቅራጥስ፡- «ታዲያ የሚታይ የሚኖረው የሚያይ ስላለ ከሆነ፣ ተመሪ የኖረው መሪ ስላለ ነው ካልን፤ ሸክም ያለው ተሸካሚ ስለኖረ ከሆነ በዚህም ሕግ ከተስማማን በራሱ ምክንያትና ውጤት የሆነውን፤ የሚታይም የሚያይም የሌለውን ቅድስናን አማልክት እንዴት አዩት?»

ሄራሊተስ፡- «ይሄ ከባድ ፈተና ነው፡፡»

ሶቅራጥስ፡- «ከመሠረቱ አንድ ነገር በራሱ ምክንያትም ውጤትም ሊሆን እንዴት ይችላል? አንድ ነገር የሚፈቀረው የሚያፈቅረው ሲኖረው ከሆነ ነገሩ በራሱ ተፈቃሪ ሳይሆን የተፈቀረ ነገር ነው ማለት ነዋ...?»

የሶቅራጥስ እነዚህና መሰል ፈተናዎቹ የግሪክ አማልክትን አራክሷል፤ የወጣቶቹንም ልብ አበላሽቷል በሚል ክስ ተመሰረተበት፡፡

ሶቅራጥስ በአቋሙ ኢ-አማኒ አልነበረም፡፡ የብዙ አማልክትን መኖር ግን የሚነቅፍ በአንድ አምላክም መኖር የሚያምን ነበር፡፡ አንድ ማለዳ ከቤቱ ወጥቶ ወደ አደባባይ ሲያመራ በእሱ ጉዳይ የፍትሕ ወንበር ተዘርግቶ «ምን እንፍረድበት?» ሲባባሉ ተመለከተ፡፡ ብዙም አልተደነቀም፡፡ «ከእነዚህ ሰዎች ከእዚህ በላይ አልጠብቅም» በማለት ወደሚያስተምርበት አደባባይ አቀና፡፡



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

በማግስቱ 500 አባላት ያሉት የዳኞች ችሎት ተቋቋመና ሶቅራጥስ ጉዳዩን እንዲያስረዳ ተጠየቀ፡፡

«የወጣቶቹን ልብ አልበከልኩም፤ የእኔ ሥራ እውነትን መፈለግ ብቻ ነበር፡፡ በፍለጋውም እንዲያግዙኝ አስተማርኳቸው... እኔን የምትከሱኝ ጥፋተኛ ሆኜ ሳይሆን የእናንተን አላዋቂነት በመግለጤ ነው፡፡ የእናንተን አላዋቂነት የገለጥኩት ደግሞ ስለምጠላችሁ ሳይሆን ከፍ ሳደርጋችሁ ስላሰብኩ ነበር፡፡ አንድ እውነት ግን አለ፡፡ ሰው ሳያስብ ከሚኖር እያሰበ ቢሞት ይሻለዋል፡፡ እንደእናንተ ከመኖር እንደእኔ መሞትም እጅግ የተሻለ ይመስለኛል፡፡ ይሁንና ሰው ለመልካምና ለክፉ ሊፈረድበት ይችላል እንጂ እንዲሞትና እንዲኖር ሊፈረድበት አይገባም፡፡ እኔን ብትገድሉኝ በራሳችሁ ላይ ትልቅ ስህተት ሰራችሁ፡፡ ምክንያቱም እኔ ብሞት አንዳች ስህተት አልፈፀምኩም፤ እናንተ ግን እኔን በመግደል ወንጀለኞች ትሆናላችሁ» በማለት ተናገረ፡፡

ችሎቱ በድምፅ ብልጫ ሞት ፈረደበት፤ ይኸው ፍርድም ተነገረው፡፡ ሶቅራጥስም፡- «ለእኔ ሞት ከሁለት ነገሮች አንዱ ነው፡፡ የመጀመሪያው ወደ ዘላለማዊ ዝምታ ውስጥ መግባት፤ ወይም ሁለተኛው ወደ ሌላ ዓለም መሸጋገር ነው፡፡ ለእኔ ሁለቱም አስደሳች ነው፡፡ ወደ ዘላለማዊ ዝምታ ብገባም እንደእናንተ የሚረብሸኝ አይኖርም፤ ወደ ሁለተኛው ዓለምም መሸጋገር ከሆነ እርግጠኛ ነኝ በዚያ ጥላቻ፣ ቅናት፣ ስድብ ብሎም አሁን እናንተ እንደምታደርጉት የሞት ፍርድ የለም» አለ፡፡ አስገዳዮቹም ወስደው አሰሩት፡፡

ከመገደሉ አንድ ቀን በፊት የእሱ ደቀመዝሙር የነበረው ክሪቶ ገንዘብ ሰብስቦ ለጠባቂዎች ጉቦ ለመስጠትና እሱን ለማስመለጥ እየሞከረ እንደሆነ ነገረው፡፡ ሶቅራጥስም፡- «በዘመኔ ሁሉ ለሕግ እንደኖርኩ አሁንም ለእሷ ለመሞት እንደተዘጋጀሁ ታውቃለህ፤ ሕግን ገድዬ እኔ ነፃ ከምሆን እኔ ሞቼ ሕግ ነፃ ትሁን» በማለት የፕሌቶን ሃሳብ ሳይቀበለው ቀረ፡፡ ለዚህም ነው የሶቅራጥስ ተከታዮችና አድናቂዎች፡- «ማሰብ ሳይችሉ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

እንደ ካሊባን ዙፋን ላይ ከመቀመጥ በወህኒ ቤት እንደ ሶቅራጥስ እያሰቡ መኖር ይሻላል» የሚሉት::

በማግስቱ መርዝ የያዘው አስገዳይ ወደ ሶቅራጥስ ቀረበ:- «መርዙን ትጠጣና በእግርህ መንቀሳቀስ ትጀምራለህ፤ ከትንሽ ሰዓታት በኋላ እግርህ መያያዝ ይጀምራል፤ ያን ጊዜ እግርህን በያዘህ ቦታ በጀርባህ ተኛና ፊትህን በልብስህ ሸፍን፤ በቅፅበትም ትሞታለህ» አለው::

ሶቅራጥስም መርዙን ተቀበለ:: ከመጠጣቱ በፊት ለአስገዳዩ የመጨረሻውን ቃል ተናገረ:- «እኔ ወደ ሞት አንተ ደግሞ ወደ ሕይወት እየሄድን ነው፤ የትኛው ይሻላል፤ እግዚአብሔር ያውቃል!» ... መርዙን ጠጣ::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# እምነትህ አዕምሮህን ካልገዛ፣ አዕምሮህ እምነትህን ይገዛል

የዜን ቡድሂስት እምነት አራማጅ ከወንዝ ዳር ተቀምጦ በተመስጦ ውስጥ ባለበት ሰዓት አንድ ወጣት ዋናተኛ በጩኸቱ አቋረጠው::

«መምህር ሆይ! የአንተ ደቀ መዝሙር መሆን እፈልጋለሁ»::

«ለምን?» በማለት መምህሩ ጠየቀው::

«ምክንያቱም እግዚአብሔርን ማግኘት ስለምፈልግ» ሆነ የወጣቱ መልስ::

መምህሩ ወደ ወንዙ በቅፅበት ዘሎ ገባና የወጣቱን ጭንቅላት በወንዙ ውስጥ ለጥቂት ደቂቃ ደፍቆ ይታገል ጀመር:: ወጣቱ እንደምንም ተንፈራግጦ እየቃተተ ከወንዙ መውጣት ሲጀምር መምህሩ:- «አንድ እውነት እስኪ ንገረኝ፤ አሁን ከውኃ በታች ሆነህ በሕይወት እጅግ የፈለከው ነገር ምንድን ነበር?» በማለት ጠየቀው::

«አየር!» በማለት ወጣቱ ጮኸ::

«ጥሩ ነው» አለ መምህሩ:: «ወደ ቤትህ ሂድ፤ አሁን አየር የፈለከውን ያህል እግዚአብሔርን መፈለግ ስትጀምር ያን ጊዜ ወደ እኔ ተመልሰህ ና» አለው::

* * *

«ማንም በምድር ላይ የኖረ ሰው ቢያንስ ለአንድ ቀን ከንቱና



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

የማይረባ ነገር ሳይናገር አልቀረም...» ይለናል ታላቁ ጠቢብ ሞንቴኝ፦ «ይህንን ድርጊት ለአንድም ቀን አድርጎት አያውቅም የምለው ሰው ቢኖር ግን ዜን ነው» በማለት ይናገራል።

ዴይስ ሱዙኪ ስለ ዜን እምነትና ፍልስፍና በሰፊው ያሳወቀን ራሱም የዜን እምነትና ፍልስፍና መምህር የነበረ ሰው ነው። ሱዙኪ እንዲያውም ዜን የሚለውን ቃል የእንግሊዝኛ ቃል ያደረገ ብቸኛው ሰው በመባልም ይታወቃል። «ማንም የዜን ተከታይ ነኝ ሲል ቡድሂስት ነኝ ከማለቱ በተጨማሪ ራሱን ከጃፓን የባህል እምነት ጋር ለማቆራኘቱ የሚያጠራጥር አይሆንም» ይለናል። የኖህ ድራማ፣ የሻይ ስነ ስርዓት፣ የአትክልት ቦታ አያያዝ፣ የሰይፍ ውድድር... እነዚህ ባህሎች ሁሉ የዜን እምነት ውጤቶች ናቸው። የዜን ፍልስፍና ከምዕራባውያኑ የሚለየው ዋናው ነገርም ይኸው ነው – «ህያው ፍልስፍና» (Living Philosophy) መሆኑ።

ዜን ሃይማኖት አይደለም፤ ቅዱሳት መፃህፍት ወይም ሌላ ሃይማኖታዊ ምልክት የለውም፤ የተለየ ባህልም ሆነ አምልኮ አይደረግለትም። የቡድሂዝም አንድ ቅርንጫፍ የሆነ እምነት ቢሆንም ከእሱ የሚለየው ዋናው ነገር በስነ መለኮት ትምህርት ላይ አለመመስረቱ ነው። ዴይስ ሱዙኪ እንደሚለን፦ «የፈጣሪን ስራ ከማየት አልፈህ የእሱን ስራ ጠያቂ ያደረገህ ማነው?» ይለናል። የዜን ተከታይ ስትሆን ስለ እግዚአብሔር አያገባህም። እሱም ስራውን ይሰራል፤ አንተም ስራህን ስራ... እንዲያውም «በምድር ላይ ስትኖር ራስህን እንደሞተ ሰው ቁጠረው» ይላል። «ምክንያቱም ራስህን እንደሞተ ሰው ከቆጠርህ ለመኖር የሚያጓጓህ፤ ለመሞትም የምትፈራው አንዳች ነገር አይኖርም። መፍራት ስታቆም ደግሞ ማሸነፍ ትጀምራለህ... ለምሳሌ የምዕራባውያን እምነትና ፍልስፍና ዛሬን ስትኖር በምድር ላይ የምትኖርባት የመጨረሻዋ ቀን አድርገህ አሳልፋት' ነው። በዜን ግን ዛሬን ራሷን እንደ ትናንት አድርገህ ውሰዳት'» ይሉናል።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ስለ ዜን ፍልስፍናና እምነት ከመናገሬ በፊት ራሱ ዜን ምንድነው የሚለውን ለአንባቢዎቼ ትንሽ ላካፍል:: ዜን የዜን ቡድሂዝም አንዱ መጠሪያ ነው:: ዜን ቡድሂዝም መልክ እየያዘ የመጣ የፍልስፍና የእምነት ዘይቤ የሆነው በ6ኛው ክ.ዘ. ሲሆን ይህ እምነት የሆነው የቻይናና የጥንቱን የቡድሂዝም ሃሳብ በተለይም የማሃያናን ባህል በመሆኑ የተመሰረተ ነው:: እንቅስቃሴውን በዋናነት የመሩት እምነቱን የተቀበሉት ጃፓናውያን እንደሆኑ ሲታወቅ ወደ ምዕራቡ ዓለም የገባ ፍልስፍና ከሆነም ቆይቷል::

ዜን የሚለው ቃል የመጣው ከጃፓን ሲሆን ትርጉሙም «በተመስጦ ማሰላሰል» (Meditation) ማለት ነው:: ማሰላሰል የሚለው የዜን ትርጉም በሁለት መንገድ የሚከናወን ሲሆን የመጀመሪያው «ዮጋ» የሚሉትና ጥልቅ የሆኑ ፍልስፍናዎችንና አባባሎችን በተመስጦ በማሰላሰል የሚካሄድ ሲሆን ይህ በዜን ዘንድ አእምሮን የማሰራት ጥበብ እንደሆነ ታምናበታል:: ሁለተኛው ከላይ እንደ ምሳሌ የጠቀስናቸው የሻይ ስነ ስርዓት፣ የሰይፍ ውድድር... የመሳሰሉት ናቸው::

የዜን እምነት አራማጅ ሆኖ በሚገባ ተምሯል የሚባለው «ሳቶሪ» በሚባለው ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ብቻ ነው:: «ዜን ሆኖ ሳቶሪ ያልሆነ ሰው ማለት ፀሐይ ሆኖ ሙቀትና ብርሃን የሌለው እንደማለት ነው» ይላሉ የዜን እምነት ተከታዮች:: ዱይስ ሱዙኪም «የአንድን ነገር ተፈጥሮ በጥልቀት የመረዳት ጥበብ ወይም ችሎታ ሳቶሪ ነው» ይለናል::

ዜን ስትሆን ፍፁም ነፃነት ትፈልጋለህ፤ ይህ ነፃነትህን እግዚአብሔር እንኳ እንዲሻማህ አትፈልግም:: ዱይስ ሱዙኪ:- «ለነገሩ ራሱ እግዚአብሔር በአንተ ምን አገባውና፤ እንዲያውም እግዚአብሔር ሲናርህ የምትቀበለው የእግዚአብሔር የሆነን ነገር ብቻ ይሆናል፤ ይህ ደግሞ እንዳታስብ ራስህን በጣም መግታት ነው» ይለናል::

ከታሪክ እንደምንረዳው ዜን ቡድሂዝም የመጣው ከሳዳሀርታ ጉተማ ትምህርት ነው:: ሳዳሀርታ ጉተማ ከክርስቶስ ልደት 500 ዓመት በፊት



Scanned by CamScanner
@BOOKALEM

የአሁኗ ሕንድ ልዑል ነበር:: በዙሪያው በሚያየው የሰው ልጅ መከራ ብሎም አላዋቂነት የታወከው የ29 ዓመቱ ልዑል የምቾት ኑሮውን በእውቀት ፍለጋ ሊለውጠው ተነሳ:: ከ6 ዓመት አድካሚ ጥረት በኋላ ከፍተኛውን የዕውቀት ደረጃ ተካነ:: እንግዲህ ከዚህ በኋላ ነው «በዕውቀት የነቃው» (One who is awake) ተባለ:: በሕንድም ለዚህ ሰው ቡድሃ የሚል ስም ተሰጠው:: በጥቅሉ ስናየው ይህ በእውቀት የነቃው ሰው በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ ለለውጥ የተጋለጡ መሆናቸውንና ሳይለወጥ የሚቀር አንዳች ነገር አለመኖሩን የተረዳ ነው:: «በራሱ ቋሚ ካልሆነ ነገር ጋር ራስን ማቆራኘት ትርፉ መከራ ነው:: ስለዚህም አንድ ሰው ቋሚ ካልሆነው ምድራዊ ነገር ራሱን ቢያላቅቅ (ከራሱም ጨምሮ) ያን ጊዜ ከመከራ ነፃ ይሆናል» ይላል::

ይህ የቡድሃ ትምህርት ሲወርድ ሲዋረድ ለዘመናት በተከታዮቹ ሲታመንበትና እነሱም ሲያስተላልፉት ቆዩ:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በ475 ዓ.ዓ. ቦድሂዳርማ ከሕንድ ወደ ቻይና ተጉዞ ይህንኑ ትምህርት በቻይና ምድር አስፋፋው:: እንግዲህ በቻይና ምድር የገባው ቡድሂዝም አስቀድሞ በሃገሩ ከነበረው የታዎኢዝም እምነትና ፍልስፍና ጋር ተቀላቀለና የቻን የቡድሂዝም ትምህርት ቤትን አስገኘ:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1200 ዓ.ዓ. የቻን ቡድሂዝም ትምህርት ከቻይና ወደ ጃፓን ተሻገረና በዚያ የዜን ቡድሂዝም (ዜን) ተባለ:: የዜን ቡድሂዝም አመጣጥ በአጭሩ ይህን ሲመስል ለመሆኑ እምነትና ፍልስፍናው እንዴት ያለ ነው::

የዜንን እምነትና ፍልስፍና በሰፊው ካራመዱት አንዱ ዴይስ ሱዙኪ መሆኑን ከላይ ገልፀናል:: አንድ ወቅት አንድ የዜን መምህር ተማሪው ስለዘላለማዊ ሕይወት በተለይም ስለ ገነት ምን ማሰብ እንዳለበት ሲጠይቀው:- «እሱን ለቡድሃ ተውለት፤ እሱ የእኛ ስራ አይደለም» አለው:: በሌላ ጊዜ ይኸው መምህር ለመሞት በሚያጣጥርበት የመጨረሻ ሰዓት ተማሪው ወደ አልጋው ቀርቦ:- «እግዚአብሔር ይቅር የሚልህ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ይመስልሃል?» በማለት ሲጠይቀው... «እሱንማ አትጠራጠር፤ ሌላ ምን ስራ አለው?» በማለት መልሶለታል::

የዜን እምነትና ፍልስፍና መገለጫው ዝምታ ነው:: ታዲያ መገለጫው ዝምታ የሆነ እምነትና ፍልስፍናን እንዴት ነው የምትማሩት፣ ተብለው ሲጠየቁ ተከታዮቹ:- «እኛ ወደ ዜን መጣን እንጂ እሱ አልመጣብንም፤ ወደ እሱ ስንመጣም የጠበቅነው መማርን ነበር፤ ነገር ግን የተማርነው መጠበቅን ራሱን ማስወገድ ነው» ይላሉ:: አንድ ቀን አንድ መነኩሴ ወደ ዜን መምህር መጣና ስለ ዜን ቡድሂዝም እንዲያስተምረው ጠየቀው:: መምህሩም:- «ሰው በማይኖርበት ሌላ ቀን ተመልሰህ ና፤ ያን ጊዜ አስተምርሃለሁ» አለው:: መነኩሴውም ከብዙ ቀን እልህ አስጨራሽ ጉትጉትና መመላለስ በኋላ መምህሩን አገኘው:: «ዛሬ ማንም የለም፤ የዜን ሚስጥርን አስተምርሃለሁ ብለህ ቃል ገብተህልኛል» አለው:: መምህሩ:- «ጠጋ በልና በጆሮህ ልንገርህ» አለው:: መነኩሴውም ይኸንኑ አደረገ:: «ዜን በቃል ሊገለፅ የማይችል ነገር ነው» በማለት መምህሩ ስለ ዜን አስተማረው:: እንግዲህ የዜን ተከታዮች የዝምታ እምነት እስከዚህ ድረስ ነው:: ይሁንና አንዳንድ ፈላስፎች:- «ዜን በቃል ሊገለፅ የማይችል ነገር ነው ማለት በራሱ ዜንን መግለፅ ነው» በማለትም ይተቻሉ::

በሌላ ቀን ደግሞ አንድ ተማሪ ወደ ዜን መምህር መጣና «በቃላት ንግግር ሳልጠቀም ነገሮችን መማርና መረዳት የምችልበትን መንገድ አሳየኝ» አለው:: መምህሩ «በል ቃላት ሳትጠቀም ጥያቄህን ጀምር» አለው:: ነገሩ እዚያ ላይ አበቃ:: ዴይስ ሱዙኪ እንደሚነግረን:- «የዜን መምህር ማለት የዛፍ ቅርንጫፍ በጥርሱ ነክሶ የተንጠለጠለ ሰው ማለት ነው:: ለአንተ ጥያቄ መልስ አይሰጥም፤ ምክንያቱም መልስ ለመስጠት አፉን ሲከፍት ይወድቃልና:: ስለዚህ የዜን ቋንቋ ተግባር እንጂ ቃላት አይደለም» ይለናል::

የዜን ተከታይ መሠረቱ የቱንም ያህል ዝምታ ነው ቢባልም መምህሩ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ተማሪውን የሚያስተምርበት ዘይቤ በጃፓንኛ ሞንዶ ይባላል። ይህም በቃለ ምልልስ መምህሩ ተማሪውን ወደ ሳቶሪ ደረጃ የሚያደርስበት ነው። ስለ ዜን እምነትና ፍልስፍና ይበልጥ ያሳያሉ ያልኳቸውን ወጐች ትንሽ ልጨምር።

አንድ ቀን አንድ የዜን መነኩሴ የሆነ ወጣት ቶኪዮ ከተማ የሚገኝ ዩኒቨርስቲን ጎብኝቶ ወደ መምህሩ ሲመለስ የክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ አንብቦ ያውቅ እንደሆነ መምህሩን ጠየቀው። አንብቦ እንደማያውቅ ሲገልፅለት ተማሪው እንዳነበበና አንድ ይዞ እንደመጣም ነገረው። መምህሩም «እስኪ ጥቂት አንብብልኝ» አለው። ተማሪውም ከማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በመለወጥ ተራራ (Mountain of Transfiguration) የተፈፀመውን አነበበለትና እየሱስ ስለ ምድር አበቦች የተናገረውን ማንበብ ሲጀምር መምህሩ አቋርጦት ተነሳና «አየህ! ይኸን ቃል የተናገረው ሰው ማንም ቢሆን በጣም አዋቂ ነው፤ እኔም እስከዛሬ ያስተማርኩህ ይኸንኑ ነበር» በማለት ጥሎት ሄደ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ የዜን እምነትና ፍልስፍና ተከታይ መነኩሴ በበረሃ ውስጥ ጠፋ። በረሃብና በውኃ ጥም እጅግ ተንገላቶ በነበረበት ሰዓት ከአንድ እንደ እሱ በበረሃ ጠፍቶ ከሚንገላታ መንገደኛ ጋር ተገናኙና ጉዞ ጀመሩ። በጣር ጉዞ ላይ እንዳሉ ወደ አንድ ትልቅ ቅጥር ደረሱ። ቅጥሩ ቁመቱ ትልቅ በመሆኑ በውስጡ ያለውን ለማየት ባይቻላቸውም የውኃ ፏፏቴና የወፎች ጫጫታ በግልፅ ይሰማቸው ነበር። በአጥሩ ላይም አሻግሮ ፍሬያቸውን ያንዠረገጉ ዛፎች ይታያሉ። መንገደኛው በቅፅበት በአጥሩ ላይ ዘሎ በመውጣት የበረሃ ጓደኛውን እንኳን ለመሰናበት ትዕግስት አጥቶ ወደ ቅጥሩ ውስጥ ለመዝለል ተዘጋጀ። ዜኑ ግን ወደ በረሃ ተመልሶ ጉዞውን ጀመረ። ይሄን ጊዜ ቅጥሩ ላይ ቆሞ የዜኑን ድርጊት ሲመለከት የነበረው ሰው «ወዴት ነው የምትሄደው?» በማለት ጮኸ። «በበረሃ ላይ እንደኔው የጠፉ ጓደኞቼን ይዤ ልመጣ ነው...» አለው። «እርግጠኛ ነኝ በዚያ ትሞታለህ!» በማለት



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

በድጋሚ ጮኸ:: ዜኑም «ብቻዬን ገነት ከምገባ ከሰው ጋር ገሃነም ውስጥ ልኑር» በማለት ጉዞውን ቀጠለ::

ዴይስ ሱዙኪ እንዳሉና ዋነኛው የሰው ልጅ ችግር «ቃላትን ከእውነታው ጋር ማምታታት ነው» ይለናል:: ይሄንኑ የዜን ሃሳብ በምሳሌ ሲገልፅልን፦ «ዓሣ የምንይዝበት ቅርጫት ዓሣ እስከያዘልን ድረስ ጥሩ ነው:: ነገር ግን ዓሣውን ለመመገብ ጠረጴዛችን ላይ ካደረሰልን በኋላ ስለ ቅርጫቱ መጨነቅ ምን ይሉታል?» በማለት ጠይቆ «የቃላትም ሥራ ይኸው ነው::» ብሏል:: የዜን የፍልስፍና ወግ ሰፊ ነውና አሁንም ልቀጥል::

አንድ ቀን የዜን መምህር ከተማሪው ጋር ሲሄድ የቡድሃ ምስል ያለበት ቦታ ይደርሳሉ:: ተማሪው በቅፅበት ለቡድሃ ምስል ተደፍቶ መስገድ ሲጀምር መምህሩ ተጠጋና በጥፊ አጮለው:: ተማሪው «መምህር ሆይ፤ ለቡድሃ መስገድ የሚያኮራ አይደለምን?» በማለት ሲጠይቀው «እሱማ ነው፤ ነገር ግን የሚያኮራንም ነገር ለመተው መቻል እጅግ የሚያኮራ ነው» አለው::

በሌላ ቀን አንድ መነኩሴ ወደ ዜን መምህር መጣና... «ክረምት ይወጣል፤ በተራው ደግሞ በጋ ይመጣል፤ ከነዚህ ማምለጥ የሚቻለው እንዴት ነው?» በማለት ጠየቀው:: መምህሩ «ለምን ክረምት ሲሆን በሙቀት ወደምትቃጠልበት በበጋ ደግሞ በቅዝቃዜ ወደምትንቀጠቀጥበት ቦታ አትሄድም» አለው:: መነኩሴው «በእርግጥ እሱ የተሻለ ነው፤ መምህር ሆይ እንደሱ ዓይነት ቦታ የትነው የማገኘው?» በማለት ጠየቀ:: የመምህሩ መልስ አጭር ነበር፦ «ገሃነም»::

«ዜን ምንድነው?» በማለት ተማሪው ላነሳው ጥያቄ ከመምህሩ ያገኘው መልስ «ዜንማ አሁን የተናገርከው ነው» ነበር:: ዜን በየቀኑ ከምትናገረው፣ ከምትበላው፣ ከምትጠጣው ሌላው ይቅርና ከእንቅልፍህም ጋር በአልጋህ ላይ የተገናኘ ነው ይላሉ::

አንድ ማለዳ ሁለት የዜን ቡድሂስቶች ወደ አንድ መንደር ጉዞ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ጀምረው ሳለ በመንገዳቸው ላይ ያለው ወንዝ ዳር እንደደረሱ የሴት ልጅ ጩኸት ሰምተው ወደዚያው ይሮጣሉ:: በዚያም አንዲት ወጣት ሴት የወንዙ ውኃ እየገፈተረ ወደ መኻል ሲወስዳት አስተዋሉ:: በቅፅበት አንዱ ዜን ወደ ወንዙ ዘሎ በመወርወር እየዋኘ ደርሶ ተሸክሞ በማውጣት ከሞት አዳናት:: ሁለቱ ዜኖች ጉዞአቸውን ቀጥለው ትንሽ እንደሄዱ ከወንዙ ዳር ቆሞ ይመለከት የነበረው ዜን ማጉረምረም ጀመረ:: ወዲያውም «እኛ የዜን ቡድሃ ተከታዮች መቀደስ እንዳለብን ሴትን በእጃችን እንኳን መንካት እንደሌለብን ታውቃለህ:: እንዴት ሴት ልጅ በዛ ላይ ራቁቷን ትሸከማታለህ?» በማለት ጠየቀው:: «ወንድሜ እኔ የተሸከምኳትን ሴት ወንዙ ዳር ነው ትቻት የመጣሁ፤ አንተ ግን አሁንም ተሸክመሃታል» በማለት መለሰለት::

የምዕራባውያን የእምነት ፍልስፍና «አንድ ሰው የእውቀት ዛፍ የምታበቅለውን ፍሬ በላ፤ ክፉንና ደጉንም ለየ (አወቀ)» ነው:: በዜን ቡድሃ እምነት ደግሞ የሰው ታሪክ የሚጀምረው ካላዋቂነት ነው:: ከእውቀት ዛፍ እንጂ የእውቀትን ፍሬ አልበላም ይላሉ:: ዴይስ ሱዙኪ እንደሚለን ደግሞ «ወደ ዜን እምነት ስትመጣ አላዋቂነትህ እጅግ ጎልቶ ይሰማሃል» ይላል::

<u>በዜን እምነትና ፍልስፍና እምነትህ አዕምሮህን ካልገዛ፤ አዕምሮህ እምነትህን መግዛት ይጀምራል</u>:: የዜን መምህር አንድ ቀን ለተማሪዎቹ «ቡድሃ ማለት የእናንተ አዕምሮ ነው» በማለት አስተማራቸው:: ይህን የሰማ ተማሪ በነጋታው የተማረውን ሊያሰላስል ሰው ወደማይደርስበት ዱር ሄደ:: በዚያ ዱር ውስጥም ይህንኑ ሲያሰላስል ሃያ ዓመት አሳለፈ:: አንድ ቀን የዜን መምህሩ ሌላ ተማሪ በዚያ ጫካ ሲያልፍ አገኘውና «እባክህን የዜን መምህሩ ዋና ትምህርት አሁን ምንድነው?» ብሎ ጠየቀው:: አዲሱ ተማሪም «ቡድሃ ማለት የእናንተ አዕምሮ አይደለም የሚል ነው፤ እኔም ይሄን ላሰላስል እየሄድኩ ነው» አለው::

የዜን እምነት መሠረቱ ራስህን እንደሞተ መቁጠር ነው ብለናል::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ዴይስ ሱዙኪም ይህንኑ ሲያጠናክርልን «ሰው በእውነት ነፃ የሚሆነው ራሱን እንደሞተ ሲቆጥረው ነው» ብሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የዜን መምህር ለተማሪዎቹ ሲያስተምር ያካፈላቸው ነው ተብሎ በሚታመንበት ወግ የዜን ፍልስፍና ጉዞአችንን እናጠቃል፡፡

አንድ ገበሬ ዕድሜው ገፍቶ እርሻ ለመዋል ጉልበቶቹ ደከሙ፡፡ በዚህ ምክንያት ጊዜውን ከደጅ ተቀምጦ ማሳለፍ ጀመረ፡፡ ይህን የተመለከተ የገበሬው ልጅ በአባቱ ተቀምጦ መዋል ደስተኛ አልሆነም፡፡ «እንግዲህ አርጅቷል፤ ስለዚህ እኔ እንዳበላው ነው የሚጠብቅ፤ ነገር ግን በራሱ ከእንግዲህ ምንም ጥቅም የለውም» በማለት አሰበና ከእርሻው ሲመለስ የሬሳ ሳጥን ገዝቶ መጣ፡፡ በማግስቱም አባቱን ከእንቅልፉ ቀስቅሶ «በል ሳጥኑ ውስጥ ግባ» አለው፡፡ ሽማግሌው አባትም የታዘዘውን አደረገ፡፡ ልጅም አባቱን የከተተበትን የሬሳ ሳጥን ተሸክሞ ወደ ተራራ ጫፍ ላይ ወጣ፡፡ ከዚያ ሳጥኑን ቁልቁል ለመወርወር ወጣቱ ሲዘጋጅ የሽማግሌው አባቱን «አንዴ ክፈትልኝ!» የጥሪ ድምፅ ሰማ፡፡ ልጅም ሳጥኑን ከፍቶ አባቱን ምን እንደሚፈልግ ጠየቀው፡፡ አባትም «ልጄ ሆይ፤ ይህን የመሰለ የሬሳ ሳጥን ወደ ገደሉ ጥለህ ከምታበላሸው እኔን አውጣና ወርውረኝ፤ ሳጥኑን ልጆችህ ለአንተ ይጠቀሙበታል» አለው፡፡



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ለአንዱ የገነት መግቢያ፤ ለሌላው የገሃነም ደጅ ነው

«ጀምስ ቻፌንስ በአሜሪካ ሰሜን ካሮሊና ግዛት የሚኖር ሀብታም ገበሬ ነበር:: ከመሞቱ ጥቂት ዓመታት በፊት እ.ኤ.አ በ1905 በምስክሮች ፊት ኑዛዜውን አስነብቦ ፈረመ:: ከኑዛዜው ቃል መረዳት እንደሚቻለው ቻፌን ከነበሩት አራት ልጆች መካከል ለሦስተኛ ልጁ ለማርሻል የነበረውን ሀብት በሙሉ እንዲወርስ የሚፈቅድ ነበር:: በ1921 እ.ኤ.አ ቻፌን ሞተና በኑዛዜው መሠረት ማርሻል የአባቱ ሀብት ሙሉ ወራሽ ሆነ:: ይሁንና ከአራት ዓመት በኋላ ማለትም በ1925 እ.ኤ.አ የቻፌን ሁለተኛ ልጁ የሆነው ጀምስ (በአባቱ ስም ነው የሚጠራው) በህልሙ አባቱ መጥቶ እንዳነጋገረው ገልፆ በንግግራቸውም ወደ እናታቸው ቤት ሄዶ አዘውትሮ ይለብሳት የነበረውን ኮት እንዲፈትሽ እንዳዘዘው ተናገረ:: በአባቱ ትዕዛዝም መሠረት ወደ እናታቸው ቤት ሄዶ ኮቱን መፈለግ ሲጀምር በአባታቸው ቃለ ኑዛዜ መሠረት ኮቱም ለማርሻል እንደተሰጠ እናቱ ነገረችው:: ጀምስ ምስክሮች ይዞ ወደ ማርሻል ቤት በመሄድ ኮቱን መፈለግ ጀመረ:: ከጥቂት ፍለጋ በኋላ የአባቱ ኮት ተገኘና ኪሱ ሲበረበር በአንዱ ውስጥ የተጠቀለለ ወረቀት ተገኘ:: በወረቀቱ ላይ ሁሉም እንደመሰከሩት የአባቱ ፅሁፍ ሰፍሮ ነበር:: እንዲህም ይነበባል:- «የአባቴ የነበረውን መፅሐፍ ቅዱስ ፈልጋችሁ ከዘፍጥረት መጽሐፍ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ላይ 27ኛውን ምዕራፍ እንዳበሩት» ይላል:: በዚህም መሠረት ሀብቴ ለአራቱም ልጆች ሊካፈል ይገባል የሚል ክርክር ተጀመረ:: ይሁንና ውርሱን ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ የነበረው ማርሻል በጊዜው ሞቶ ስለነበር ሚስቱን መጠየቅ የግድ ሆነ:: የማርሻል ሚስትም በመስማማቷ ሀብቱ ለቀሪዎቹ ልጆች እንደ አዲስ ተካፈለ::»

እንግዲህ ጥያቄው ከሞት በኋላ ሕይወት ባይኖር የእነማርሻል አባት ቻፌን እንዴት ለጀምስ ነገሩን ሁሉ ሊገልጥለት ቻለ? የሚል ይሆናል::

ከዘመናችን የፍልስፍና ምሁራን አንዱ አንቶኒ ፍሊው በጉዳዩ ላይ በሰነዘረው አስተያየት:- «...ጀምስ አባቱ ከመሞቱ በፊት አስቀድሞ ነግሮት የነበረውን ለጥቂት ዓመታት ዘንግቶት ከዕለታት በአንድ ቀን ግን ነገሩን በተኛበት አስታወሰው፤ በህልሙ አባቱ ሲያናግረውም የተመለከተው ከዓመታት በፊት በእውን ሲነግረው የነበረውን ነው::... ለነገሩ የቻፌን ነፍስ በእውነትም ካለች ቦታዋ ገነት ካልሆነም ገሃነም ይሆናል እንጂ ምድር ላይ ምን ትሰራለች?... በጉዳዩ ላይ ለመፍረድ በዳኝነቱ ወንበር ላይ የተቀመጥኩት እኔ ብሆን ኖሮ ቻፌን ራሱ ቀርቦ ነገሩን ካላስረዳ የቀድሞ ኑዛዜው ፀንቷል ብዬ መፍረዴ አይቀርም ነበር» ብሏል::

መቼም ከፍልስፍናው ጎራ ተሰልፎ ለምን እሞታለሁ? ከሞትኩ በኋላስ የምሄድበት አለኝ? ብሎ ያልጠየቀ ፈላስፋ ማግኘት አይቻልም:: ብዙዎቹ ፈላስፎች «የምትሞተው የሰውነትህ ሴል ሕዋስ በዕድሜ ብዛት አልያም በበሽታ ስለሚሞት ነው፤ ሌላ ነገር የለም» ይሉናል:: ሌሎቹ ደግሞ «የምንሞተው ለሕይወት ሲባል እንደሆነስ?» በማለት ይጠይቁና «ሕይወት ሁልጊዜ ወጣትና አዲስ ሆና ለመገኘት ያረጀውን የመለወጫ ጥበብዋ ሞት ብቻ ነው» ይላሉ::

እንግዲህ ሞት አሮጌውን ማስወገጃና አዲሱን የመቀበያ ጥበብ ነው በማለት እንጀምርና ሞትና ከሞት በኋላ አለ የሚባለውን ነገር በመጠኑ እንመርምር::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ሞትን ከዚያም በኋላ ሊኖር የሚችለውን ሕይወት በኒኮላይ ፌዶሮቭ እምነትና ፍልስፍና ማየት ብንጀምርስ:: ታላቁ የራሽያ ፈላስፋ ኒኮላይ ፌዶሮቪች ፌዶሮቭ (1829 - 1903 እ.ኤ.አ) የዘላለማዊነት ወይም የፀረ ሞት ፍልስፍናን (Immortalist/Anti-death Philosophy) የመሠረተ ምሁር ነበር:: ይህ ራሽያ በዘመናት ካፈራቻቸው ፈላስፎች ታላቁን ቦታ የሚሰጠው ፌዶሮቭ በምዕራቡ ዓለም እምብዛም ግምት የሚሰጠው አይሁን እንጂ ከእሱ በላይ በዓለም ታላላቅ ስም ያላቸው እንደ ዶስቶቪስኪ፣ ሌዎ ቶልስቶይ እና አፋንሲ ፌት ዓይነቶቹ ለፌዶሮቭ የነበራቸው ከበሬታና ግምት እጅግ ከፍተኛ እንደነበር በታሪክ ይጠቀሳል:: ወደ ፌዶሮቭ እምነትና ፍልስፍና እንመለስ:-

«በምድር ላይ ስኖር አንድ የተረዳሁት ነገር ቢኖር በሀብታምና በደሀ መካከል ካለው ልዩነት ይልቅ በተማረውና ባልተማረው መካከል ያለው እጅግ የሰፋ መሆኑን ነው» የሚለን ፌዶሮቭ:- «የተማረው ከሥራ ይልቅ በማሰብ ላይ ይበረታል፤ ያልተማረው ብርታት ደግሞ ከማሰብ ይልቅ ሥራ ላይ ነው:: ታዲያ የተማረውን ስለ ገነት ወይም ስለ ዘላለማዊ ሕይወት ብትነግረው 'መጀመሪያ ላስብበት' ይልሀል:: አስቦበት ሲመለስ ደግሞ መልሱ 'ገነት የሚባል ነገር የለም፤ ይልቅ ገነትን እዚሁ ምድር ላይ እንስራው' ነው:: ያልተማረው ለማሰብ ጊዜ ስለሌለው ገነት አለ የሚለው የአንተ ንግግር ለእሱ በቂው ነው፤ በዚያው እምነት ይኖራል፤ በዚያው እምነትም ይሞታል...» ፌዶሮቭ ይሄን ጠይቆ ከሞት በኋላ ስለሚኖረን ሕይወት እንዲህ ይላል:-

«እኔ ለምሳሌ አንድ ሰው ነኝ፤ ማመን የምችለውም አንድ ነገር ነው፤ መሆንም የምችለው አንድ ነገር ነው፤ ገነት የሚገቡት ደግሞ የተመረጡት ናቸው፤ ካልተመረጥኩ የዘላለም እሳት ይጠብቀኛል:: ትልቁ ጥያቄ ደግሞ ለመመረጥ የሚያበቃው መመዘኛ (Criteria) እንደ ሃይማኖቱ የተለያየ ከመሆኑ ላይ ነው:: የአንዱ የገነት መግቢያ ለሌላው የገሃነም ደጅ ነው:: ለአንዱ እግዚአብሔርን መምሰያ ለሌላው የሰይጣን ወንድምነት



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ይሆናል...

«እንደ እኔ እምነት ዘላለማዊ መሆንና እግዚአብሔርን መምሰል ከፈለግን የጋራ ገነት መፍጠሩ የተሻለ ይመስለኛል:: የእሱ ፈጣሪዎች ደግሞ እኛ የተማርነው ነን» ይለናል::

«እንግዲያውስ ስለዘላለማዊነት ንገረን?» በማለት ፌዶሮቭ ተጠየቀ::

«እሱን እንድነግራችሁ መጀመሪያ አስቀድሞ የሞቱት ሲነሱ ማየት አለብኝ» ብሎናል::

«እግዚአብሔርን ስለመምሰልስ...?» ተባለ::

«ሁላችንም 'የምንመስለው ሳይሆን የምንሆነው' እንደ እግዚአብሔር ነው:: ጨካኝም ብትሆን ደግ፤ ቁጡም ብትሆን ታጋሽ፤ የምትገድልም ብትሆን የማትገድል... እሱን ነው የምትሆነው... ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ነውና» ብሏል::

ፌዶሮቭ እግዚአብሔርን ስለመምሰል ባስፈረው ሀተታ ደግሞ «እግዚአብሔር ስጋና ደም የለውም ትላላችሁ:: እንግዲህ አስቀድሞ ሲፈጥራችሁ እሱን አስመስሎ ካልሰራችሁ እሱን መምሰል ለምን ፈለጋችሁ?» በማለት ይጠይቃል::

ስለ ፌዶሮቭ ፍልስፍና በሌላ ምዕራፍ ስለምንመለስበት በዚሁ እናቁምና ወደ ተነሳንበት ርዕስ ተመልሰን የሌሎቹን ፈላስፎች እምነት ደግሞ እንቃኝ:: እ.ኤ.አ በ1937 ዓ.ም. በኦስትሪያ ቪዬና ላይ የተመሠረተው Vienna Circle of Logical Positivists መሪ የነበረው ሞሪትዝ ሽሊክ «ከሞት በኋላ ሌላ ሕይወት አለ» ለሚለው እምነት የራሱን ፍልስፍና እንዲህ አስቀምጦታል:-

«...በእርግጥ ለእኔ የሚፈጥርብኝ ስሜት የተለየ ነው:: ምክንያቱም ከሞት በኋላ ሕይወት ካለ በቀብሬ ስነስርዓት ላይ የእኔ መገኘት አይቀሬ ይሆናልና:: የሚቀፈው ነገር ታዲያ ስጋዬ መሬት ውስጥ ሲገባ ቆሞ ማየቱ ነው:: ለማንኛውም ኑይሄንን ነገር በትዕግስት ጠብቄ ማየቴ አይቀርም» ብሏል::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ከእሱ ቀጥሎ ይሄንን ተመሳሳይ ጉዳይ ያነሳው ጆን ዊዝደም ነበር:: እሱም ሲናገር:- «የራሴ ቀብር ላይ መገኘት ምን ሊመስል እንደሚችል መገመት እችላለሁ:: ወዳጆቼ በጥቁር ሱፍና ከረባት አጊጠው፣ አበቦችን ደርድረው፣ በሬሳ ሳጥን ውስጥ ከአበቦች ስር የሚታይ ፊት (ምናልባት ፊቱን ሳይ እደነግጥ ይሆናል)... » ብሏል::

አንቶኒ ፍሊው የሁለቱን ፍልስፍናዎች ማጠቃለያ ሲሰጠን:- «ከሞት በኋላ ሕይወት ካለህ በራስህ ቀብር ላይ ትገኛለህ... እንግዲህ በቀብርህ ላይ ከተገኘህ ደግሞ አልሞትክም ማለት ነው... ከመሞትህ በፊት አስቀድሞ የሞተውን ጓደኛህን እንደቀበርክ ሁሉ ዛሬም ራስህን እየቀበርክ ነው፣ የሚያሳዝነው ግን በቀብርህ ላይ መገኘትህን ማንም አለማወቁ ነው» ይለናል::

ይህ የገነት መግቢያ መስፈርት (criteria) ግራ ያጋባቸው ፈላስፎች ሌላ የሚሉትም አለ:- «ሂትለር በሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዶችን የፈጀ ነው:: እንደዕድል ሆኖ ከመሞቱ በፊት ለቄስ ሃጢያቱን ቢናዘዝ ኖሮ ገነት መግባቱ አይቀርም ነበር:: የሚያሳዝነው ደግሞ እሱ የገደላቸው አይሁዶች መስፈርቱን ሳያሟሉ በመሞታቸው ገሃነም ይገባሉ:: ከዚህ በኋላ ሂትለር ከእግዚአብሔር ጋር አይሁዶች ደግሞ ከሰይጣን ጋር ዘላለማዊውን ሕይወት ይገፋታል ማለት ነው::»

የሰው ልጅ የሚፈራው ሞቱን ሳይሆን ከሞት በኋላ የሚኖረውን «ሕይወት» ነው የሚሉ ምሁራን ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ ታላቁ ደራሲ ቪክቶር ሁጐ «የሰው ልጅ እንደራሱ ሞት የሚያስጨንቀውና የሚያስፈራው ነገር የለም:: ይህ ፍርሃት ደግሞ ሃይማኖትን ፈጥሯል» ይላል:: የፈረንሣይ ንጉስ የነበረው ናፖሊዮን ቦናፓርትም በአንድ ወቅት ሲናገር:- «ሰዎች ከአሁኑ የምድራዊ ሕይወታቸው ይልቅ ለሁለተኛው ይጓጓሉ፣ እኔም ለዚህ ነው ሕዝቤ ጳጳስ ባይኖረው ኖሮ አንድ ጳጳስ እፈጥርለት ነበር የምለው» በማለት ተሳልቋል::

እዚህ ላይ ዛሬ በፍልስፍና እምነታቸው ከሚያስደነግጡን በባሰ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

መልኩ ድንቅ ፈላስፋዎች በኢየሱስ ዙሪያም እንደነበሩ መመስከር ስለሚቻል አንድ ሁለቱን እንመልከት:-

«እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፣ ወደእኔም እወስዳችኋለሁ:: ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ፤ መንገዱንም ታውቃላችሁ:: ቶማስም:- ጌታ ሆይ ወደምትሄድበት አናውቅም፤ እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው::» (ዮሐ.14:4-5) (ስረዝ የተጨመረ)

ለሦስት ዓመት ከስድስት ወር ከኢየሱስ ጋር አብሮ መከራን የተካፈለው ሰውዬ ከምድራዊ ሕይወት ሌላ አዲስ ሕይወት እንደሚኖር አያውቅም ነበር:: ለዚህም ነው:-«ሌሎቹ ደቀመዛሙርት:- ጌታን አይተነዋል አሉት:: እርሱ ግን:- የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው::» (ዮሐ.20:25) (ስረዝ የተጨመረ)

ይህ ሰው ታዲያ ከሶፊስቶች በምን ይለያል? የሶፊስቶች እምነት መገለጫ:- «አንድ ነገር እውነት የሚሆነው ለስሜት ህዋሳትህ መልእክት ከሰጠህ ብቻ ነው» ይላሉ:: ይኸው የፍልስፍና እምነት በቶማስ ልብ ውስጥ ነፍስ ዘርቶ ይታያል::

የሌላው ደቀመዝሙር የፊልጶስ ጥያቄ ደግሞ ኢየሱስን ብቻ ሳይሆን ፈላስፎቹንም ያስገረመ ነበር:-

«እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር:: ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁትማል አለው::

ፊልጶስ:- ጌታ ሆይ፣ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው::» (ዮሐ.14:7-8) (ስረዝ የተጨመረ)

«ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ፈላስፋ ዛሬ የሚገኘው ገነት ይሆን?» በማለት የዘመናችን ፈላስፎች ይጠይቃሉ::

የፍልስፍናው ዓለም ምሁራን ሌላም ጥያቄ አላቸው:- «ለመሆኑ ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብለን ከተቀበልን ወዳጃችን ሲሞት የምናለቅሰው



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ለምን ይሆን? ለጥቂት ዓመታት ተለያይተን ስለምንኖር? ወይስ ከሞት በኋላ ሕይወት ለመኖሩ እርግጠኛ ባለመሆናችን? አልያም ደግሞ የወዳጃችንን መሄጃ (ገነት ወይም ገሃነም) ስለማናውቅ፤ የእኛንም እርግጠኞች ስላልሆንን ከሆነስ?»

እዚህ ላይ የአሪስቶተልን ፍልስፍና ለዚህ ሃሳብ ሳያነሱ ማለፍ የተገባ አይሆንም:: የአሪስቶትል የፍልስፍና ሃሳብ ካታርሲስ (Catharsis) ስሜትን ማጥለል ይባላል:: ስለካታርሲስ ቲዎሪ በአጭሩ ላስቀምጥ:-

«አንድ ሰው የቅርብ የሆነ ዘመዱ ወይም ወዳጁ ሲሞት የሚያለቅሰው ለሟቹ ሰው በማዘን ሳይሆን በማዘኑና በማልቀሱ ግን ራሱ የሚያገኘው እፎይታ (relief) ስለአለ ነው:: በለቅሶውም የራሱ ሃጢያትና ክፋት ካሳ እንደሚያገኝለት ያምናል::» በሌላ አገላለፅ አሪስቶትል ይህንኑ ሲያስረዳን:- «አንድ ንፁህ ሰው በሞት ሲቀጣ ብትመለከትና ብታለቅስ፤ ንፁሁ ሰው ያለጥፋቱ በመሞቱ ሳይሆን ያለቀስከው ራስህን በሰውዬው ቦታ በማስቀመጥ 'እኔ በዚህ ሰው ቦታ ብሆንስ?' በሚል ስሜት ስለምትንገላታ ነው:: እንግዲህ በሰው ሞት ውስጥ የራስህን ሞት ማየት ካታርሲስ ይባላል» ይለናል::

የእሱ አስተማሪ የነበረው ፕሌቶ ደግሞ ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት ሲናገር:- «የእኔ ዘላለማዊነት በገነት ሳይሆን በሰዎች ልብ ውስጥ ነው:: ምክንያቱም አስተማሪው በምድራዊ ሕይወቱ ከሚያፈራቸው ይልቅ ትቶት በሚያልፈው ሥራው የሚፈጥራቸው እጅግ ይበዛሉና» ብሏል::

በዚህ ዓይነት ከቀጠልን ስለዘላለማዊነት (eternity) በፈላስፎቹ የተሰነዘሩትን አስተያየቶችና ትንታኔዎች ለማየት በራሱ ዘላለም ሳያስፈልገው ይቀራል?



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# ገሃነም የገባኸው በእግዚአብሔር ቁጣ ሳይሆን በራስህ ምርጫ ነው

የዚህን ምዕራፍ የፍልስፍና ወግ በዚህች ቀልድ ብንጀምርስ፡-

አንድ የፍልስፍና ፕሮፌሰር ተማሪዎቹን የመጨረሻውን ዓመት ፈተና ለመፈተን ወደ ክፍሉ ገባ፡፡ በክፍሉ ውስጥ ገብቶም መጀመሪያ ያደረገው ነገር ቢኖር ወንበሩን ጠረጴዛው ላይ መጫን ነበር፡፡ «ለአንድ ዓመት ያስተማርኳችሁን የፍልስፍና ትምህርት መሠረት በማድረግ የዚህን ወንበር አለመኖር አረጋግጡልኝ» በማለት ፈተናውን ለተማሪዎቹ አቀረበ፡፡

ብዙዎች መፃፍና ብሎም የፃፉትን ማጥፋት ለሰዓታት ተያያዙት፡፡ አንዳንዶቹ ተማሪዎች የወንበሩን አለመኖር ለማሳየት የልብወለድ ድርሰት የሚያህል ፅሁፍ ፃፉ፡፡ ከመሃከላቸው አንዱ ተማሪ ግን መልሱን ለመፃፍ የፈጀበት ጊዜ ሦስት ሴኮንድ ነበር፡፡

በሳምንቱ ፕሮፌሰሩ የፈተናውን ውጤት ይዞ መጣ፡፡ ከዚያ ተማሪ በስተቀር ሁሉም ወድቀዋል፡፡ የተማሪው መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡- «የትኛው ወንበር?»

* * *



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ብዙውን ጊዜ ፍልስፍና በባዶ ነገር የተሞላ ቅዠት አድርገው የሚመለከቱት በርካታ ናቸው። በተለይም ደግሞ ፍልስፍና ግላዊ እምነትን የመንካትና ብሎም ጥርጣሬ ውስጥ የመጣል ባህርይው እስከመጠላት አድርሶታል። ለመሆኑ እምነትን መሠረት ያደረገ ፍልስፍናስ የለም? ለዚህ መንደርደሪያ ይሆነን ዘንድ ቀጥሎ የምናየው ከፍልስፍናው ጉራ ስለሚመደቡት ነገር ግን ፍልስፍናቸውን በእምነታቸው ላይ ስለመሠረቱት የሚስቲሲዝም አራማጆች ይሆናል። በምዕራባውያን ዘንድ ስለ ሚስቲሲዝም ስናነሳ በተለይ Perennial Philosophy የሚያነሳው ሃሳብ እምነቱን በሰፊው የሚያብራራና የሚያራምድ ሆኖ ተገኝቷል። የዚህ የPerennial Philosophy መስራች የሆነው Aldous Huxley *"The Cloud of Unknowing"* በሚለውና በተለይ በእንግሊዞች ዘንድ በሚታወቀው መንፈሳዊ ጽሑፉ የሚስቲሲዝምን መንፈሳዊ ሚስጥራት ሊያሳየን የሞከረ ሰው ነው። እንደ ሀክስሌይ ሐሳብ ዛሬ የምናያቸው መንፈሳዊ ልምምዶችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዛት በእርግጥ ለእኛ ያገለግላሉን? ተብሎ ሲጠየቅ መልሱ «አትጠራጠሩ» የሚል ነው። ሀክስሌይ ሃሳብ ልገፋበት ስለማልፈልግ ስለሚስቲሲዝም አራማጆችና በተለይም በዚህ የእምነት ፍልስፍና ትልቅ ቦታ ስለሚሰጠው St. John of the Cross ማንሳት እወዳለሁ።

የዘመኑ ፈላስፎች «አለአግባብ ትርጉም ተሰጥቶት የባከነ ቃል ቢኖር ሚስቲሲዝም ነው» ቢሉም ከተራና የተለመደው ትርጉሙ እንጀምርና ይህን ሚስቲሲዝም ጠለቅ ብለን ለማየት እንሞክር።

*«በተመስጦ በሆነና በፍቅር ነፍስህ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታና ብሎም ጥልቅ በሆነ አንድነት ውስጥ ስትገባ ይህ እምነት ሚስቲሲዝም ይባላል።»*

እንግዲህ ይህ አንድነት ነፍስህን ከፍ ወደአለ ደረጃ በማድረስ ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት ብቻ አታቆምም፤ ነገር ግን ራሷም ወደ እግዚአብሔርነት ትለወጣለች፤ «በድርጊቷም እንደ እግዚአብሔር



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ትሆናለች» እንደ ማለት ነው ይላሉ የሚስቲሲዝም አራማጆች:: ስለዚህም «ተፈጥሮ በራሷ እውነታ (Reality) አይደለችም፣ የተፈጥሮን እውነታ ለማየት ከፈለግህ ሚስቲሲዚም የተሻለው መንገድ ነው» ይሉናል ::

ከሚስቲሲዚም አራማጆች አንዱና ታላቅ ቦታም የሚሰጠው ቅዱስ ዮሐንስ (St. John of the Cross 1542-1591) ነው:: የዚህ ሰው ታላቅ ሥራ ተደርጎ የሚወሰድለት «The Ascent of Mount Carmel» የሚለው ዕሁፉ ነው:: Ascent የሚለው ቃል ማሳረግ እንደማለት ነው:: Mount Carmel ደግሞ የቀርሜሉስ ተራራ በሚል ስያሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናውቀውና ነብዩ ኤልያስ የሐሰተኛ ነቢያት ጣኦታትን ለማፈራረስ እውነተኛውን እግዚአብሔርን ለመጥራት መስዋዕቱን ያሳረገበት ቦታ ነበር:: ቅዱስ ዮሐንስ በተለይ በዚህ መጽሐፉ የዚህን ቦታ ክስተት ያስቀመጠው በግጥም ሲሆን በድርጊቱ ውስጥ እንዴት ነፍስ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሆና በራሷ እንደ እግዚአብሔር መስራት እንደምትችል ሊያሳየን ሞክሯል::

*«ኤልያስም:- እስራኤልን የምትገለባብጡ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ትታችሁ በአሊምን የተከተላችሁ አንተና የአባትህ ቤት ናችሁ እንጂ እኔ አይደለሁም... እስከመቼ ድረስ በሁለት ሃሳብ ታንከሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፣ በአል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ... መስዋዕተ ሰርክ በሚቀርብበት ጊዜ ነብዩ ኤልያስ ቀርቦ:- አቤቱ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፣ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንህ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንሁ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ... የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፣ የሚቃጠለውን መስዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም በላች፣ በጉድጓዱ ውስጥ ያለውን ውሃም ላሰች...» (1ኛ ነገሥ. 18:20-40)* (ሰረዝ የተጨመረ)

ቅዱስ ዮሐንስ በዚህ ታሪክ ሊያሳየን የሚሞክረው የኤልያስ ነፍስ በራሷ እንደ እግዚአብሔር መሆኗን ነው:: «ነፍሱ ከእግዚአብሔር ብርሃን



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ጋር ተዋህዳ በጨለማው ምድር ላይ የኃይል ብርሃንን ፈንጥቃለች። ይህ ማለት ግን የኤልያስ ነፍስ እግዚአብሔርን ሆናለች ማለት አይደለም። ምክንያቱም በፈጣሪና በተፈጣሪ መካከል ያለው ልዩነት ይገባናልና። ነገር ግን ነፍስህ በፍቅርና በፍፁም ፍቃደኝነት ከመለኮታዊው ፍቃድና ፍቅር ጋር ስትዋሀድ ወይም ለመለኮታዊ ኃይልና ፍቅር ማለፊያ ስትሆን ያንጊዜ በነፍስህ የእግዚአብሔርን ስራ ትገልጣለህ፤ ወይም ነፍስህ እንደ እግዚአብሔር ትሆናለች» ይለናል ቅዱስ ዮሐንስ።

ይህንኑ በምሳሌ ሲያብራራልን፡- «በቤትህ መስተዋት ትይዩ ፀሐይ ወጥታለች እንበል... የቤትህ መስተዋት ደግሞ ያደፈና የቆሸሸ ነው። እንዲህ ከሆነ የፀሐይዋ ጨረር ነፀብራቅም የሚያስጠላ ወይም እስከነአካቴው የማይታይ ይሆናል። ምክንያቱም የፀሐይዋ ጨረር በቆሻሻው ይዋጣልና። ነገር ግን መስተዋቱ ከቆሻሻ የፀዳና ንፁህ ከሆነ የፀሐይዋን ጨረር እንደአመጣጡ ያንፀባርቀዋል፤ ያሳልፈዋልም። ከቤት ውጭ ነፀብራቁ፤ ከቤት ውስጥ ደግሞ ብርሃኑ በሚገባ ይታያል። ነፍስህም እንደዚህ መስተዋት ነች። እግዚአብሔርን የመሆን መለኮታዊ ብርሃን ዕለት ዕለት በነፍስህ መስተዋት ላይ ይወርዳል፤ ነገር ግን እንደ ነፍስህ ሁኔታ ይዋጣል ወይም ይንፀባረቃል...

«እንግዲህ ነፍስህ ፀድታ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ፀሐይ ስትሞቅ ራሷን ወደ እግዚአብሔርነት ታሸጋግራለች፤ እንደ እግዚአብሔርም ትሆናለች። ምክንያቱም የእሱ ልዕለ ኃያል ጥበብ ይገናኛታልና። አንድ ነገር ልብ በል! መስኮቱ ተፈጥሮውን ሳይቀይር የፀሐይዋን ጨረር በማንፀባረቅ ፀሐይን እንደመሰለ እንዲሁም ነፍስህ የእግዚአብሔርን ፀሐይ በማንፀባረቅ እንደ እግዚአብሔር ትሆናለች። ይህ የሚሆነው ግን ነፍስህ ከማንኛውም ምድራዊ ነገር ተላቅቃ ብቻዋን ለእግዚአብሔር በፍቅርና በንፅህና ስትቀርብ ነው...» ይለናል።

«ይህ የነፍስ ንፅህና ደግሞ ከስጋ እጅግ የላቀ ነው» የሚለን ቅዱስ ዮሐንስ፡-«የእስራኤል ሕዝብ ከባርነት ወጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ሲጓዝ በምድረ በዳ ያንጎራጉር ነበር:: መናው ስለቾን! አስጠላን! አሉ (መና የመላዕክት እንጀራ መሆኑን ልብ ይበሉ):: ለዚህ ምክንያታቸው በግብፅ ምድር ይበሉት የነበረው የሥጋና የጣፋጭ ምግብ ትዝታ ነው:: እንደዚሁ ነፍስህ ታላቁን እግዚአብሔርዊነት ልትቀዳጅ የምትችለው ከምድራዊውና ከተለመደው ተራ ነገር ስትነፃ ብቻ ነው...

«በምድር ላይ የለመድከው ብርሃን ለአንተ ታላቅ ከሆነ ነፍስህ ከዚያ በላይ ብርሃን ለማሰብ ያዳግታታል:: ነገር ግን ነፍስህን እጅግ የላቀ ብርሃን እንዳለ ብታሳምናትና ብታለማምዳት ያ ብርሃን በአንተ ውስጥ ማለፍ ይጀምራል... ብርሃኑ በውስጥህ ሲያልፍ ደግሞ የምታንፀባርቀው ያንኑ ብርሃን ነው፤ እንደ እግዚአብሔር ሆንኩ ማለትም ይኸው ነው::» በማለት ቅዱስ ዮሐንስ የሚስቲሲዚምን ምንነት ሲያሳየን ሞክሯል::

የእምነቱ አራማጅ ፈላስፎች በጥቅሉ የሚነግሩን ደግሞ «በመሆን ውቅያኖስ ውስጥ ገብተህ መዋኘት ስትችል ፍጡር መሆንህ ያበቃና የፈጣሪ አንድ አካል መሆንህን ትረዳለህ፤ በዚያውም የሃይማኖት ምንነት ይገባሃል» ይላሉ::

የሚከተሉትን ድንቅ የሚስቲሲዚም አራማጆችን አባባል መመልከቱ ይበልጥ ይጠቅማል እላለሁ:-

* አምላኬ ሆይ! በእኔው እንባ ለራሴ እያለቀስኩ ከእግዚአብሔር ወደ እግዚአብሔርነት ሄድኩ::

(Byazid of Bitsum)

* እኔነቴ እግዚአብሔር ነው:: ከእኔነቴም አምላክ በቀር ሌላ አላውቅም::

(St. Catherine of Genoa)

* ውስጣዊ ብርሃን ከምስጋናም ከነቀፋም በላይ ነው:: ይህ ዓለም ዳርቻ እንደሌለው ሁሉ ውስጣዊ ብርሃንም በሰላምና በሙላት በውስጤ አለ... ብርሃንህን የምታጣው ስታሳድደው ብቻ ነው:: ልትቆጣጠረው እንደማትችል ሁሉ ልታስወግደው እንደማትችል ግን ተረዳ::

(Yung-Chia-Ta-Shih)



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

* እንደ መንፈስ ስትሆን ከጊዜያዊነት ወደ ዘላለማዊነት ትሸጋገራለህ:: እንደ ስጋ ስትሆን ደግሞ ከዘላለማዊነት ወደ ጊዜያዊነት ትለወጣለህ:: እውነትን ማግኘት ማለት በመለኮታዊ ብርሃን እግዚአብሔርን ማግኘት ነው... ይህም ብርሃንን በብርሃን እንደመፈለግ ነው::

(Meister Eckhart)

* ገሃነም የገባኸው በእግዚአብሔር ቁጣ ሳይሆን በራስህ ምርጫ ነው::

(William Law)

* ነፍስህ የተያዘችበት ምድራዊ ነገር የቱንም ያህል ጥሩ ቢሆን ነፃነትን ያመጣልኛል ብለህ አታስብ::

(St. John of the Cross)

ሚስቲሲዚም ለሌሎቹ ፈላስፎችስ ምንድነው? ታላቁ የዘመናችን ፈላስፋ ዊል ዱራንት The Pleasure of Philosophy በሚለው መጽሐፉ:- «ሚስቲሲዚም ሃይማኖት አይደለም:: ነገር ግን ሞራላዊ ሕግ ነው:: የሞራል ሕግ ደግሞ የሚሰራው ለተማረው ክፍል ብቻ ነው፤ የተማረው ደግሞ የሞራል ሕግ አይፈልግም፤ ስለዚህም ሚስቲሲዚም 'ሙቀቱ የማይሰማህ በሩቁ የተቀጣጠለ እሳት ሆኖ ቀርቷል'» በማለት አስፍሯል::

ሌላው የዘመናችን ፈላስፋ ስለሚስቲሲዚም በተናገረው እናብቃ:-

«ለእኔ ሚሲቲሲዚም 'የሕንድን ፍልስፍና ስትወድ ከሩዝ በቀር ሌላ ምግብ የለም' እንደማለት ነው:: አንድ ቀን በባቡር በመጓዝ ላይ ሳለሁ በሰማያዊው ሰማይ ላይ ደመናው በመስመር በመስመር ተዘርግቶ የተፈጥሮን ውበት አሳየኝ:: በዚያን ወቅት የተፈጥሮ ውበት ስቦኝ ራሴን በሃሳቤ በደመናው ላይ እንዳንሳፈፍኩት ትዝ ይለኛል:: እንግዲህ እኔ እግዚአብሔር ሆኛለሁ ማለት ነው?»



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# «የሚገርመኝ የጓደኛዬ ሞት ሳይሆን የእኔ መኖር ነው»

እጅግ ታላላቅ የዘመናችን ጠቢባን፣ ፈላስፎች፣ ሳይንቲስቶች፣ የሃገ
መሪዎች... ስለዚህ ሰው የሚናገሩት አንድና ተመሳሳይ ነገር ነው
ጥቂቱን እንመልከት:-

«ምድራችን ካፈራቻቸው ጭንቅላቶች ወደር የማይገኝለት::»

«እንዲህ ዓይነቱ አዕምሮ በመቶ ዓመት አንዴ ከተገኘ ለዚህ
ምድር በቂ ነው::»

«አዋቂ ሳይሆን ራሱ እውቀት ነው::»

«የሰው ልጅ ሥልጣኔን የምመዝነው በእሱ ግኝት ነው::»

«የሰው ልጅ ሕይወት በእሱ እውቀት ሥር ወድቃለች::»

ይኸ ሰው ደግሞ ስለራሱ እንዲህ አለ:- «ዝናዬ በሰፊው እየና
በመጣ ቁጥር የማልረባ እየሆንኩ መጣሁ፣ በእርግጥ ይኸ በሰዎ
ዘንድ የተለመደ ነው...»

ተማሪዎቹንም መከረ:- «በውዳሴ እንዳትደክሙ በሥራ አምልኩ
ሌላ አማራጭ የለውምና:: ወጣት ሆኜ በጣም የምደሰትበት ነገር ቢኖር
ማንም ስለእኔ ጉዳይ ሳይል በአንዲት ቦታ ተቀምጨ የራሴን ሥራ
ምርምር ማድረግ ነበር:: ያ ሥራና ምርምር አሁን ምን እንዳተረፈል
ተመልከቱ::»

ታላቁ ሳይንቲስት አልበርት አይንስታይን ማርች 14/1879 ኡልም በምትባል አንዲት አነስተኛ የጀርመን ግዛት ተወለደ:: በ1880 እ.ኤ.አ. ከወላጆቹ ጋር ወደሙኒክ ተጉዞ የልጅነት ሕይወቱን በዚያ ጀመረ:: በ1894 እ.ኤ.አ. ቤተሰቡ ወደጣልያን ሲጓዝ አይንስታይን በሙኒክ ትምህርቱን ለመቀጠል ቢቀርም በዚያው ዓመት መጨረሻ ግን ትምህርቱን በማቋረጥ ወደጣልያን ተጉዞ ከቤተሰቡ ጋር ተቀላቀለ:: በጣልያን የፖሊ ቴክኒክ ት/ቤት ገብቶ ለመማር የመግቢያ ፈተና ወስዶም በመውደቁ አራው ካቶሊክ ት/ቤት ገብቶ ለመማር ተገደደ::

«የእኔ ሥራ በዚህ ዓለም ምስጢራት መደነቅ ነው» የሚለው አይንስታይን ከወጣትነት ጊዜው ጀምሮ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ እንደነበረው ከታሪኩ እንረዳለን:: አንዳንድ ወዳጆቹ ስለሕይወት በነበረው ፍልስፍና በመደነቅ የፈላስፋነት ካባም ሊደርቡለት ከጅለው ነበር:: ለፍልስፍና ትልቅ ግምትና አክብሮት የነበረው አይንስታይን፡- «ፍልስፍናን ስታያት ማር በተለወሰ የዕውቀት ብዕር የተፃፈች ትመስላለች:: ለዚህም ነው ልታነባት ወደሀ ስትጀምራት ግልፅና ጣፋጭ ትመስልና ወደውስጧ ጠልቀህ ስትገባ ግን የአንተን የአላዋቂነት እሬት ታስልስሃለች...

«ፍልስፍና በመጪው ዘመን የሰው ልጅ የሚመራባት ትሆናለች ብዬ አልገምትም፤ ለጥቂቶችና የላቀ አዕምሮ ላላቸው ግን ማረፊያ ቤተ መቅደስ እንደምትሆን አምናለሁ» ብሏል::

የአይንስታይንን የእምነት ፍልስፍና ላጤነ ግን ወዳጆቹ የፈላስፋነት ካባ ሊደርቡለት መከጀላቸው እምብዛም አይደንቀውም::

እ.ኤ.አ. በ1915 በእንግሊዞች ላይ ደርሶ ስለነበረው እልቂት የሚገልፅ አንድ ደብዳቤ ከስዊዘርላንዳዊ ጓደኛው ኤድጋር ሜየር ደረሰው:: ሜየር በደብዳቤው መጨረሻ፡- «እግዚአብሔር እንግሊዞችን በመቅጣቱ ደስ ሊልህ ይገባል» አለው:: አይንስታይን ለጓደኛው በፃፈው የመልስ ደብዳቤ፡- «ለምን ይህን ደብዳቤ እንደፃፍክልኝ አልገባኝም:: እኔ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከእንግሊዞች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለኝ በሚገባ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ታውቃለህ:: የሰውን ዘር በምድር ላይ እየቀጣ ያለው እግዚአብሔር ከሆነ ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባ ነበር፤ እግዚአብሔር የሚባል ነገር አለመኖሩ ግን በራሱ ይቅር አስብሎታል» በማለት መልሶለታል::

«እስከዛሬ በምድር ላይ ስኖር ለአንድም ቀን እለ ብዬ አስቤው የማላውቀው ነገር እግዚአብሔር ነው» የሚለው አይንስታይን አንድ ወቅት በተማሪዎቹ:- «ራስህን ከእግዚአብሔር በላይ ታየዋለህ?» ተብሎ ተጠይቆ ነበር:: እሱም ሲመልስ:- «አዎን! ከኢየሱስ በላይ ማድረግ ከቻልኩ እንዴት ከእግዚአብሔር ላንስ እችላለሁ:: እኔ ከማደርገው በላይ ታደርጋላችሁ አላለም እንዴ?» በማለት መልሷል::

የቅርብ ጓደኛው አይሁዳዊው ሄይል ፍሬድማን:- «የአይሁድ ዘር ሆነህ በእግዚአብሔር አለማመንህ ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስ ያለማንበብህ ውጤት ይሆናል?» በማለት ለፃፈለት ደብዳቤ ደግሞ በላከለት መልስ:- «መጽሐፍ ቅዱስ ያነበብኩት ኮፒውን ነው:: በሙሴ የተፃፈው እሪጅናሉ ካለህ እባክህ ላክልኝ... በእግዚአብሔር መኖር የማላምን ኃይማኖተኛ መሆኔን ግን አሁንም የረሳኸው አይመስለኝም» ብሎታል::

አይንስታይን ሲበዛ ብቸኝነቱን የሚወድ ሰው ነበር:: «የሰዎች ወዳጅነት ጊዜያዊ እንደሆነ በሚገባ ተረድቻለሁ፤ ስለዚህም በሙቀቱ ላለመቃጠል፣ በቅዝቃዜውም ላለመንቀጥቀጥ ርቄ መኖርን መርጫለሁ:: ያን ጊዜ የሙቀት መጠኑ መካከለኛ ይሆናል» ይላል:: ፍቅረኛው ከነበረችው ግራጫዊቷ ሚሌቭ ጋር በትዳር ለ17 ዓመታት አብረው ኖረዋል:: «በእነዚህ ዓመታት» አይንስታይን እንደሚናገረን «ብዙ ነገር ለመረዳት ስችል ሚሌቭ ግን ምስጢር እንደሆነችብኝ ቀርታለች» ብሏል:: ሚሌቭ የሳንባ በሽታ ፊቷ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ካደረሰባት በኋላ መራርነቷ ከፍተኛ እየሆነ እንደመጣ የሚናገረን አይንስታይን ከዓመታት የትዳር ዘመን በኋላ ቢፋቱም ከልጆቹ ጋር የነበረውን ግንኙነት ጨምሮ እንደጉዳችበትና ይህም ከሰው ርቆ ለመኖሩ የራሱን ድርሻ እንዳበረከተ ይናገራል::

በጀርመን ወታደሮች ባህርይና ድርጊት እጅጉን ይበሳጭ የነበረ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

አይንስታይን በጣሊያን ኑሮውን ሲመሰርት የጀርመን ዜግነቱን ሰርዞ የስዊስ ዜግነት እንዲሰጠው ጠየቀ፤ ጥያቄውም ተቀባይነት አገኘ። ይህንኑ አስመልክቶ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ:- «ሰው በሕግ ፊት የእኩልነት መብቱና ነፃነቱ የማይጠበቅበትና የወደደውን ማስተማር የማይችልበት ሃገር ዜጋ ለመሆን ስለማልፈልግ ብቻ ይህን ወሰኛለሁ» በማለት ተናግሯል።

የአቶሚክ ኢነርጂን ቀመር በማግኘት የታላቅ ዕውቀት ባለቤትነቱን ካረጋገጠ በኋላ በዲሴምበር 11/1945 የኖቤል ሽልማት ተቀብሎ ንግግር እንዲያደርግ ተጋበዘ። ንግግሩ አጭር ነበር:- «ጦርነቱን አሸንፈናል፤ ሰላምን ግን አላሸነፍንም (We won the war; but not the peace)»። የአቶሚክ ኢነርጂ ቀመር በመጠቀም የአውቶሚክ ቦምብ ከተሠራ በኋላ «የኒውዮርክ ታይምስ» ጋዜጣ አዘጋጅ ወደ አይንስታይን መኖሪያ በማቅናት በእሱ ግኝት ስለተሰራው አውዳሚ መሣሪያ የተሰማውን ጠየቀው:- «እኔ የማውቀው አንድም የአውቶሚክ ቦምብ አለመስራቴን ነው፤ ሰዎች መስራታቸውን ግን ሰምቻለሁ» አለው። ይህን ማለቱ የእሱ ግኝት ዓላማ ለሰው ልጅ ልማት እንጂ ጥፋት እንዳልነበር፤ ነገር ግን ሰዎች ግኝቱን በመጠቀም የጥፋት መሣሪያ መስራታቸውን ለመግለፅ ነው።

ለጋዜጠኛው በማከልም እንዲህ አለው:- «ልብ በል! እኔ አውቶሚክ ኢነርጂን ቀድሜ ባላገኘው ኖሮ ጀርመኖች ማግኘታቸው አይቀርም ነበር። በዚህም ግኝታቸው የሰው ዘር ቁንጮ እኛ ነን ለሚሉት እንደማረጋገጫ ይጠቀሙበታል። ምናልባት የእኔ ስህተት ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት የአውቶሚክ ቦንብ እንዲሰራ ሲጠይቀኝ መፈረሜ ነበር፤ ለእሱም ቢሆን ይቅርታ አይነፈገኝም። የጊዜ ጉዳይ እንጂ ጀርመኖች እሱንም መስራታቸው አይቀርም ነበር» ብሏል። ጋዜጠኛው በማስከተል አንድ ጥያቄ አቀረበለት:- «ታዲያ አውቶሚክ ቦንብን የሰሩት እንዴት መቆጣጠር ያቅታቸዋል?» አይንስታይን ለጥያቄው ሲመልስ «ይህ የሚያሳየው ከፊዚክስ ይልቅ ፖለቲካ ከባድ መሆኑን ነው» አለው።



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ስለዓለም ሰላም ተጠይቆም በሰጠው መልስ:- «ሦስተኛው የዓለም ጦርነ በምን እንደሚካሄድ ባላውቅም አራተኛው ግን በድንጋይና በዱላ እንደሚሆን አውቃለሁ» በማለት የሰው ልጅ ስልጣኔ መጥፊያ የመቃረቡን ስጋት ገልፆ «ለዚህች ዓለም ሰላም ማምጣት ከተፈለገ ግን የጋንዲን ሃሳብ ብቻ ስራ ላይ ማዋል በቂ ነው» ብሏል::

ሳይንሳዊ ግኝቱን አስመልክቶ የፈረንሣይ የፈላስፎች ማህበር በኤፕሪል 6/1922 ባደረገለት ግብዣ ላይ ተገኝቶ:- «የእኔ ቲዎሪ ስኬታማ ከሆነ ጀርመኖች የጀርመን ዜጋ፤ ፈረንሣውያን ደግሞ የዓለም ዜጋ ይሉኛል:: የእኔ ቲዎሪ ደግሞ ሀሰተኛ ከሆነ ፈረንሣዮች ጀርመናዊ፤ ጀርመኖች ደግሞ አይሁድ ይሉኛል» በማለት ተናግሯል::

«ስለነገ ለአንድ ቀን ተጨንቄ አላውቅም፤ ምክንያቱም በፍጥነት እንደሚመጣ አውቃለሁና» የሚለን አይንስታይን የእርጅና ዘመኑን ፕሪንስተን በምትባለው የአሜሪካ ግዛት ለማሳለፍ በመወሰን በግዛቷ ኑሮውን መስርቶ ነበር:: በዚያን ወቅት አንዲት ወጣት የአይንስታይንን በሕይወት መኖር ሰምታ በመደነቅ «እስከዛሬ በሕይወት አለህ?» በማለት መገረሟን የሚገልፅ ደብዳቤ በኦገስት 25/1946 ላከችለት:: እሱም «እስከዛሬ ከህያዋን ጋር አብሬ በመቆየቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤ ለነገሩ ለዚህም መፍትሄ አለው» የሚል መልስ ልኮላታል::

በዚሁ ወቅት የቅርብ ጓደኛው የነበረው ማይክል ባስ አረፈና በእሱ የቀብር ስነስርዓት ላይ ተገኝቶ ሲተክዝ የተመለከቱት ጋዜጠኞች ምን እንደተሰማው ሲጠይቁት በሰጠው መልስ:- «የሚገርመኝ የጓደኛዬ መሞት ሳይሆን የእኔ እስከዛሬ መኖር ነው» አላቸው:: ሌላው ጋዜጠኛ «ለመሆኑ ስትሞት እዚሁ ነው መቀበር የምትፈልገው?» በማለት ጠየቀው:: «የእኔ ፍላጐት ሬሳዬ እንዲቃጠል ነው:: ይህን ያህል ሕዝብ በቁሜ ካመለከኝ ይበቃኛል፤ ከሞትኩ በኋላ ደግሞ አጥንቴን እንዲያመልክ አልፈልግም» በማለት መልሶለታል::

አይንስታይን መደነቅም ሆነ መወደስ ፈጽሞ አይወድም::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

አዘውትሮም፦ «እኔን የሚያስቀኝ አዋቂ ነህ የሚለኝ ሰው ብቻ ነው» በማለት ይናገር እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን:: እሱ መደነቅ ባይወድም የሚያደንቃቸው ብዙ ሰዎች እንዳሉ ግን አልሸሸገም:: የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለነበረው ሩዝቬልት ያለውን ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት ሲገልፅ፦ «በሩዝቬልት ፕሬዚዳንት መሆን ከእኔ በላይ ማንም ሊያዝን አይችልም:: ምክንያቱም በየዕለቱ ላገኘው ባለመቻሌ ነው» ብሏል:: በተመሳሳይ የእስራኤል ፕሬዚዳንት ስለነበረው ዌይዝማንም ሲናገር፦ «በተመረጠ ሕዝብ መሃል የተመረጠ ሰው» ብሎታል::

ከከንፈሩ ፒፓ የማይለየው አይንስታይን የ«ኒውዮርክ ታይምስ» ጋዜጣ አዘጋጅ የእርጅና ዘመኑን የሚያሳልፍባትን የፕሪንስተንን ከተማ እንዴት እንዳገኛት ላቀረበለት ጥያቄ በሰጠው መልስ «እንዳልተጨሰ አዲስ ፒፓ!» በማለት ለከተማዋ ያለውን ፍቅር ገልጿል::

«ከሁለት ጦርነት፣ ከሁለት ሚስትና ከሂትለር ተርፌአለሁ» የሚለው አይንስታይን በመጨረሻ ዘመኑ ስለጋብቻ የነበረው አመለካከት በከፍተኛ ጥላቻ የተሞላ ነበር:: አብዛኛውን ጊዜውንም የሚያሳልፈው በቤተ መጽሐፍት ውስጥ አልያም ጀልባ ሲቀዝፍ በመዋል ነበር::

አይንስታይን በስተመጨረሻ ያገኘውን የንፅፅር ሕግ (Theory of Relativity) ብዙዎች በቀላሉ ሊረዱት ባለመቻላቸው ለማስረዳት ይቸገር ነበር:: አንድ ቀን ይህንኑ ጥያቄ ላነሳበት ተማሪው በቀላል ምሳሌ እንዲህ በማለት አስረዳው፦ «ከቆንጆ ሴት ጋር በሚያምር አትክልት ቦታ ለአንድ ሰዓት ተቀመጥ፤ አንዱ ሰዓት እንደ አንድ ደቂቃ ይሆንብሀል:: በጋለ ምድጃ ላይ ደግሞ ሱሪህን አውልቀህ ለአንድ ደቂቃ ተቀመጥ፤ አንዱ ደቂቃ እንደ አንድ ሰዓት ይሆንብሀል:: የንፅፅር ሕግም ይኸው ነው»::

አልበርት አይንስታይን ኤፕሪል 16/1955 ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: የቀብር ሥነ ሥርዓቱም የመጨረሻ ዜግነቱን በተቀበለባት አሜሪካ፣ ፕሪንስተን ግዛት ተፈፀመ::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# «ተናግረህ ማሳመን ካልቻልክ ባትናገር ይሻላል»

አይሁድ «ራሱን ንጉስ ብሏል» በማለት ኢየሱስ ላይ ክስ መስርተው ሊያስገድሉት ወደ አገረ ገገርው ግቢ ሄዱ:: በዚያም እንደደረሱ «ይኸ ክፉ ሰው ነው፤ ራሱን የአይሁድ ንጉስ ብሏል» በማለት ለአገረ ገገርው ጲላጦስ አመለከቱ:: ጲላጦስም ኢየሱስ ላይ የተመሰረተውን ክስ ከሰማ በኋላ... «እውን አንተ ንጉስ ነህ?» በማለት ኢየሱስን ጠየቀው:: «አንተ አልህ» በማለት ኢየሱስ በትህትና መለሰ:: ተፅፎ ባናነበውም ጲላጦስ «ታዲያ ንጉስ ካልሆንክ እዚህ ምን ትሰራለህ?» ያለው ይመስለኛል:: «ለእውነት ልመሰክር ስለተወለድኩ...» አለ ኢየሱስ:: ጲላጦስም ለኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ለዘመናት የፈላስፎች ፈተና የሆነችውን ጥያቄ ወረወረ:- «እውነት ምንድር ነው?»

ታላቁ ፈላስፋ ኒች:- «መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር ዳር አነበብኩት፤ በዚያ መጽሐፍ ውስጥም ላከብረው የሚገባኝ አንድ ሰው አገኘሁ፤ እሱም ጲላጦስ ነው:: እሱ የጠየቀው ጥያቄ መልስ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ፍልስፍና የሚባል ነገር አይኖርም ነበር:: ምክንያቱም የጥያቄዎች መጀመሪያ ብቻ ሳይሆን መጨረሻም ይኸው ነው:: ሌላው ጥያቄው ሁሉ ትርፍ ነውና» ብሏል::

የእውነት ምንድነው ጥያቄን ለመመለስ የመጀመሪያ ሙከራ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

አድርገዋል የሚባሉት ሶፊስቶች ናቸው:: ለዛሬ የእነሱን ፍልስፍና ለዚህ ጥያቄ ከሚሰጡት መልስ ተነስተን ለማየት እንሞክራለን:: ለሶፊስቶች እውነት የስሜት ሕዋስህ ነው:: አንድ ነገር በዓይን ከታየ፣ በአፍንጫ ከተሸተተ፣ በእጅ ከተዳሰሰ፣ በምላስ ከተቀመሰ ወይም በጆሮ ከተሰማ ነገሩ እውነት ነው:: ስለዚህ ለጲላጦስ ጥያቄ መልሱን አግኝተነዋል:- «እውነት የስሜት ሕዋስ (sensation) ነው» በማለት አስቀመጡ::

ፕሌቶ እዚህ ላይ ተነሳና «እናንተ እውነት የምትሉት ይህ ከሆነማ እውነት የለም ማለት ነው» አለ:: «እንዴት?» በማለት ሶፊስቶች ጠየቁ:: ፕሌቶ በምሳሌ ነገራቸው:- «አንተ ጣፍጦህ የምትጠጣው ወይን ጠጅ ለእኔ ከመረረኝ ወይን ጠጁ ወይ ጣፋጭ  አለበለዚያም መራር መሆን እንጂ ሁለቱንም መሆን እንዴት ይችላል? የመቅመስ የስሜት ሕዋስ ግን አንዱን ነገር ሁለት አደረገው:: ስለዚህም የነገሩን እውነትነት አላሳወቀንም:: በሌላ ምሳሌ ደግሞ... አንድ ሚዳቋ ዝንጀሮና ነብር ፊት ብታቆማት አንዲቷን ሚዳቋ ሁለቱም እኩል ያይዋታል:: የሚያይዋት ሚዳቋ ግን እኩል ስሜት በሁለቱ እንስሳት ላይ አታሳድርም፤ ሚዳቋዋ ግን ለሁለቱም እኩል ትታያለች:: ለአንዱ ስሜት አትሰጥም፤ ለሌላው ረሃቡን ትቀሰቅሳለች:: ስለዚህ ሚዳቋዋ በአንድ (የማየት) የስሜት ሕዋስ ታይታ ሁለት ትርጉም ሰጠች:: እንግዲህ አንዱ ነገር ሁለት ትርጉም ከሰጠ የነገሩ እውነትነት አብቅቷል» አለ::

የሶፊስቶችን የፍልስፍና እምነት ገደል የከተተው ደግሞ «እውነትም ሆነ እውቀት የሚባል ነገር የለም» የሚለውና የስኬፕቲሲዝም ፍልስፍና መስራች ፊሮ ነበር:: «እንኳን የአንተ ሃሳብ ቀርቶ የአንተ ራስህ መኖርን እውነት ለመሆኑ እንዴት እርግጠኛ ትሆናለህ?» የሚለን ፈላስፋ ነው:: ታዲያ የሶፊስቶቹም «የስሜት ሕዋስ የእውነት ማረጋገጫ ነው» የሚለውን እምነታቸውን እንዲህ በመጠየቅ ፈተነው:-

«ከፀሐይና ከመሬት የትኛው ይበልጣል?»

ሶፊስቶችም መለሱ:- «ፀሐይ::»



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ፊሮ ጠየቀ:- «ምነው አሁን ሳያት ሽምብራ አከለችብኝ?»

ሶፊስቶች መለሱ:- «ለምድር በርቀት ስለምትገኝ::»

ፊሮ ጠየቀ:- «እንግዲያውስ አሁን የማየው እውነት አይደለማ?»

ከዚያ በኋላ ሶፊስቶች የመለሱትን አላውቅም:: («ስለ ምንም ነገር እርግጠኛ እንዳትሆኑ» በማለት ያስተማራቸው የፊሮ ተማሪዎች ግን ሲሞት እንዳላለቀሱለት አውቃለሁ:: ስለሚጠሉት ሳይሆን መሞቱን እርግጠኛ መሆን ስላቃታቸው ነበር::)

ሶፊስቶች የሶቅራጥስ ዘመን ፈላስፎች ነበሩ:: የሶፊስቶችን ትምህርት በነፃ ለማግኘት የማይታሰብ ነበር:: ለዚህም ነበር አስተማሪነታቸው ለግሪክ ሀብታሞችና ለልጆቻቸው ብቻ ሆኖ የቀረው:: በዚህም ከፍተኛ ገንዘብ ያገኙበት እንደነበር ታሪካቸው ይነግረናል:: በትምህርታቸው አበክረው የሚናገሩት የአቴና ትምህርት ከነበረበት ልማዳዊ አካሄድ ወደተሻለና የላቀ ደረጃ መምጣት እንደሚያስፈልገው ነበር:: ለዚህም እንደዋነኛ መሠረት ያደረጉት «የመናገር ጥበብ» (The art of speaking well ) ነው:: «ቋንቋን መናገርህ በራሱ በቂ አይደለም» የሚሉት ሶፊስቶች «ተናግረህ ማሳመን ካልቻልክ ባትናገር ይሻላል፤ ምክንያቱም የአንተ ንግግር ተራና ውዳቂ ነውና» ይላሉ:: «ይህ ተናግሮ የማሳመን ጥበብ ደግሞ በትምህርት የሚገኝ ነው» በማለት በዚያ ላይ ያተኩራሉ:: በሶፊስቶች እምነት ገንዘብ ካለህ የተሳካልህና እውነተኛ ሰው ነህ:: የገንዘቡ ምንጭ ከየትም ይሁን እሱ ለሶፊስቶች ትርፍና አላስፈላጊ ነገር ነው:: ለነገሩ የሥነ ምግባር (ethics) ትምህርት ጀማሪዎችም እነሱ ናቸው ይሏቸዋል::

የመጀመሪያው ሶፊስት በመባል የሚታወቀው ፕሮታጎራስ (490-420 B.C.) ነው:: ፕሮታጎራስ አቴንስን በተደጋጋሚ በመጎብኘት የገናናው የፔሪክልስ ወዳጅ ለመሆን የበቃ ሰው ነበር:: ይህ ወዳጅነቱም ቱሪ ለምትባለውና በወቅቱ በአቴና ቅኝ ግዛት ስር ወድቃ ለነበረችው ሃገር የመተዳደሪያ ሕግ እንዲያወጣላት ዕድሉን አስገኘለት:: አንዳንዶች ለዚሁ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ስራው ሌሎች ደግሞ በግልፅ በማይታወቅ ሁኔታ በመርከብ ከአቴና ወጥቶ ሲሄድ በደረሰበት አደጋ እንደሞተ ይናገራሉ:: ፕሮታጎራስ፡- «ስለ እግዚአብሔር የማውቀው ነገር የለም፤ ምክንያቱም የእኔ እውቀት እሱን ለማወቅ የሚበቃ አይደለምና» ይላል:: ስለ እውነት ያለው አስተሳሰብ ደግሞ እንዲህ ነበር፡- «ሰው የሁሉ ነገር መመዘኛ ነው:: አንድ ነገር የሚኖረው ሰው ሲኖር ነው፤ ነገሩ የማይኖረው ደግሞ ሰው ሳይኖር ነው::» ይህ ማለት ተጨባጭ እውነት የሚባል ነገር የለም፤ የዓለምን እውነት እያንዳንዱ ሰው እንደራሱ መገለጥ ይመለከተዋል ነው::

ፕሮታጎራስ ለተማሪዎቹ ደጋግሞ የሚመክረውና የሚያስተምረው ደካማውን ሃሳብ ጠንካራ አድርጎ ስለመከራከር ነበር:: በዚህም ሰዎች ስለአንድ ነገር ያላቸውን አስተሳሰብ መቀየር ይቻላል ብሎ ያምናል፡- «የአንተ አስተሳሰብና እምነት ከሌላው በምንም መንገድ የተሻለና የላቀ ሊሆን አይችልም፤ ነገር ግን ጠቃሚ ሊሆን ይችላል:: ሕግና ልማዶቻችንን የምንከተላቸው ከሌላው የተሻሉና የላቁ ስለሆኑ ሳይሆን የሚጠቅሙ ብቻ ስለሆኑ ነው» ይለናል::

የኤምፒዶክልስ ተማሪ የነበረው ጎርጊያስ (483-376B.C.) ሌላው የሶፊስቶችን እምነት ያራመደ ፈላስፋ ነበር:: ይህ ሰው ከትውልድ ሃገሩ ጣሊያን ወደ አቴና በአምባሳደርነት ተልኮ በነበረበት ወቅት በድንቅ ንግግሩና ትምህርቱ የአቴናውያንን ቀልብና ልብ እንደማረከ በታሪክ ይነገራል፡- «ዋና ተግባሬ ግሩም ተናጋሪዎችን ማፍራት ነው» የሚለን ጎርጊያስ «እውነት የሚባል ነገር የለም፤ ቢኖር እንኳን ነገሩን እውነት የሚያደርገው የአንተ ተናግሮ የማሳመን ችሎታ እንጂ የነገሩ እውነትነት አይደለም» ይላል:: ይህንንም ሲያብራራልን፡- «ምንም ነገር የለም፤ አንድ ነገር ቢኖር እንኳን መኖሩን ማወቅ አንችልም፤ ማወቅ ብንችል እንኳን ስለዚያ ነገር ማስረዳት አንችልም፤ ምክንያቱም አለ ብለን የምናስበው ነገር የለምና፤ ስለዚህም አለ ብለን ነገሩን ስላሰብን ብቻ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

እንዴት በድፍረት አለ ብለን እንፈርዳለን» ይላል::

«ለምሳሌ» ይላል ጕርጂያስ «አንድን ነገር ሁለት ሰዎች እንዴ እንደሚያዩት ብትጠይቅ በጣም የተለያየ መልስ ታገኛለህ፤ ስለነገ አስረዱኝ ብትላቸው ደግሞ ከሁለቱ ሰዎች የአንዱ ንግግር ስለነገ የበለጠ ሊያሳምንህ ይችላል:: ለዚህም ነው ነገሮች እውነት ናቸው ብለን እንድናምን የተሻለ ተናጋሪ ሰው መፍጠር አለብን የምንለው... ይህ ደግሞ በእኛ ትምህርት እንጂ በሌላ አይገኝም» ይለናል::

በዚህ መልክ እጅግ የበዙ የፍልስፍና ሥራዎቹን አበርክቷል የሚባለው ጕርጂያስ ከሥራዎቹ በአሁኑ ወቅት አሉ የሚባሉት ሦስት ብቻ ናቸው:: ከሦስቱ በአንዱና ታላቅ ሥራው ተደርጐ በሚወሰደው "Ecomium on Helen of Troy" ውስጥ በአሰፈረው የፍልስፍና ሃሳቡ «የሃገር ክብር ፅናት፣ የሰውነት ክብር ውበት፣ የነፍስ ክብር ጥበብ፣ የተግባር ክብር ኃይል፣ የንግግር ክብር ደግሞ እውነት ነው» ይለናል::

ሌላው የሶፊስት ፍልስፍና አራማጅ ደግሞ አንቲፎን ነበር:: አንቲፎን ከሌሎቹ እጅግ የተሻለና የበረታ ፈላስፋ እንደነበር የሚነገርለት ሰው ነው:: ስለ አንቲፎን ሕይወት ብዙ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ትምህርቶቹ ግን በሶፊስቶች ፍልስፍና ሰፊውን ቦታ ይዞ ይገኛል::

«ከሕግና ልማድ ይልቅ ልንከተለውና ልናከብረው የሚገባን ተፈጥሮ ነው» የሚለን አንቲፎን «ሕግና ልማድ ስትጥስ ሌላው ሰው ምስክር ሆኖ ካልተመለከተህ በቀር እንደጣስክ አይቆጠርም፤ ተፈጥሮን ግን ማንም ሊጥስ አይችልም... ለምሳሌ ከሽምግልናና ከወጣትነት ለእኔ የበለጠው እውነት ሽምግልና ነው:: ምክንያቱም ሽማግሌው ወጣት ነበር፤ ወጣቱ ግን ሽማግሌ አልሆነም:: የሽማግሌው ወጣትነት እውነት ነው (በአንድ ወቅት ወጣት ነበርና)፤ የወጣቱ ሽማግሌ መሆን ግን እርግጠኛ አይደለሁም (ወጣቱ ሳይሸመግል ሊሞት ይችላልና):: ስለዚህ የበለጠ እርግጠኛ የሆንኩበት ሽምግልና ለእኔ እውነት ነው:: የተፈጥሮ እውነት የማይጣሰው እንዲህ ነው» ይለናል::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

«አንድን ነገር እውነት የሚያደርገው የአንተ የንግግር ኃይል ነው» የሚለን አንቲፉን ማቴሪያሊስት ነበር የሚሉትም አሉ:: ይህንንም በራሱ ምሳሌ ሲነግረን:- «ለምሳሌ አልጋህ የተሰራው ከእንጨት ነው፤ እንጨት ደግሞ የዛፍ ውጤት ነው:: አልጋህን መሬት ውስጥ ተክለኸው ለመብቀል እንኳን ቢችል የሚሆነው ዛፍ እንጂ አልጋ አይደለም:: ስለዚህም አልጋ ተክለህ ዛፍ አገኘህ:: ታዲያ እውነት ያለው ከነገሩ ነው ወይስ ከአንተ ንግግር?» ይላል:: ይህ የእሱ ሃሳብ አሪስቶትልንም አበክሮ እንዲያስብ ያደረገው ጉዳይ ነበር::

ስለሌላው የሶፊስቶች ፍልስፍና አራማጅ ፕሮዲከስ (5ኛው ክ.ዘ.) በመጠኑ ላንሳ:: ፕሮዲከስ በሶፊስቶች ፍልስፍና አንዱና ምናልባትም ከፍተኛውን ቦታ የሚይዘው ነው:: የፕሮዲከስን የፍልስፍና ትምህርት ገብቶ ለመስማት የሚታደሉት በጣም ጥቂቶች ነበሩ ይባላል:: ምክንያቱም የትምህርቱ ክፍያ በወቅቱ እጅግ ከፍተኛ ስለነበር ነው:: የእሱ ትምህርት ሁለት ክፍል የነበረው ሲሆን የመጀመሪያው 50 ድራህማ (በእኛ 50 ብር ሊሆን ይችላል) ሲያስከፍል በሁለተኛው ደግሞ ገብቶ ለመማር የሚያስከፍለው 1 ድራህማ ብቻ ነበር:: ታዲያ ሶቅራጥስ ስለፕሮዲከስ ሲናገር:- «50 ድራህማ አስከፍሎ የሚያስተምረው ትክክለኛ ቃላትን መርጦ ስለመናገር ነው፤ ነገር ግን የሚያስተምራቸው ቃላት በራሳቸው ትክክለኛ መሆናቸውን ምን እርግጠኛ አደረገው?» በማለት ጠይቋል:: ፕሮዲከስም እንደሌሎቹ ሶፊስቶች የሚያበክረው የንግግር ኃይልና ውበት ላይ ነበር:: በዚህም ትምህርቱ በአቴናውያን ዘንድ ከፍተኛ መደነቅን አትርፎ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን::

ሶቅራጥስም በጥሩ ተናጋሪነታቸው ከሚያደንቃቸው ሰዎች አንዱ ፕሮዲከስ እንደነበር አልሸሸገም:: በአንድ ወቅት ሶቅራጥስ ለተማሪዎቹ ሲያስተምር ስለፕሮዲከስ የተናገረው ነው ተብሎ በሚነገረው ቀልድ ልሰናበት:- «ፕሮዲከስ አንድ ቀን የ50 ድራህማ የሚያስከፍለውን ትምህርቱን ጨርሶ በሁለተኛውና 1 ድራህማ ብቻ ተከፍሎ በሚገባበት



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ክፍል ጠለቅ ያለ የፍልስፍና ሃሳብ ሲያስተምር ቆየና በድንገት ትምህርቱን አቋረጠ። ታዲያ ተማሪዎቹ ለምን እንዳቋረጠባቸው ጠየቁት፣ ፕሮዲከስም፦'አዳልጦኝ 50 ድራህማ ወደሚያስከፍለው ትምህርት ነው በማለት መልሶላቸዋል» ይለናል ሶቅራጥስ።

# «እነሆ! ከአዳም ጐን አንዲት አጥንት ወጣች፤ እስከዛሬም ታመዋለች»

ከምዕራባውያን ፈላስፎች ታላቅ ክብር የሚቸረው ባውሴት እግዚአብሔርን ቢያገኘው፤ እግዚአብሔርም አንድ ጥያቄ ብቻ የማቅረብ ዕድል ቢሰጠው ያ ጥያቄ ምን ሊሆን እንደሚችል በተማሪዎቹ ተጠይቆ ሲመልስ፡- «ሔዋንን እንዴት እንደፈጠርካት ንገረኝ እለው ነበር» አላቸው:: ባውሴት ይህን ይበል እንጂ በሌላ አጋጣሚ ሲናገር፡- «እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ ከጨረሰ በኋላ አተኩሮ ተመለከተውና ከዚህ የተሻለ መስራት እችል ነበር በማለት አሰበ:: ለጥቂት ጊዜም አሰላሰለና ሰውን በመፍጠሩ ተፀፀተ» ይለናል:: እግዚአብሔር ሔዋንን ስለመፍጠሩ ባውሴት «እጠራጠራለሁ» ብሏል:: «ለዚህም ነው» ይላል «እግዚአብሔር ከአዳም በኋላ እምብዛም ሰው ለመፍጠር ያልተጨነቀው»::

«እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠረበት ብቸኛው ምክንያት የአዳም ጥያቄ ነው» የሚሉን ምዕራባውያን ፈላስፎች «ለነገሩ ሔዋን ሳትፈጠር እስቀድሞ ብዙ ተባዙ ስላለን ምድርን ለመሙላት የእሷ መምጣት እምብዛም አስፈላጊ አልነበረም:: የሚገርመው ግን ከጐኑ አጥንት ወጥታ ተመልሳ የአዳም የጐን ውጋት መሆንዋ ነው» ይላሉ:: ፈላስፎቹ አክለውም፡- «እግዚአብሔር በመጀመሪያ ዓለምን ፈጠረ:: በቀጣዩ ቀን ሰውን ፈጠረና ከስራው ሁሉ አረፈ:: በማግስቱ ሴትን ፈጠረ:: ከዚያን



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ቀን ጀምሮ እግዚአብሔርም ሆነ ሰው እረፍት አላገኙም» ይሉናል::

እግዚአብሔር አስቀድሞ የፈጠረው ሔዋንን ነው የሚሉንም አሉ:: ታዲያ አንድ ቀን ሔዋን እግዚአብሔር በገነት ሲንሸራሸር አገኘችው:- «አባክህ እግዚአብሔር ከእዚህ የገነት ፍሬ መብላት፣ ከአባብም ጋር መጫወት ሰልችቶኛልና ወንድ ፍጠርልኝ» አለችው:: እግዚአብሔርም በአንድ ነገር ከተስማማች ወንድ እንደሚፈጥርላት ነገራት:: ብቸኝነት ያንገፈገፋት ሔዋን የእግዚአብሔርን ጥያቄ ያለማንገራገር እንደምትቀበል ነገረችው::

«ወንድን እፈጥርልሻለሁ፤ ነገር ግን እሱ ከአንቺ ቀድሞ እንደተፈጠረ፣ አንቺም ከእሱ እንደወጣሽ ታሳምኚዋለሽ» አላት:: ሔዋንም:- «ጌታ ሆይ! ወንድን ፍጠርልኝ እንጂ ያልከኝን አደርጋለሁ» በማለት በደስታ ፈነደቀች:: እግዚአብሔር በቅፅበት ወንድን ከሔዋን የጐን አጥንት ምዝዝ አድርጎ አጠገቧ ቁጭ አደረገው:: ሔዋን ደስታዋን መቆጣጠር አቅቷት ስትፈነድቅ «በይ ስም አውጭለት» አለ እግዚአብሔር:: ሔዋንም «አዳም» ብዬዋለሁ አለች:: በዚህም ለእግዚአብሔር የገባችለትን ቃል ፈፀመች:: አዳም ማለት የፍጥረት መጀመሪያ ማለት ነዋ!

በዚህ ታሪክ ከተስማማን ሴት ውሸትን የተማረችው ከእግዚአብሔር ሊሆን ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ አይዋሽም፤ እንዲያውም ሔዋን ድንገት አዳልጧት ለአዳም እውነቱን ትነግረው ይሆናል በማለት በእሷ ላይ ክትትሉን እስከዛሬ አላቋረጠም:: የመጀመሪያ ሥራው ያደረገውም ሔዋን የምትናገረውን ሁሉ አዳም እንዳያምናት ማድረግ ነበር:: በዚህ በኩል እግዚአብሔር የተሳካለት አይመስልም:: እንዲያውም አዳም ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚያምነው ሔዋንን ሆነ:: እግዚአብሔር አትብላ ያለውን ፍሬ በልቶ በሕይወት ከመኖር የሔዋንን ቃል ሰምቶ መሞትን መረጠ:: በዚህም እግዚአብሔር ቂም ቋጥሮ «ትሞታለህ» አለው:: አዳም እንግዲህ ለፍቅር የተሰዋ የምድራችን የመጀመሪያው ጀግና መሆኑ ነው::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ሔዋን የእግዚአብሔርን ቃል ትፈፅም እንጂ ራሱን እግዚአብሔርን መጠራጠሯ ደግሞ አልቀረም፡፡ በተለይም አዳም በገነት ውስጥ ሲዞር አምሽቶ ከመጣ ቁጣዋና ግልምጫዋ አዳምን ማበሳጨት ጀምሮ ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ቀን አዳም ሲዞር ካመሸበት በድካም ተመልሶ አልጋው ላይ ጉትን እንዳሳረፈ እንቅልፍ ይዞት ሄዷል፡፡ ከእንቅልፉ በድንገት የባነነው ሔዋን ደረቱን ስትቆነጥጠው ነበር፤ በድንጋጤ የነቃው አዳም ምን እያደረገች እንደሆነ ሔዋንን ጠየቃት፡፡ የሔዋን መልስ አጭር ነበር፦ «የጐድን አጥንትህን እየቆጠርኩ!» (እግዚአብሔር ሌላ ሴት ሰርቶለት ይሆናል ብላ መጠርጠሯ ነበር፡፡)

አንድ በምዕራባውያኑ ዘንድ የተለመደ ቀልድ ላውጋችሁ፡፡ በምድር ላይ የነበረው የሰው ዘር በሙሉ ይሞትና ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይሄዳል፡፡ ታዲያ በዚያ እግዚአብሔር ለሁሉም አንድ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ይኸውም ወንድን የበደሉ ሴቶች በግራ በኩል እንዲሰለፉና እንዲመዘገቡ ነበር፡፡ ሴቶች በሙሉ ይሰለፉና ይመዘገባሉ፡፡ ምዝገባው ሲያልቅ በሉ ወደ ገነት ሂዱ ይላቸዋል፡፡ የወንዶች ተራ ይደርስና በሴት የተበደላችሁ ወንዶች በአንድ መስመር፤ ሴትን የበደላችሁ ደግሞ በሌላው መስመር ተሰለፉና ተመዝገቡ ይላል፡፡ በሴት የተበደሉት ሰልፍ በወንዶች ሲሞላ ሴትን በበደሉት ሰልፍ ላይ የቆመው ግን አንድ ወንድ ብቻ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሰልፉን ሲመለከት በጣም ተቆጣና፦ «እናንተ በእኔ መልክና ምሳሌ ሰርቻችሁ በሴት ስትበደሉ መኖራችሁ ሊያሳፍራችሁ ይገባል፡፡ በእሱ ደስ የሚለኝ አንዱ ልጄን ተመልከቱት፤ ከእሱም ተማሩ፡፡ ልጄ ሆይ በአንተ ኩራሁ፡፡ እንዴት በእዚህ ሰልፍ እንደገባህ በል ለሌሎቹ ንገራቸው» በማለት እግዚአብሔር አዘዘው፡፡

ሰውዬው ግን ግራ በተጋባ መንፈስ፦ «ጌታ ሆይ! በዚህ ሰልፍ ለብቻዬ መቆሜ ለእኔም ግራ የገባኝ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም በእዚህ በኩል እንድሰለፍ ያዘዘችኝ ሚስቴ ነበረች» በማለት መለሰለት፡፡

መቼም የፍልስፍና ተግባር ሕይወትን መዳሰስ ሲሆን የሕይወት



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

አንዱ ክፍል ደግሞ ሴቶች ናቸውና ፍልስፍና እነሱንም በሚገባ ዳሷል:: ወንድን ጓደኛህ ልታደርገው ስትችል ከሴት ጋር ግን ከትውውቅ በላይ (Acqueintance) ልታልፍ አትችልም ያለው ማን ነበር?

ታሪክ እንደሚነግረን በጥንታዊ የአይሁዶች ሕግ አንድ ሰው ሴት ልጅ ከወለደ ሻማ አያበራም፤ ሴት ልጅ የወለደች እናትም የመንፃት ጊዜዋ ወንድ ልጅ ስትወልድ ከሚኖርባት እጥፍ ጊዜ ነበር (እንደረከሰች ትቆጠራለችና):: እንዲሁም የአይሁድ ወንድ ከእግዚአብሔር ጋር ራሱን የተቀራረበ አድርጎ ስለሚያምን በየዕለቱ ከሚፀልያቸው ፀሎቶች አንዱና ዋነኛው «አምላኬ ሆይ! አሕዛብ ወይም ሴት አድርገህ ስላልፈጠርከኝ አመሰግንሀለሁ» ነበር:: ይህ እምነት በምስራቁ ጎራ በአንድ ወቅት ተስፋፍቶ እንደነበርና እንዲያውም በአንዳንድ ሃገሮች ወንድ ልጅ ያልወለደች ሴት የተናቀች እንደነበረች ታሪክ ዘጋቢዎች አስፍረውት እናገኛለን::

እግዚአብሔር ሔዋንን ወንድ እንዳያምናት ያደረገው ጥረት ሙሉ በሙሉ ከሽፏል ማለትም አይቻልም:: ታላቁ ራሽያዊ ደራሲ ቶልስቶይ ወዳጆቹ ወጋቸውን ሲሰልቁ በመንገድ አገኛቸው:: የወዳጆቹ ወግ ስለ ሴት እንደነበር የተረዳው ቶልስቶይ:- «ወጋችሁ ውሸት ነበር ማለት ነዋ፤ እኔ ስለ ሴት እውነትን የማወራው አንድ እግሬ በመቃብር አፋፍ ላይ ተንጠልጥሎ ነው:: ያን ጊዜ እውነቱን ተናግሬ ወደ መቃብሬ እዘላለሁ» አላቸው:: ምናልባት የቶልስቶይ ፍርሀት ስለ ሴት እውነቱን ተናግሬ በምድር ላይ አያኖሩኝም ይሆን?

አርስቶትል ስለሴት ሲናገር «ተፈጥሮ በመጀመሪያ ወንድን ፈጠረች፤ ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ወንድን መስራት ስትጀምር ሥራዋ ከሸፈባትና ሴት ሆነች» አለ:: እንግዲህ ሴት የተፈጥሮ ክሽፈት ናት ማለቱ ነው:: በአርስቶትል ሃሳብ ብዙዎቹ ፈላስፎች ሲስማሙ «ይህን ጉዳይ ራሱ እግዚአብሔርም አምኖበታል፤ አድርጎታልም» በማለት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለሙሴ በመጨረሻ በሰጠው



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ትዕዛዝ:- «የእስራኤል ወንድ ልጆች፣ ሴቶችን፣ እናቶችንና ከብቶችን እንዲሁም የቤታቸውን ንብረት ሰብስበው ከግብፅ እንዲወጡና እሱም እንዲመራቸው» ማዘዙን ይጠቅሱና «እንግዲህ ሴት ለወንዱ እንደ አንድ የንብረቱ ክፍል አድርጎ እግዚአብሔርም ቆጥሯታል» ይሉናል::

ብዙዎቹ ፈላስፎች ሴትን የተፈጥሮ ስህተት አድርገው ለመሳል ቢሞክሩም ፕሌቶ «ስህተቱ የተፈጥሮ ሳይሆን የወንዶቹ ሃሳብ ነው» በማለት ያጣጥለዋል:: ስለዚህም ሲናገር:- «ቆንጆ ልጃገረድ በአጠገቡ ስታልፍ አንገቱን ጠምዝዞ በዓይኑ የማይከተል በልቡም የማይመኝ ወንድ ለመኖሩ እጠራጠራለሁ» ይለናል::እንደ ፊሮ ዓይነቶቹ የኋለኛ ዘመን ፈላስፎቹ ደግሞ ይህንን ሲሰማ:- «ወንዱ በዓይኑ የተከተለው በልቡም የተመኘው የራሱን ምኞት እንጂ የሴቷን ውበት አይደለም... እንዲያውም አይሁዶች ስለሴት የነበራቸውን እምነትና ንቀት እግዚአብሔር እንዳዘዘውና ሕግ ሆኖም እንዲኖር የሰሩት ሥራ ተሳክቶላቸዋል» ይለናል::

የቅርብ ዘመናት የዓለማችን ድንቅና ብርቅ ሰዎችም እምነት ከፈላስፎቹ ብዙም ያልራቀ ሆኖ እናገኘዋለን:: ካውንት ኬንሰርሊንግ በጋብቻ ጉዳይ ላይ የእሱና የጓደኞቹን እውነተኛ ተሞክሮ በመጣጥፍ መልክ አንድ መድበል አዘጋጅቶ ለግምገማ ሴሚናር ይጠራል:: በሴሚናሩ እንዲገኙለት ከጋበዛቸው ሰዎች አንዱ በርናርድ ሾው ነበር:: ሾው የግብዣው መልዕክት ሲደርሰው የሰጠው መልስ «ሚስቱ በሕይወት እያለች ስለጋብቻ ሕይወቱ እውነትን የሚፅፍ አንድም ወንድ ስለሌለ በውሸት መድብል ላይ ለመተቸት አልገኝም» የሚል ነበር::

ምንም እንኳን ፈላስፎቹም ሆኑ ፀሐፍት ይህን ይበሉ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢዮብ «...ምነው ጠላቴ ስለ እኔ መጽሐፍ በፃፈ» በማለት የተመኘው ሁሉ የደረሰው ለሴት ሆኖ እናገኘዋለን::

በእውቀቱ ከፍተኛ ክብርና ዝና የነበረው ኦቶ ዊንገር «ወንድ እንጂ ሴት ነፍስ የላትም፣ ስትፈጠር ያለነፍስ ነው የተፈጠረችው» ይል



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ነበር፡፡ ምንም እንኳን በዚህ ሃሳቡ ለረዥም ጊዜ ሽንጡን ገትሮ ይከራከር እንጂ የቤቱ አገልጋይ በነበረች ፍቅር ተሸንፎ ሲሰቃይ ፊትዋን ስላዞረችበት ራሱን እስከማጥፋት ደርሷል፡፡

እግዚአብሔር ወንድ ስለሆነ ወንድን ሲፈጥር አድሎ የፈፀመ መስሎ የሚሰማቸው ብዙዎች ቢኖሩም «ወንድንም በድሎታል» በማለት የሚከራከሩም አልጠፉም፡፡ የ18ኛው ክፍለ ዘመን ድንቅ ፈላስፋ ሞሪስን እዚህ ላይ በመጥቀስ ልሰናበት፡- «እግዚአብሔርም አዳምን ጠራው፡ አዳም ሆይ! መልካምና ክፉ ዜና አምጥቼልሀለሁ፡፡ በመጀመሪያ የቱን ልትሰማ ትወዳለህ?» በማለት ጠየቀው፡፡

አዳምም መለሰ፡- «መልካሙን ዜና ጌታ ሆይ!»

እግዚአብሔርም፡- «መልካሙ ዜና የምታመነዝርበትም ሆነ የምታስብበት ሰርቼልሀለሁ» አለው፡፡

አዳምም፡- «ታዲያ ክፉው ዜና ምንድነው?» በማለት ጠየቀ፡፡

እግዚአብሔርም፡- «ክፉው ዜናማ ሁለቱንም በአንድ ጊዜ መጠቀም አለመቻልህ ነው! አንዱን ስትጠቀም ሌላውን ጥለህ ነው» አለው፡፡

ሞሪስም «ከዚህ በላይ በደል ሊኖር አይችልም» በማለት ለወንድ ሃዘኑን ይገልፃል፡፡



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ፈርቼ የደበቅሁትን እውነት የማይፈራ አውጥቶ ይፃፈው

«ጥንት የተወለድሁት ከአክሱም ካህናት ነው:: እኔ በአክሱም አውራጃ ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በ1592 ዓ.ም ነሐሴ 25 ቀን በሦስተኛው ዓመተ መንግሥቱ ለአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከአንድ ገበሬ ተወለድሁ:: በክርስትና ጥምቀት ዘርዓ ያዕቆብ ተሰየምኁ፣ ሰዎች ግን ወርቂ ይሉኛል...

«በልጅነቴ ስጫወት እግዚአብሔር ከሞት አወጣኝ፤ ከጓደኞቼ ጋር ስጫወት ወደ ገደል ወደቅኁ፤ እግዚአብሔር በተዓምራቱ እንዳዳነኝ እንጂ በምን እንደዳንኁ አላወቅሁም:: ከዳንኁም በኋላ ገደሉን በረኸርም ገመድ ስፈርሁት፤ 25 ክንድ ተስንዝርም ሁኖ ተገኘ:: እኔም ተነስቼ ድኄ የአዳነኝ እግዚአብሔርን እያመሰገንኁ ወደ መምሬ ቤት ሄድኁ::»

ይህ እንግዲህ ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዓ ያዕቆብ ነው:: ለዘርዓ ያዕቆብ እግዚአብሔርና ሃይማኖት ሁለት ነገር ናቸው:: በራሱ አንደበትም ሲናገር «...የቅዱሳት መፃህፍትን ትርጓሜ እንድማር ሄድኁ... መፃህፍትንም ፈረንጆች እንደሚተረጉሟቸው፣ እንደገናም የሃገራችን መምህራን እንደሚተረጉሟቸው ተማርኁ:: ትርጓሜአቸው ግን ብዙ ጊዜ ከልቦናዬ ጋር አልተስማማም:: ነገር ግን ሃሳቤን ሁሉ በልቤ ሸሽጌ ዝም አልኁ...»

ዘርዓ ያዕቆብ ከትውልዱ ቀድሞ የሄደ፣ ቀድሞም የነቃ ሰው



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

እንደነበር የእሱ ታሪክ ፀሐፊዎች ይናገራሉ:: እግዚአብሔር ለመኖሩ ባይጠራጠርም ሰዎች ለእግዚአብሔር በሰጡት ፍቺ ላይ ግን አይስማማም:: አለመስማማቱን ግን ለመናገር ድፍረቱ አልነበረውም... የሶቅራጥስና የመሰሎቹን ፈላስፎች ዕጣ በሚገባ የተረዳ ይመስለኛል::

እንዲህ ብታደርግ፣ እንዲህም ባታደርግ እግዚአብሔርን ታገኘዋለህ ወይም ትቀደሳለህ አሉኝ፤ እኔ ግን አልተቀበልኩትም፣ አለመቀበሌን ደግሞ በልቤ ሸሽግሁት እያለን ነው:: ለነገሩ በልብ ከሸሸጉት እውነት በግልፅ የተቀበሉት ሐሰት ሳይበልጥ ይቀራል?

ዘርዓ ያዕቆብ «በቅዱሳት መፃህፍት የተፃፈው ሁሉ እውነት ይሆንን?» ብሎ ለመጠየቅ መድፈሩ በራሱ የነበረውን ነገሮችን በጥልቅ የመመርመርና የመረዳት ችሎታ ያሳየናል::

«ኋላም ይህ በቅዱሳት መፃሕፍት የተፃፈው ሁሉ እውነት ይሆን አልን? ብዬ አሰብኩ» ይላል:: ይህ ሃሳቡ በራሱ በዘመኑ ከፍተኛው ኃጢያት ተደርጎ ሊወሰድ ሲችል ቅጣቱም እንደዚያው የከበደ ይሆን ነበር... ዘርዓ ያዕቆብ በልቡ ሸሽገው እንጂ::

«በጣም አላወቅሁምና የተማሩና መርማሪዎች ሰዎች እውነት እንዲነግሩኝ ሒጀ ልጠይቃቸው ብዬ አሰብኩ:: እንደገናም ሰዎች በልባቸው የአለው ከአልሆነ በቀር ምን ይመልሱልኛል ብዬ አሰበኩ:: ሰው ሁሉ ሃይማኖቴ የቀናች ናት ይላል፤ በሌላ ሃይማኖት የሚያምኑም በሐሰት የሚያምኑ የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው...»

ዘርዓ ያዕቆብ በዚህ ዓይነት የሚያነሳው ጥያቄ ሃይማኖትን ሳይሆን የእምነትን ጉዳይ የሚፈትን ነው:: የምታምነው ለመኖሩ ማስረጃ ማቅረብ ካልቻልክ የአንተ እምነት ሐሰት ነው እንደማለት ነው:: ዘርዓ ያዕቆብ አንድስ እንኳን ሰው እምነቱ እውነት ለመሆኑ የሚያስረዳኝ አላገኘሁም ይለናል::

«እኔም መጀመሪያ ስለ ብዙ የሃይማኖታችን ነገር አንድ የፈረንጆች መምህር ጠየቅሁ፣ እርሱ ግን ሁሉን እንደ ሃይማኖቱ አድርጎ ፈታው



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

(ተረጉመው):: ኋላም አንድ ትልቅ የኢትዮጵያ መምህር ጠየቅሁ፤ እርሱም ሁሉን እንደ ሃይማኖቱ አድርጎ ተረጉመው፤ እስላምና አይሁድም ብንጠይቅ እንደ ይሁ እንደ እየሃይማኖታቸው ይተረጉማሉ:: ታድያስ እውነት የሚፈርድ የት አገኝ አለኑ? ሃይማኖቴ ለእኔ እውነት እንደ እሚመስለኝ እንደ ይሁ ለሌላው ሃይማኖቱ እውነት ይመስለዋል:: ነገር ግን ፅድቅ አንዲት ብቻ ናት...»

ዘርዓ ያዕቆብ ፅድቅ የሚላትን ነገር በግልፅ ባያስቀምጣትም ከፍልስፍናው መረዳት እንደሚቻለው እግዚአብሔር ይመስለኛል::

«እኔ አዋቂ ብሆን ምን አውቃለሁ? ብዬ አሰብኑ:: ከፍጥረት ሁሉ የሚልቅ ፈጣሪ እንዳላለ አውቃለኑ አልኑ:: ከታላቅነቱ የተረፈ ታላላቅን ፈጥሮአልና፤ ሁሉንም የሚያውቅ ነው:: ከአዋቂነቱ በተረፈ አዋቂዎች አድርጎ ፈጥሮናል፤ ለእርሱ ልንሰግድለት ይገባንአል:: እርሱ የሁሉ ጌታና ሁሉንም የያዘ ነውና፤ ወደ እርሱ በፀለይን ጊዜም ይሰማናል» ይላል:: ይኸ ዘርዓ ያዕቆብ እግዚአብሔር የሚለው አምላክ ከልጅነቱ ጀምሮ ስለእሱ (ስለ እግዚአብሔር) የሚነግረው (የሚያስተምረው) ሃይማኖት ባይኖር እንዴት ሊያውቀው ይችል እንደነበር በጊዜው ሊጠየቅ በተገባ ነበር:: አለበለዚያ እግዚአብሔርን አውቃለሁ እያለ እሱን ያሳወቀውን ሃይማኖትን እንዴት ሊጠራጠር ይችላል?

ለምሳሌ ዘርዓ ያዕቆብ ስለ ፆም ሲናገር... «አንድ ቀን በልቶ አንድ ቀን መፆም ጤናን ያጠፋል» ይላል:: እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር አልበላም ማለት በራሱ ኃጢያት ነው እንደማለት ነው... «በልተን ልናመሰግነው እንጂ በረከቱን ልናርም አይገባንም» ይላል::

ፆም ከፍትወተ ሥጋ ራስን መቆጠብ ነው የሚሉም አሉ:: በዚህም ዘርዓ ያዕቆብ አይስማማም:: «ሕገ ፆም የሥጋን ፍትወት ለመግደል የተሰራ ነው የሚሉኝ ቢኖሩም፤ ፍትወተ ሥጋ ወንድ ወደ ሴት ሊሳብ፤ ሴትም ወደ ወንድ ልትሳብ የፈጣሪ ጥበብ ነውና:: እርሱ ፈጣሪ በሰራው በታወቀ በሥጋዊ መገናኘት ስርዓት ካልሆነ በቀር ማጥፋቱ አይገባም



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

አልጉ:: ፈጣሪያችንም ይኸን ፍትወት በሰው ስጋና በእንስሳም ላይ በከንቱ አላስገባውም... ነገር ግን ለዚህ ዓለም ሕይወትና ለፍጥረት በተሰራለት መንገድ ሁሉ መሠረቱ ሁኖ እንዲቆም ይኸንን ፍትወት በሰው ሥጋ ዘንድ ተከለው» ይላል::

የዘርዓ ያዕቆብ ድንቅ ፍልስፍና እና ምርመራ በጊዜው በልቡ ሽሽጎ ባይቀር ድንቅ ነበር:: በአጭሩ የዘርዓ ያዕቆብን ፍልስፍና ጠጋ ብለን ስንፈትሽ ምግብ ሰጥቶ አትብላ፣ የፍትወት ሥጋ ሰጥቶ አታመንዝር የሚል አምላክ አይኖርም እንደማለት ነው:: እሱ ለፈጠረው ነገር ሰዎች ሕግ አበጁለት ይለናል:: ሰዎች የሰሩት ሕግ ደግሞ ሃይማኖት ተባለ «ነገር ግን ሰዎች ያስተማሩትን ሃይማኖት በመረመርን ጊዜ በእርሱ ውስጥ ሐሰት ከዕድቅ እውነት ጋር ተጨምሮበታልና:: ስለዚህ በእነርሱ አንስማማም» ብሏል:: ጥያቄው እንግዲህ እውነትና ሐሰት ምንድነው? ይሆናል::

ለዘርዓ ያዕቆብ ሐሰት ወይም ኃጢአት ማለት ራሱ ሃይማኖት ነው... «እንደገናም የሰው ሃይማኖት ከእግዚአብሔር ብትሆን ክፉዎችን ክፉ እንዳያደርጉ እያስፈራራች መልካም እንዲያደርጉ ትፈቅድላቸው ነበር:: ደጉችንም በትዕግስታቸው ባፅናናቻቸው:: ለእኔም እንዲያ ያለችው ሃይማኖት ባሏ ሳያውቅ በምንዝርና የወለደች የወንድ ሚስት ትመስለኛለች:: ባሏ ግን ልጅ ስለመሰለው በህፃኑ ይደሰታል:: እናቲቱንም ይወዳታል:: በዝሙት እንደወለደች ባወቀ ጊዜ ግን ያዝናል ሚስቱን ከልጇ ጋር ያባርራታል::

«እንደዚሁ እኔም ሃይማኖቴን አመንዝራ ወይም ዋሾ መሆንዋን ካወቅሁ በኋላ ስለ እርሷና በዝሙት ስለተወለዱ ልጆቿ አዘንሁ...» ይለናል::

በዘርዓ ያዕቆብ እምነት የእግዚአብሔር ሥራ እጅግ መልካም ሃሳቡም ጥልቅና የማይደረስበት ሆኖ ሳለ ትንሽና ምስኪን የሆነው ሰው ለሌላው ሰው፡- የእግዚአብሔርን ጥበብና እውነት እንድገልፅለት ከእግዚአብሔር



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ዘንድ ተልኬ መጣሁ' በማለት ለምን ይዋሻል? በማለት ይጠይቃል፡፡ የዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና መቋጫ «እግዚአብሔር እኔን ለመምራትም ሆነ ለማስተማር ከበቂ በላይ ነው» ይሆናል፡፡

የዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና ጥያቄ እንጂ መልስ የለውም የሚሉም አሉ፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር በራሱ እኔን ለማስተማር በቂ ነው ይበል እንጂ እሱን ለማስተማር በቂ ነው የሚለውን እግዚአብሔር «አስተማሪዎቹ የእሱን መኖር አስቀድሞ ባይነግሩት ከእነመኖሩም ላያውቀው በተቀመጠ ነበር» ይላሉ፡፡

ዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍናውን በልቡ ሸሽጐ በሚስጥርም ዕፎ ያስቀምጥ ነበር... «ብዙዎች ክርስቲያን እመስላቸው ነበር፤ እኔ ግን አልነበርሁም» የሚለው ዘርዓ ያዕቆብ ለዚህ ምክንያቱ ከላይ በመጠኑ እንደዳሰስነው ቢሆንም ለእሱ ግን እየሱስ የተናገረውን ተቀብዬ ነው ይላል፡- «ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው፡፡» (ሉቃ. 5:32)

ፈላስፋው በልቡ የሸሸገውን እውነት አንድ ቀን (እሱ ከሞተ በኋላ) የሚመረምረውና የሚጨምርበት ይነሳ ዘንድ ይመክራል... «ከእኔ በኋላ የሚመጡ እንዲያውቁኝ ግን እስክሞት ድረስ በእኔ ዘንድ ሸሽጌ የምይዘው ይህን መጽሐፍ ልፅፍ ወደድሁ፡፡ ከሞቴ በኋላ አዋቂና መርማሪ ሰው ቢገኝ ግን በሃሳቤ ላይ ሃሳቡን እንዲጨምርበት እለምነዋለሁ፡፡ ይኸውም እኔ ከዚህ በፊት ያልተመረመረውን መመርመር ጀመርሁ፡፡ የሃገራችን ሰዎች በእግዚአብሔር ረድኤት አዋቂዎች እንዲሆኑና እውነትንም ወደማወቅ እንዲደርሱ ሐሰትን እንዳይታመንዋትና አመፃንም ተስፋ አድርገው ዝም ብለው ከከንቱ ወደ ከንቱ እንዳይሄዱ እውነትን እንዲያውቁና ወንድሞቻቸውንም እንዲወዱ እንጂ ከእንግዲህ እስከአሁን እንደሚያደርጉት በከንቱ ሃይማኖታቸው እንዳይጣሉ እኔ የጀመርሁትን አንተ ጨርሰው...»

እዚህ ላይ የዘርዓ ያዕቆብ ንግግር በአጭሩና በግልፅ ሲቀመጥ፡-

@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

«እኔ የደረስሁበት እውነት አለ፤ እውነትን እንዳልናገር ግን [illegible] ፈራሁ፤ ስለዚህም ፈርቼ የደበቅሁትን እውነት የማይፈራ [illegible] ይፃፈው፤ እሱም ቢሆን ግን እኔ ከሞትኩ በኋላ መሆን አለበት...» [illegible] ማለት ነው:: የዘርዓ ያዕቆብን ነፍስ እግዚአብሔር ይማር!



Scanned by CamScanner

@BOOKALEM

# «ሕይወቴ እንደተከፈተ መጽሐፍ ነው»

*«መንገዱን አውቀዋለሁ:: ቀጥታና ጠባብ ነው:: እንደሰይፍ ስለትም የሰላ ነው:: ነገር ግን በዚያ ላይ ስሄድ በደስታ ነው:: በመንገዱ ላይ ስወድቅ አለቅሳለሁ:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል 'የሚበረታ አሱ አይጠፋም' ይላል:: በዚህ ቃል ላይ የማይናወጥ እምነት አለኝ:: በድካሜ አንድ ሺህ ጊዜ በመንገዱ ላይ ብወድቅ እንኳን እምነትን አላጠፋም:: ሥጋዬ ለመከራ የተጋለጠ ቢሆንም በመከራዬ ውስጥ ግን ታላቅ ብርሃን እንደማይ ተስፋ አለኝ::»*

ከታላቁ የጋንዲ ባህር በጥቂቱ እንቀዳለን:: ጋንዲ ዓለም በታሪኳ ካየቻቸው መሪዎች፣ ፈላስፋዎች፣ ኃይማኖተኞች... ወዘተ ታላቅ ዕውቀትና ጥበብ የነበረው ብቻ ሳይሆን፤ አንድ ሰው የእውነትን መንገድ ከተረዳ በኋላ በዚያ መንገድ ለመሄድ የሚያስፈልገውን መስዋዕት፡ ፣ ለመክፈል ምን ያህል ብቃት በውስጡ እንዳለ ያሳየ ብቸኛው ሰው ነበር::

«መንፈሴ በአንድ መንገድ፤ ሥጋዬ ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ይመሩኛ ል:: ከሁለቱ ኃይሎች ፍጭት ነፃነቴ እንደሚወጣ ግን ይሰማኛል:: ያ ነፃነት ግን ዘግይቶ እንደሚመጣ፣ በስቃይም እንደሚገኝ አውቃለሁ...» የሚለው ጋንዲ ነፃነቱን ለማግኘት የሄደበት ጉዳና በሰው ችሎታና



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ጭርደ ሊወጡት ይችላሉ ብሎ ማሰቡ እጅግ ይከብዳል:: ስለ ጋንዲ ሕይወት የማይታወቅ ነገር የለም ማለት ይቻላል:- «ሕይወቴ እንደተከፈተ መጽሐፍ ነው፤ ምስጢር የለኝም፤ ሰዎች ምስጢር እንዲኖራቸውም አላደፋፍርም...» የሚለው ሞሐንዳስ ካራማቻንድ ጋንዲ ኦክቶበር 2 ቀን 1869 ዓ.ም ካቲህዋር በምትባለው የሕንድ ግዛት ተወለደ:: ለቤተሰቡ ሦስተኛ ልጅ የነበረው ጋንዲ አባቱ በሕንድ የሚገኙ ሦስት ግዛቶችን በተለያየ ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትርነት አስተዳድሯል:: በልጅነቱ ከቤተሰቡ እየተደበቀ በሕንድ እምነት የተከለከለውን ሥጋ ይበላ የነበረው ጋንዲ በአንድ ወቅት ግን ይህንኑ ድርጊቱን አቆመ:- «ሥጋ መብላት ያቆምኩት ኃጢአት ሆኖብኝ ሳይሆን ወላጆቼን መዋሸቱ የከበደ ኃጢአት ሆኖ ስላገኘሁት ነው» የሚለው ጋንዲ በ19 ዓመቱ ወደ እንግሊዝ ሃገር ተጉዞ አትክልት ተመጋቢነቱን በዚያ ጀመረ::

በእንግሊዝ ሃገር የሕግ ትምህርቱን ተከታትሎ ሲጨርስ ወደ ቦምቤይ ተመልሶ የሕግ አርቃቂ ሆኖ ይሠራ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን:: ይህ የሕግ አርቃቂነት ሥራው አንድ የሕግ ብርሃንን በውስጡ አበራለት_ ይኸውም የዘር መድልዎ በሕንድ ሥር የሰደደ መሆኑን መረዳቱና ይኸንንም ለመታገል ቆርጦ መነሳቱ ነበር:: ከሕንድ የእምነትና የፍልስፍና መጻሕፍት በተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስና የቁራን ጥልቅ ዕውቀት እንደነበረው የሚነገርለት ጋንዲ ከምንም በላይ ግን ለራሺያው ደራሲ ቶልስቶይ ታላቅ ፍቅርና ክብር እንደነበረው በሕይወት ዘመኑ በተደጋጋሚ ተናግሯል:: በተለይም በቶልስቶይ "The Kingdom of God is within you" በተባለው ሥራው እጅግ ተማርኮ እንደነበር ታሪኩ ይነግረናል:: ጋንዲ ስለ ቶልስቶይ ሲናገር:- «ውስጣዊው እኔነቴ ላይ ታላቅ ተፅዕኖውን አሳርፏል» ብሏል::

የጋንዲን የሕይወት ታሪክ ተለክታ በተሰጠችኝ የጥበብ አምድ በሃ ዘርዝሮ ለመፃፍ የማይታሰብ ስለሆነብኝ ከጋንዲ እምነትና ፍልስፍና በመጠኑ ልቆንጥር::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ጋንዲ ስለ እውነት ከነበረው እምነት ብንነሳ፡- «በዚህ ምድር ስኖር ከእውነት በቀር የፈለግሁት ነገር የለም:: መንገዱን አግኝቼዋለሁ ብዬ አሰብሁ:: እውነትን ለማግኘት የማያቋርጥ ትግልና መፍጨርጨር አደረግሁ:: የተረዳሁት ግን እውነት ማግኘት ማለት ራስን ማወቅና መድረሻንም መረዳት ማለት እንደሆነ ነው:: ይህም በአጭር ቃል ሲጠቃለል 'ፍፁም መሆን' ማለት ነው:: ሕሊናዬ ግን ፍፁም አለመሆኔን ሲረዳ ያመዋል:: ፍፁም ለመሆን ብርታትና ኃይሌን በሙሉ ተጠቀምሁ:: ለመሆን ግን አልቻልኩም:: እንደማንኛውም ሰው ፍፁም የማያደርግ ድክመት በውስጤ ነበር...» ብሏል፡

ጋንዲ በማከል እንዲህ ይላል፡- «...ለእኔ እግዚአብሔርን መፈለግ ማለት እውነትን መፈለግ ነው፤ እውነትን ለማግኘት ሕይወቴን መስዋዕት ማድረግ ቢያስፈልግ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ:: እውነትን የሚፈልግ ሰው ደግሞ ከትቢያ ባነሰ ራሱን ያዋረደ (ትሁት) ይሁን:: ዓለም ትቢያን በእግሩ ጫማ ይረግጠዋል፤ እውነትን የሚፈልግ ሰው ግን በትቢያ የተረገጠ ሆኖ ራሱን ያዋርድ:: ያን ጊዜ የእውነት ጭላንጭል ይበራለታል::»

በእግዚአብሔር ስለመታመን ደግሞ እንዲህ አለ፡- «ከከበበኝ ጨለማ ይልቅ በደጅ የማያት የብርሃን ጭላንጭል ለእኔ ቅርብ ናት:: ብዙ ጊዜ እሳሳታለሁ፣ እጠፋለሁም:: እምነቴ ግን ሳይሳሳት በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ተመስርቷል:: እግዚአብሔርን ስለማምን ሰዎችን አምናለሁ:: የማምነው እግዚአብሔር ባይኖር ኖሮ የማምነው ሰውም አይኖርም ነበር::» ወዳጆቹንም መከረ፡- «እምነት ሳይኖርህ የምትሠራው ሥራ መጨረሻው በማይደረስበት ጉድጓድ እንደመውደቅ ይቆጠራል::»

ጋንዲ በዘመኑ ሁሉ በሰው ልጅ ዘንድ እንደ ቅዱስ ይታይ እንጂ የራሱን ቅዱስ መሆን «ፈፅሞ አልቀበለውም... በአንፃሩ ቅዱስ ሳልሆን ምናልባት በሥርዓት የታነፅኩ ሰው እንደሆንኩ እንጂ» ይላል:: «እኔን ቅዱስ ማለት ቅድስናና አለማወቅ ወይም ማርከስ ነው» የሚለው ጋንዲ

በአንድ ወቅት በዚሁ ጉዳይ ላይ ሲናገር፡- «ባለራዕይ ነኝ ብዬ አልዋሽም... ቅዱስ ነህ የሚሉኝንም አይደለሁም እላለሁ... እኔ ከምድር የወጣሁ ምድራዊ ነኝ... እንደ እናንተው ለብዙ ድክመቶችም ተጋልጫለሁ... ነገር ግን ዓለምን አይቻታለሁ:: ዓለምን በተከፈቱ ዓይኖቼ አስተውያታለሁ... በሰው መንገድ የተወረወሩ ፍላፃዎች በእኔም መንገድ ላይ በተደጋጋሚ ወድቀዋል... የዚህ ሁሉ ድምር ግን በሥርዓት አንፆኛል...» ብሏል::

«የሃገሬ የሕንድ ሰዎች! ራስን መስዋዕት ከማድረግ ወንጌል ውጭ ሌላ ወንጌል አትከተሉ» በማለት ሕዝቡን ያስተማረው ጋንዲ ለእሱ ግድ አድራጊም ሆነ ግፍ የተዋለበት ልዩነት የለውም... ምነው ቢሉ፡. «ሁለቱም መስዋዕት በመሆን እሳት ውስጥ ያልፋሉና:: ነገር ግን የህሊናን ድምፅ ማንም ሊያጠፋት አይችልም... በሁለቱም አእምሮ እስከ ወዲያኛው ትጮኻለች» ብሏል::

«በውስጤ ያለው የህሊና ድምፅ ዕለት ዕለት እንዲህ በማለት ይቆትታል... በምድር ላይ ብቻህን ብትቀር እንኳን ከግፈኞች ጋር አትተባበር... ዓለም ዓይኗን ብታቀላብህ አንተ ግን ፈገግታህን ለግላት... አትፍራ... በልብህ ያለውን የእውነት ድምፅ ብቻ ታመን፡- «ያ ድምፅ ደግሞ እንዲህ ይላል፡- ባልንጀራህ፣ ሚስትህ፣ ዘመዶችህ... ሁሉም ቢተዉህ... ለምትኖርለትና ልትሞት ለተዘጋጀህበት እውነት ብቻ መስክር... የመኖር ትርጉሙም ይኸው ነውና» በማለት ጋንዲ ስለ እውነት ሊከፈል ስለሚገባው መስዋዕትነት ተናግሯል::

ጋንዲ ስለምዕራባዊ ሥልጣኔ የነበረው ሐሣብ ሲመረመር ከጉዳት በቀር አንዳች ጥቅም እንደሌለው እምነቱ አሳይቶናል::

ከምዕራባውያን ሥልጣኔ አንዱ ተደርጐ በጊዜው ይውሰድ የነበረው የፓርላማ ሥርዓታቸው ነበር:: ነገር ግን ጋንዲ በተለይ ስለ እንግሊዝ ፓርላማ የተናገረውና ከበደ ሚካኤል «ሥልጣኔ ማለት ምንድነች?» በሚለው መጽሐፋቸው ያሰፈሩትን እንመልከት፡- «በጠቅላላው በሚደረገው አስተያየት የፓርላማ አባሎች ግብዞችና የግል ጥቅማቸውን



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ፈላጊዎች ናቸው:: ሥራቸው በፍርሃት ላይ የተመሠረተ ነው:: ዛሬ የተወሰነው ነገ ሊፈርስ ይችላል:: በፓርላማ ተወጥኖ ፍፃሜው ምን እንደሆነ የሚታወቅ አንድ ሥራ እንኳን አይገባኝም:: በጣም ከባድ የሆኑት ጉዳዮች እንኳ በሚቀርቡበት ቀን የፓርላማ አባሉች የሆኑት ሲያንቀላፉ፣ በመቀመጫቸው ላይ ሆነው ሲንጠራሩ ለማየት ተችሏል:: አንዳንድ ጊዜም ሰሚዎችን እስቲያስቆጡ ድረስ እርስ በእርሳቸው የሚለፈልፉበት ሰዓት አለ:: ካርላይል ፓርለማን:- 'የዓለም መለፍለፊያ መደብር' ብሎ ሰይሞታል::... ለፓርላማ የሚባክነው ጊዜና ገንዘብ ሁሉ ዋጋ ላላቸው ሰዎች ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ የእንግሊዝ ደረጃ አሁን ካለበት የበለጠ ከፍ ብሎ በተገኘ ነበር:: ይህ አሁን እኔ የምሰጠው አስተያየት በተለይ ከእኔ ብቻ የመነጨ ሳይሆን ብልሆች የሆኑ ብዙ የእንግሊዝ ተወላጆች ተናግረውታል::...

«ፓርላማ ማለት ሕፃን ልጅ ነው:: ከተቋቋመ ሰባት መቶ ዓመታት በመሆኑ ትልቅ ባያደርገው ኖሮ መቼም ቢሆን የሚያድግ መሆኑ የሚያጠራጥር በሆነ ነበር...» ሲል ተናግሯል::

ጋንዲ ታሪክን መማር የማይጠቅም መሆኑን ይናገራል:: ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ የሚሰጠው የታሪክ ትምህርት ስለ ጦርነት ብቻ የሚናገር በመሆኑ «ይህ ታሪክ ተብሎ ሊጠራ አይገባውም» በማለት ያሳስባል::

ብዙዎች እብድ፣ ሥራ ፈት፣ በሰው ዘንድ ያልተለመደ ሃሳብ የተሸከመና አዕምሮው የተቃወሰ ሰው በማለት ይጠሩሃል ተብሎ በአንድ ወቅት የተጠየቀው ጋንዲ ሲመልስ:- «ይህ ሁሉ ስያሜ ለእኔ ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም እስከዛሬ በትምህርቴ ተስበው የተከተሉኝና ወደ መልካም ምግባርም የመጡ እነሱ ናቸውና» በማለት መልሷል::

«ብዘመኔ በተደጋጋሚ ኃጢአትን ፈፅሜአለሁ» የሚለው ጋንዲ «ለአንድም ቀን ግን ቀንበሩን ተሸክሜ አልዞርኩም» ብሏል:: ስለዚህም ሲናገር... «ጉዞዬ ወደ እግዚአብሔር እንደሆነ አውቀዋለሁ... የኃጢአትን ቀንበር ብሸከም ኖሮ ወደ እሱ አንዲትም እርምጃ ባልተራመድኩ ነበር» ብሏል::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ጋንዲ በተደጋጋሚ በሃሣቡ የማይስማሙ ሰዎች ቢያጋጥሙትም «በሃሣብ አለመስማማት ማለት ጥላቻ ማለት አይደለም... ጥላቻ ቢሆን ኖሮ ከሚስቴ በላይ ጠላት ባልኖረኝ ነበር» የሚለው ጋንዲ «ቢያንስ በአንድ ሃሣብ የማይለያዩ ሁለት ሰዎች እስከዛሬ አጋጥመውኝ አያውቁም» ብሏል::

«ገነትን በምድር ላይ ማምጣት ከተፈለገ 'እኔ' የሚለውን ቃል ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከሃይማኖት... ወዘተ ውስጥ መፋቅ ያስፈልጋል» ይላል ጋንዲ:: ስለ ሰው ልጅ ደህንነት፣ ሰላም፣ ብልፅግና፣ ፍቅር... ከማንም በላይ ያስተማረና፣ የሰበከ ራሱንም አርአያ አድርጐ ያቀረበው ጋንዲ ታሪኩን የሰሙ፣ ያነበቡና የተረዱ ሰዎችም በዚህ ሐቅ ይስማማሉ::

ስለ ጋንዲ ሕይወት በሰፊው የዘገቡ የታሪክ ፀሐፍትም ቢሆኑ ለአንድም ቀን ቢሆን የገባውን ቃል አፍርሶ እንደማያውቅ መስክረውለታል::

ጋንዲ ስለ ሃገር መሪነትና በዙሪያው ስለከበቡት ጠላቶቹም የሚናገረው አለ:- «ከመሣሪያው ጋር የሚጣላ እሱ ክፉ አናጢ ነው፣ ጥፋትን በወታደሮቹ የሚያሳብብም እሱ ክፉ ጄኔራል ነው:: እኔ ክፉ ጄኔራል እንዳልሆንኩ በሚገባ አውቃለሁ:: እስከምን ድረስ መሄድ እንደምችል ጥበብ በሚገባ አስተምራኛለች:: ከንቱ ሆኜ እንዳልቀር እግዚአብሔር ብርታትን ሰጥቶኛል:: ለ50 ዓመታት ከሠራሁት ሥራ እግዚአብሔር የማይፈልገኝ ሰዓት ሲደርስ እንደሚወስደኝ አውቃለሁ... ነገር ግን የከበበኝ ጨለማ በአጭር ጊዜ በብርሃን እንዲዋጥ ፀሎቴ ፅኑ ነው.... ግፈኝነትን የሚቃወም ሕያው እምነት ያላችሁ ሁሉ በፀሎታችሁ ከእኔ ጋር ተባበሩ...» ብሏል::

ጋንዲ ጃንዋሪ 30/1948 ዓ.ም የምሽት ፀሎቱን ለማድረስ በመጓዝ ላይ ሳለ ከጠላቶቹ በተተኮሰ ጥይት ተገደለ::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# «እግዚአብሔርም ሰውን ፈጠረ፤ ሰው ደግሞ ሰይጣንን ፈጠረ»

የዚህ ምዕራፍ ሃሣባችን የሚያጠነጥነው እኔንም እናንተንም ስለሚያስጨንቀን፣ ስለሚያሳስበን ብሎም ስለሚያስፈራን «የጠላታችን» ጉዳይ ይሆናል:: ይህ «ጠላታችን» በላይኛው ዓለም እያለ ስሙ ባህታር ነበር፤ ወደ ታችኛው ዓለም ሲወርድ ብዔልዜቡል፣ ሳጥናኤል፣ ባልዔል፣ ዛምዔል፣ አህርማን፣ ማራ፣ አብዶን፣ ዲያብሎስ በሚሉ ስሞች ሲጠራ ቆየና በመጨረሻም በጣም በተለመደው ስሙ አሁን ድረስ እየተጠራ ይገኛል:: ሰይጣን...

ታላቁ ደራሲ ገጣሚና ፈላስፋ ካህሊል ጅብራን "Satan" በሚለው መጽሐፉ ሰይጣንን እንደሚከተለው እንዲናገር አድርጎት ነበር:: (ሰይጣን የሚናገረው ለቄስ ሳማን ነው)

*«ከፀሐይ በታች ባሉ ከተሞች ሁሉ ስሜ የሃይማኖት የጥበብና የፍልስፍና ምህዋር ሆኗል:: እኔ ባልኖሮ ኖሮ አንድም ቤተ መቅደስ ባልተገነባ፤ አንድም ማማና ቤተመንግስትም ባልተሠራ ነበር:: በሰዎች ልብ ውስጥ ውሳኔን ያመጣሁና፤ የአዲስ ሃሣብ ምንጭ የሆንኳቸው እኔ ነኝ:: የሰዎችን እጅ ያንቀሳቀስኩ እጅ እኔ ነኝ:: ሰዎች ራሳቸውን በሕይወት ያኖሩ ዘንድ የሚታገሉት ኃይል ቢኖር እኔ ሰይጣንን ነው:: ከእኔ ጋር መታገል ቢያቆሙ ስንፍና አእምሮአቸውን፣ ልባቸውንና ነፍሳቸውን*



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ያመነበትን ቅጣት እየሰጠ ይገድላቸዋል::

«የወንዶችን አእምሮ የሴቶችንም ልብ በፍርሃት እያራድኩ በቀጣዩ ብርታት ወደብ ሆኜ የምኖር እኔ ነኝ፤ ለእኔም ባላቸው ፍርሃት ወደተሰያዩ የአምልኮ ቦታዎች እኔን ለማውገዝ፤ አሊያም ወደ ክፋው ማምለኪያ ለእኔ ፍላጐት ለመገዛትና እኔን ለማስደሰት ይጓዛሉ:: መነኩሴው በእኩለ ሌሊት ከአልጋው ተነስቶ እኔን ለማባረር ሲፀልይ ለእኔ ግን ወደ አልጋዋ ከምትጋብዘኝ ሸርሙጣ ለይቼ አልመለከተውም:: እኔ ዘላለማዊና ቋሚ የሆንኩ ሰይጣን ነኝ::

«የገዳማትና የማምለኪያ ቤቶች መሠረት የእኔ ፍርሃት ነው:: በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት መሠረት ላይ ደግሞ መጠጥ ቤቶችና የክፋት ሥራ ቦታዎችን ሁሉ እገነባለሁ፤ እኔ መኖር ባቆም ፍርሃትና ደስታ ከዓለም ላይ ይጠፋሉ፤ በእነሱም መጥፋት ፍላጐትና ተስፋ ያከትማል:: ያን ጊዜ ሕይወት ክሩ እንደተበጠሰ በገና ቀዝቃዛና ባዶ ትሆናለች:: እኔ ዘላለማዊው ሰይጣን ነኝ::

ሰው እንግዲህ አንድም በሚባርከውና ከፍ ከፍ በሚያደርገው በሌላ በኩል ደግሞ በሚረግመውና በሚፈራው ኃይል መካከል እንደተወጠረ ዘመናት አለፉ፤ ነገር ግን የአንዱን ይሁን የሌላውን ትርጉም አያውቀውም ነበር:: ዛፍ በክረምት እንደሚያብብ በበጋ ደግሞ እንደሚረግፍ እንዲሁ ሰውም በሁለቱ መካከል ይገኛል::

የዜን ቡድሂዝም እምነትና ፍልስፍና ተማሪ ብሎም አራማጅ የሆነው አሜሪካዊው ዴቪድ ኩክ ለዛሬው ሃሣባችን ሰፊውን ቦታ እናስይዘዋለን:: ኩክ በቅርቡ «አምላክ፣ ሰይጣንና ታኦ» የሚል ሰፊ የፍልስፍና ሥራውን በመጽሐፍ መልክ ከማሳተሙም በላይ በጉዳዩ ላይ የሰነዘረው ሰፊ አስተያየትም በመረጃ መረብ ተሰራጭቷል:: በኩክ ፍልስፍና መከራና ስቃይ የሰው ልጅ ሊያመልጣቸው የማይቻላቸው እውነታዎች ናቸው:: «ነገር ግን» ይላል ኩክ:- «የመከራና የስቃይ ምንጭ ሰይጣን ነው ማለት የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት እንደመካድ ይቆጠራል...



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ምክንያቱም በእሱ የሚያምኑት ሁሉ 'እግዚአብሔር ለሰው ዘር ያለው እቅድ የሚፈፀመው እሱን በመዋጋትና በማጥፋት ላይ የተመሠረተ ነው' ይላሉና...

«ስለዚህ ይህ የመልካምና የክፉ ሁለትዮሽ አስተሳሰብ በእግዚአብሔር መኖርና አለመኖር ላይ ግጭት ፈጥሯል» የሚለን ዴቪድ ኩክ «...ይህ ግጭት ደግሞ በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ተፈጥሮአዊ ልዩነት ለማወቅ አዳጋች ከማድረጉም በላይ፣ በራሱ በእግዚአብሔር ላይ የተሳሳተ ግምት እንዲኖረን አድርጓል»።

«ነገር ግን የታኦኢስት ፍልስፍና በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት በተለየ መንገድ እንድናየው ከማድረጉም ባሻገር «የሰይጣን ችግር»ን አስመልክቶ ያለውን ግራ መጋባት በተለየ መንገድ ያቀርብልናል» በማለት ዴቪድ ኩክ በታኦኢዝም ፍልስፍና የሰይጣን ምንነትና ችግርን እንዲህ ሊያሳየን ተነሳ...

«ሰይጣን በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል። በሰዎች ውስጥ ያለ ሰይጣንና በተፈጥሮ ውስጥ ያለ ሰይጣን። የሰይጣን ቀንደኛ ጠንሳሽና ፈፃሚውም የሰው ዘር ነው። ክፋት፣ ጥላቻ፣ የዘር መድልዎ፣ ጦርነት፣ ነፍስ ግድያ፣ ስርቆት... እነዚህ ሁሉ የሰው ድርጊቶች ሲሆኑ የሰው ዘር ደግሞ እነዚህን ድርጊቶቹን ሊቆጣጠር ባለመቻሉ ለማመን በሚያዳግት ሁኔታ ዛሬ ድርጊቶቹ ተቆጣጥረውት እናያለን። እዚህ ላይ ተፈጥሮም የራሷ ሰይጣን እንዳላት እናስተውል... ለምሳሌ ተፈጥሮአዊ አደጋዎችን ስንመለከት የሰይጣን ውጤት ነው እንላለን። ነገር ግን ሰይጣን በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በሰው አእምሮም ተዘርቶ፣ አድጐና አብቦ እናየዋለን።...

«በእግዚአብሔር የማያምኑት የሰይጣን መኖር በራሱ የእግዚአብሔርን መኖር ጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል ይሉናል። ይህ አባባል ብዙ ዓይነት ቅርፅ ይዞ ሊወጣ ሊችል ነገር ግን ነጥቡ በአጭሩ ሲቀመጥ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ቻይ፣ ብቸኛ ፈጣሪ ከሆነ ለሰይጣን መኖር ብቸኛው ተጠያቂም እሱ ይሆናል፤ ወይም ደግሞ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

በሰይጣን መኖር የራሱን መኖር ጥያቄ ውስጥ ይከታል፤ ይኸ ካልሆነ ደግሞ ሰይጣንን ለማጥፋት ብቃቱ ወይም ፍላጐቱ የለውም...» በማለት ኩክ አስፍሯል፡፡

ዴቪድ ኩክ በዚህ አባበቃም:- «እነዚህ በእግዚአብሔር የማያምኑት ፈላስፎች እንደሚሉት ምድራዊ አባት ልጁን ከክፉ ለማዳንና ለመጠበቅ በሙሉ ኃይሉና ችሎታው የማያደርገው ነገር የለም... ይሁንና እውን በምድር ላይ ያለውን መከራና ስቃይ ለተመለከተ ሰው እንደ አባት እንዲያየው በአእምሮው የተሳለለት አምላክን አባትነቱ ከምን ላይ ነው? ብሎ መጠየቁ አይቀሬ ነው ይሉናል» በማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት መጽሐፍ በሰው ልጅ አፈጣጠር ታሪክ ላይ ራሱ ሊያሳየን የሚሞክረው ነገር አለ፡፡

*«እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ...» (ዘፍጥ.1:27)*

«እንግዲህ አዳምና ሔዋን ተፈጥረው ብዙም ሳይቆዩ ለፈጠራቸው <u>እንታዘዝም</u> አሉ፤ አለመታዘዝ ብቻ አይደለም <u>ዋሹ</u>፤ መዋሸትም ብቻ አይደለም <u>ተካሰሱ</u> *(አዳምም አለ:- [«ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ፡፡» (ፍጥ.2:12)፤]* ልጃቸው ቃየን ደግሞ ወንድሙን አቤልን ገደለ፡፡ ሩቅ ሳንሄድ እግዚአብሔር በመልኩ በፈጠረው በመጀመሪያው ትውልድ ብቻ የተሠራው ሥራ የእሱን ሁሉን ቻይነትና ጠባቂነት ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል፡፡ ካልሆነም እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪና ጠባቂ ነው የሚለው ሃሳብ የሚያነጣጥረው ለመልካምና ለክፉ አድራጐት ባለበት ኃላፊነት ላይ ይሆናል፤ በአጭሩ ለበጐውም ሆነ ለክፋው ድርጊት ኃላፊው ራሱ ነው» በማለት ዴቪድ ኩክ የሰይጣንን ነገር ሊያሳየን ይሞክራል፡፡

የእግዚአብሔርን ፈጣሪነትና ጠባቂነት «በፍፁም አልቀበልም» የሚለን ክላረንስ ዳሮው ደግሞ ለሰው ዘር መከራን ያቱረፈችለት ምድር በሰው በራሱ እንኳን ለጥፋቱ ከሰራው መሣሪያ በኋላ ታላቅ ጥፋት ስለመጣችለት «ተፈጥሮ በራሷ የእግዚአብሔርን መኖር ጥርጣሬ ውስጥ

ትከተዋለች» ይላል:: ዳርው በመቀጠል:- «በእዚህ እምነት ገፍተን እግዚአብሔር የለም ካልን ደግሞ የምናየው ሕይወት ሁሉ የድንገተኛ ክስተት ውጤት ሊሆን ነው:: ስለዚህም ሰይጣንን የፈጠረው የራሳችን ምርጫ ይሆናል» በማለት ይናገራል::

እግዚአብሔር አለ በእርሱም እናምናለን የሚሉት ደግሞ ይህን የሰይጣን ሃሣብ ሲያጣጥሉት:- «ሰይጣንን በምርጫህ የምትከተለው ከሆነ ይህን በነፃ የመምረጥ መብት የሰጠህ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቅ ይገባል:: እግዚአብሔርን እናውቀው ዘንድ በክፉና በበጎ መካከል በነፃነት ሰቆናል:: እንግዲህ የሰይጣንን አሠራር የማያውቀው ሰው ሰይጣን የለም ይላል» በማለት ይከራከራሉ::

ሪክ ሮድስ ደግሞ "How Can a Good God Allow Evil" በሚለው መጣጥፉ ይህንኑ ሃሣብ ሲያጠናክር እንዲህ ይላል:- «ስለ ሰይጣን እንዲህ ዓይነቱን የፍልስፍና ትንታኔ የምንሰማው አሁን ስለ እግዚአብሔር ካለን እውቀት አናሳነት የመነጨ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን መረዳት ከችሎታችን በላይ ስለሆነብን ነው... ህፃን ልጅ አባቱ ይህን አድርግ ያንን ደግሞ አታድርግ የሚልበትን ምክንያት ህፃኑ ሁልጊዜ አይረዳውምና» በማለት አስፍሯል::

በሚያምኑትና በማያምኑት መካከል ክርክሩ በሰፋ ቁጥር የክፉና የበጐ ምንነት እየጠፋ መጥቷል:: ስለዚህም እያንዳንዱ ገጠመኛችን አንድም በረከት ይሆናል አሊያም እርግማን ነው፤ አንድም የእግዚአብሔር ሥራ ካልሆነም የሰይጣን ነው... እግዚአብሔር ኖረም አልኖረም በክፉና በበጐ ኃይላት ምህረት ሥር የምንገኝ ነን:: አላን ዋትስ የተባለው ፈላስፋ:- «ይህ ዓይነቱ ክርክር በፅኑ የተስፋ መቁረጥ ስሜት የተሞላ ግጭት ነው፤ ምክንያቱም ክፉ ከሌለ በጐ አይኖርም፤ በጎም ከሌለ ክፉ አይኖርም:: ሸለቆውን አስወግደን ተራራውን ለማስቀረት እየሞከርን ይመስለኛል...» ብሏል::

ዋትስ ይኸንኑ ሃሣብ በምሳሌ አስቀምጦታል:- «ክፉና በጐ ሁለት



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ተቃራኒ ጫፎች ነገር ግን የአንድ ነገር ውጤቶች ናቸው:: የሁለቱ ልዩነት የጉላ ነው:: የአንድ ልምጭ ሁለት ጫፍን ልብ ይሏል:: የሁለቱ ልዩነት ሰፊ ነው:: የሚገኙት ግን በአንድ ነገር ላይ ነው::... በልዩነታቸው ውስጥ አንድነት አለ... በአንድነታቸው ደግሞ ልዩነት» ይላል::

የ18ኛው ክ.ዘ. ታሪክ ፈላስፋ ሞሪስ ለመሞት ሰዓታት በቀሩትና በአልጋው ላይ ሆኖ በሚያጣጥርበት ወቅት በእግዚአብሔር አማኝ የነበረው ጓደኛው ከመሞቱ በፊት ሰይጣንን በአንደበቱ እንዲክድ መከረው:: ሞሪስም:- «አሁን ከጀው ከሞትኩ በኋላ ገሃነም ብሄድ ለሰይጣን ምን እመልሳለሁ? ወዳጄ ሆይ! ለጊዜው የት እንደምሄድ ስለማላውቅ በአንደበቴ ማንንም አልክድም» በማለት መልሶለታል::

ከ1632-77 የኖረው ታላቁ የደች ፈላስፋ ቤንዲክት ስፒኖዛ ስለ ክፉና በጎ ሲናገር:- «ሰው የሚፈልገው ነገር ሲኖር መልካም፤ የማይፈልገው ሲሆን ደግሞ ክፉ ይለዋል:: እግዚአብሔር ፍፁምና አንዳች ፍላጐት የሌለው አምላክ እንደሆነ ደግሞ እናውቃለን [God is perfect and has no needs] ...

«እንግዲህ እግዚአብሔር ፍፁም ከሆነ ፍላጐትም ከሌለው በእሱ ዘንድ ክፉና በጐ የሚባል ነገር የለም ማለት ነው:: በአጭሩ እግዚአብሔር ዘንድ የሌለው ነገር በሰው ዘንድ ከተገኘ የተፈጠረው በሰው ነው ማለት ነው:: ስለዚህም የሰው ፈጣሪ እግዚአብሔር፤ የሰይጣን ፈጣሪ ደግሞ ሰው መሆኑ ነው...» ብሏል::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# «የማልጠራጠረው 'መጠራጠር መቻሌን' ብቻ ነው»

አንድ ወዳጄ ይኸን ጠየቀኝ... «ከብዙ ዓመታት በፊት የነበረው ቁመናህ፣ ንግግርህ፣ መልክህ፣ እውቀትህ፣ ፀባይህ... በሙሉ ዛሬ የለም:: ከትናንቱ ማንነትህ ዛሬ የቀረው ስምህ ጲላጦስ ብቻ ነው:: ታዲያ ትናንት የነበረው ጲላጦስ ዛሬ ከሌለ፤ የዛሬው ጲላጦስ ትናንት አልነበረም ማለት ነው?»

«መቼም ማንኛውም ፍጡር በለውጥ ውስጥ ያልፍ ዘንድ የግድ ነው:: የትናንቱ ጲላጦስም አደገ፣ ተማረ፣ ተለወጠ፣ ገዘፈ...» በማለት መለስኩለት::

«አየህ! የትናንቱ ጲላጦስ ዛሬ ከተለወጠ የትናንቱ ዛሬ የለም ማለት ነው:: ዛሬ የምናየው አዲስ ጲላጦስ ነው... የትናንቱ ጲላጦስ መኖር እውነት ቢሆን ኖሮ ዛሬ አይለወጥም ነበር» አለኝ::

ወዳጄን ጠየቅኩት:- «ታዲያ እውነተኛው ጲላጦስ የትናንቱ ነው ወይስ የዛሬው?»

«ስለሁለቱም እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም:: ምክንያቱም የዛሬው ጲላጦስ ደግሞ ነገ አይኖርምና...» በማለት መለሰልኝ::

* * *

ከፍልስፍና አባቶች አንዱ የሆነውን ፕሌቶን በቅድሚያ እንመልከት...



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

«ከጓደኛህ ጋር በመንገድ ስትሄድ ዝናብ መዝነብ ይጀምራል:: በዚህ ጊዜ አንተ መሮጥ ትጀምራለህ፤ ነገር ግን ጓደኛህ እንዳልተከተለህ ተረድተህ ፊትህን ስታዞር እሱ ከእርምጃው ትንሽ ፍጥነት እንኳን ሳይጨምር በመንገዱ ላይ ነው:: በሁኔታው ብትገረምም ዝናብ እየመታው የማይሮጥበትን ምክንያት ቆም ብለህ መጠየቅህ አይቀርም:: ታዲያ ጓደኛህ... «የትኛው ዝናብ?» በማለት ቢጠይቅህ ጓደኛዬ አብዷል ብለህ ልትደነግጥ ትችላለህ::

«በአይንህ የምታየው፣ በላይህ ላይ ሲወርድ የሚሰማህ ዝናብ...' በማለት ልታብራራለት ስትሞክር... 'ዝናብ ለመዝነቡ እርግጠኛ የሆንከው በስሜትህ ስለታመንክ ብቻ ነው:: ስሜት ደግሞ የእውነት መሠረት አይደለም' ይልሀል:: ይኸን ጊዜ ወዳጅህን ወደ አእምሮ ሐኪም የመውሰጃው ጊዜ እንደተቃረበ ታስባለህ::»

የፕሌቶ ነጥብ እንግዲህ እዚህ ጋ ሲያጠነጥን «የምናውቀውን ያወቅነው፣ ያወቅነውንም እውነት ነው በማለት የምናምነው በስሜት ሕዋሳችን ምክንያት ነው:: ይኸም 'ማየት ማመን ነው' እንደማለት ይሆናል::» የምታየውን ለማመን ግን መረዳት (Perception) ያስፈልጋል::

በዚህ እሳቤ ላይ ስንመሰረት ጥንታዊው የግሪክ ፍልስፍና... «እግዚአብሔር ከሌለ ሰው ለራሱ እግዚአብሔር ይሆናል፤ እውነት ከሌለ ደግሞ ሰው የራሱን እውነት ይፈጥራል» ይለናል:: እንግዲህ እውነት ለእያንዳንዱ ሰው አንፃራዊ (relative) ልትሆን ነው::

ከ1592-1650 የኖረውን ታላቁን የፈረንሣይ ፈላስፋና የሒሣብ ሊቅ ሬኔ ዴካርትን ለዛሬ በስፋት እንመልከት:: ይኸ ሰው የብዙ እውቀት ባለቤት ከመሆኑም በላይ የዘመናዊ ፍልስፍና አባት በመባል ይታወቃል:: ዴካርት ነገሮች መኖራቸውን ለማወቅና ለመረዳት ብሎም ለማመን መጀመሪያ «እንጠራጠር» ዘንድ የግድ ነው ይለናል:: «ለምሳሌ የሒሣብ ስሌት ስትሰራ አይንህን፣ አፍንጫህን ወይም ሌላው የስሜት ሕዋስህን ሳይሆን የምትጠቀመው 'ማሰብ' ብቻ ነው... ስለዚህ ለማንኛውም ነገር



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

የእውነትነት መሠረቱ 'ማሰብ' (Reason) ነው» ይሉናል::

ከዚህ በመነሳት አእምሮውን 'እስከዛሬ' የሞላውን ነገር ጠራርጎ ሊያስወጣና ከባዶ አእምሮ ሊነሳ ወሰነ:: መነሻውንም ሁሉን ነገር መጠራጠር አደረገ:: ይኸንንም የመጠራጠር ሂደት 'Systematic Doubt' በማለት ጠራው:: በአጭሩ «ልትጠራጠር የምትችለውን ነገር ሁሉ መጠራጠር» እንደማለት ሲሆን ይኸም በሌላ አገላለፅ «በምድር ላይ የምታምነው ነገር ስለሌለ ሁሉንም መጠርጠር» እንደማለት ነው::

አንድ ብርዳማ የክረምት ቀን ዴካርት በስቶቭ የሞቀ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ ለአንድ ሙሉ ቀን የማይታሰበውን ሲያስብ፣ የማይጠረጠረውንም ሲጠረጥር ዋለ:: በዚያ ቀን እጅግ አድርጎ ካሰበበት ነገር ውስጥ 'ሰው የሚባል ነገር አለ?' ... 'ይኸስ የምናየው ዓለም እውነት ነው?' የሚሉት ይገኙበታል:: ራሱን እየጠየቀም ለራሱ መልስ ሰጠ::

ለነገሩ ጥያቄውን ሲሰሙት የማይረባ ሊመስል ይችላል:: ሁላችንም እንዳለን (እንደምንኖር) እናውቃለን:: «እናውቃለን» ስንል ለማወቃችን ምን እርግጠኛ አደረገን የሚለው ጥያቄ መነሳቱ ግን አይቀሬ ይሆናል:: ኖረናል የምንለውስ በምን መንገድ ነው? ተፈጥሮአችንስ ምንድነው? ተፈጥሮስ አለን? አሁን አንተ (የእኔ አንባቢ) መኖርህን በማስረጃ ልታረጋግጥልኝ ትችላለህ? ቀላል አይመስለኝም!

ብዙዎች ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተምረው፣ ዩኒቨርስቲውንም ጨርሰው፣ የምሁር ካባቸውንም ለብሰው... ነገር ግን መኖራችሁን በማስረጃ አረጋግጡ ሲባሉ የሚናገሩት ይጠፋቸዋል:: አንዳንዶቹም ማስረጃቸው የስሜት ሕዋሳቸው ይሆንና:- «ራሴን በአይኔ ከአየሁት አለሁ ማለት ነው» የሚል መልስ ይሰጣሉ:: እንግዲህ ዴካርት እነዚህንና መሰል ሁኔታዎችን አሰበና ይህችን ተመልከቱ አለን:-

- «በእርግጥ ራስህን በአይንህ ማየት ትችላለህ:: አንድ ዱላ ውሃ ውስጥ ሲሰምጥ አይተህ ታውቃለህ?» በማለት ጠየቀ::

- «አዎን አይቻለሁ...»



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

- «ዱላው ውሃ ውስጥ ሲገባ ምን መስሎ ይታይሃል?»

- «ከወገቡ የታጠፈ ይመስላል...»

- «ዱላው በእርግጥ ከወገቡ ታጥፏል?»

- «አልታጠፈም፤ ቀጥ ያለ ነው።»

- «ታዲያ ልክ እንደዱላው አንተም ራስህን ስታይ የምታየው ነገር ሐሰት ሊሆን አይችልም?»

- «ሊሆን አይችልም!»

- «ዱላው ከወገቡ የታጠፈ ሲመስል አይተሃል፤ ነገር ግን ያየኸው ሐሰት ነው?»

- «ዴካርት የምትለኝ ነገር በጣም የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ዱላውን ከውሃው አውጥቼ በእጄ ስደብሰው ቀጥ ያለ መሆኑን አውቃለሁና...»

- «ይኸ ማለት ደግሞ በዓይንህ ከምታየው ይልቅ በእጅህ የምትነካውን የበለጠ ታምናለህ ማለት ነው?»

- «ይህን የሚያስረዳማ የፊዚክስ ሕግ አለ!»

- «በሌላ አባባል በአይንህ የምታያቸው ነገሮች ሐሰት እንደሆኑ የሚያስረዳ ሕግ አለ ማለት ነው። ስለዚህ 'አለሁ ብለህ አንተ ስለራስህ የምታምነውን ነገር' ይህ ሕግ ጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል ማለት ነው?»

- «ምናልባት።»

- «እንግዲህ ለመኖርህ እርግጠኛ አይደለህም፤ እርግጠኛ ከሆንክ ደግሞ አንተ ምንድነህ?»

- «እኔኮ እንደአንድ ዱላ አይደለሁም። እንደዚያ ከሆንኩ የማየውና የሚሰማኝ እርስ በእርሱ ይጋጫል። ነገር ግን እኔ እኔነቴን ማየት ብቻ አይደለም፤ የማየውም እኔነቴ ይሰማኛል...»

- «እኔነቴን እኔነቴ ይሰማዋል?»

- «በትክክል!»

- «'እኔነቴ ይሰማኛል' ማለት ምን ማለት ነው?»

- «አልገባኝም...»



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

- «እንግዲህ የሚሰማህ እጅህ፣ እግርህ ወይም ፊትህ ይሆናል፤ ያ አንድ ነገር ነው። እኔነት ግን ምንድነው? እኔነት አንድ እጅ ወይም አንድ እግር ነው? እንደዚያም ከሆነ እሱም ሳይኖርህ እንዳለህ ሆኖ ሊሰማህ እንደሚችል አታውቅም? ለምሳሌ በጦርነት ወቅት እግሩን ቆስሎ የተቆረጠ ወታደር የእግሩ መቆረጥ ሳይነገረው በፊት እግሬን አመመኝ በማለት ይጮኻል። ነገር ግን እግሩ የለም። ስለዚህ ወታደሩ ይጮኽ የነበረው በሌለው ነገር ነው።»

- «ሊሆን ይችላል፤ እኔ ግን ራሴን እንደማየው፣ ያየሁት እኔነቴም እንደሚሰማኝ አውቃለሁ...»

- «ሕልም አልመህ ታውቃለህ?»

- «ብዙ ጊዜ።»

- «በሕልም ሰዓት አንድ ነገር ታያለህ፤ ይሰማሃልም?»

- «ትክክል።»

- «እንግዲህ በሕልም ያየኸው፣ የተሰማኽም ነገር ከእንቅልፍህ ስትነቃ ግን ውሸት ነው፤ ወይም የለም!»

- «በእርግጥ የለም።»

- «ስለዚህ በሕልምህ ለማየት ከቻልክና፣ ስሜትህም ሊሰማው ከቻለ አሁንስ እያለምክ አለመሆኑን ምን እርግጠኛ አደረገኽ? አሁን እኔን የምታየኝና ስናገር የምትሰማኝስ በሕልምህ ሊሆን አይችልም...?»

- «አሁን መጠራጠር ጀመርኩ።»

- «አንድ መጠራጠር የማትችለው ነገር መኖሩን ግን አትዘንጋ። እሱም መጠራጠር መቻልህን ነው። በመጠራጠራችን እየተጠራጠርን እንገፋለን፤ ከመጠራጠር የሚያወጣን ምንም ነገር የለምና።»

- «እሱማ ምን ጥርጥር አለው!»

- «መጠራጠር ደግሞ ማሰብ ነው። መጠራጠርንም ሆነ ማሰብን ማስወገድ አይቻልም፤ ስለዚህ 'ስለማስብ አለሁ' [I think, therefore I am]፤ ማሰብ ይቀጥላል፤ ማሰብ ደግሞ የሚኖረው የሚያስብ ሲኖር



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ነው፤ ስለራሴ ምንም ነገር እርግጠኛ መሆን ባልችል እንኳን መጠራጠር (ማሰብ) የምችል ነገር እንደሆንኩ እርግጠኛ ሆኛለሁ:: ያንን መጠራጠር ካልቻልኩ ደግሞ በእርግጠኝነት መኖሬን አውቄዋለሁ ማለት ነው:: ስለዚህ ሌላውን ነገር ለማወቅ ጉዞ የምጀምረው ከዚህ በመነሳት ይሆናል::»

- «በእርግጥ ዴካርት ድንቅ ነገር አሁን አገኘህ!»

ዴካርት ራሱን እየጠየቀና ለራሱም እየመለሰ ሁሉን ነገር ሲጠርጠር ቆይቶ አንድ ነገር መካድ ያልቻለው መጠራጠር መቻሉን ነበር:: ስለዚህም «መጠራጠር ከቻልኩ ማሰብ የምችል ፍጡር ነኝ» አለ:: ዴካርት ብዙ ጊዜ ሲናገር:- «እንዴ ወደ ዓለም መጥተናል ብለን የመጣንበት ዓለም ላይ ለመኖራችን እርግጠኛ ሳንሆን መቀመጥ የለብንም» ይላል:: «የሰው ተፈጥሮ ማሰብ ነው፤ ስለዚህም ሰው የሚያስብ ነገር ነው... ይኽ ማሰብ ደግሞ የሚገኘው በስሜት ሳይሆን ውስጥን በማየትና በመመርመር ነው...» የሚለው ዴካርት የመጨረሻ ሐሣቡ በዚህ ዙሪያ ሲያጠነጥን:- «የእኔ መኖር ከማሰብ ጋር ብቻ የተገናኘ ነው...:: 'እግዚአብሔር አለ፣ ይኽ ዓለም አለ፣ ሰው አለ... ወዘተ' የሚለውን ማሰብ የምጀምረው ግን ከዚህ በኋላ ነው» በማለት ተናገረ::

በዚህ የዴካርት ፍልስፍናና ትምህርት ተስበው ከነበሩት ውስጥ የስዊድኗ ንግሥት ክሪስቲና ይገኙበታል:: «ብዙ ነገር እየተጠራጠርኩ ነውና መጥተህ አስተምረኝ» በማለት ንግሥቷ ደጋግመው ለዴካርት መልዕክት ቢልኩለትም እስከ 1649 ዓ.ም. ድረስ ፍቃደኛ ሳይሆን ተቀመጠ:: በመጨረሻ ግን በዚያው ዓመት ሐሣቡን ለምን እንደለወጠ በውል በማይታወቅ ሁኔታ ወደ ስዊድን በመሄድ ንግስቷን ማስተማር ጀምሮ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን:: በጠዋት ከእንቅልፍ የመነሳቱ ነገር ሞቱ የነበረው ዴካርት ንግስቷን ለማስተማር በገባው ግዴታ መሠረት በማለዳ ወደ ቤተ መንግሥት መሄድ ይገባው ነበር:: በዚህም ግዴታው ጠዋት ጠዋት እየተነሣ ወደ ንግስቲቱ ዘንድ በሚያደርገው የእግር ጉዞ በቅዝቃዜ ምክንያት በሚመጣ የPneumonia በሽታ በ53



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ዓመቱ በ1649 ዓ.ም. ሞተ:: ዕድሜውን በሙሉ የራሱን መኖር ሲጠራጠር ለኖረው ዴካርት ሞት ብዙም ለውጥ የሚያመጣበት አይመስለኝም::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# የጥበብ መጀመሪያ አስማት መሥራት ነው

ጥንታዊው ሰው ዓለምን ሞልተዋታል በሚባሉት መናፍስት ዘንድ ሞገስ ያገኝና እርዳታቸውም ይቸረው ዘንድ የማያደርገው ነገር እንዳልነበር ታሪክ ይነግረናል:: ሬናክ የተባለ ፈላስፋ "A History of Religion" በሚለው መጽሐፉ አስማትን :- «በመንፈስ የሚኖረው የልዕለ ኃያል አምላክ (Animism) ስትራቴጂ ነው» ይለናል:: አስማተኛ ወይም መተተኛ ምንድነው? ቢያንስ ለቃሉ እንግዳ አይደለንምና በአስማት ታሪክ ዙሪያ ትንሽ ልወርውር::

በጥንት ዘመን ዝናብ ይዘንብ ዘንድ ዋናው አስማተኛ በሌሊት ዛፍ ላይ ይወጣና ውሃ ወደ ምድር ያፈስ ነበር ይባላል:: ታዲያ በማግስቱ የሃገሬው ሕዝብ ውሃው በፈሰሰበት ዙሪያ ቆሞ ከሰማይ ዝናብ ይጠብቅ ነበር:: እስከዛሬ ድረስ ባባልካን አካባቢዎችና እንዲሁም በጀርመን የገጠር ሥፍራዎች ዝናብ መዝነብ ካለበት ጊዜ ከዘገየ አንዲት ወጣት ሴት ልብሷ ከገላዋ ላይ ተገፎ ራቁቷን በአደባባይ ትቆምና በላይዋ ላይ አስማተኞች ውሃ እንደሚያፈሱ ሬናክ ከላይ በጠቀስነው መጽሐፉ አስፍሮት እናገኛለን::

በአንዳንድ የአፍሪካ ሃገሮች ደግሞ የድርቅ አደጋ ሲያንዣብብ ሚሲዮናዊ ይፈለግና ጥላውን ዘርግቶ በሜዳ ላይ እንዲመላለስ ያደርጉ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ነበር ይባላል:: በሱማትራ አንዲት ሴት ልጅ መውለድ ሲያቅታት ወይም መኻን ከሆነች ከእንጨት ተቀርፆ የተሠራ የሕፃን ልጅ ምስል በጭኖቿ መሀል ለቀናት ይዛ እንድትቀመጥ ትደረግ ነበር:: በዚህም መኻንነቷ ይፈወሳል፣ ትፀንሳለችም የሚል እምነት ስለነበራቸው ነው::

በባባር ደሴቶች ደግሞ መኻን ሴት ትፀንስ ዘንድ ከቀይ ሐር አሻንጉሊት ትሠራና ጡቷ ላይ እንደምታጠባ አድርጋ በመያዝ አስማተኛ ው የሚነግራትን ቃል እየደገመች ለሙሉ ቀን ስትለፈልፍ ትውል ነበር:: በነጋታውም የመንደሯ ሰዎች እንኳን ደስ አለሽ ለማለት ተሰብስበው ይመጡ ነበር:: በዚያም መኻንነቷ ያበቃል ይላሉ:: በቦርኔኦ ደሴት ነዋሪዎች ዘንድ ደግሞ አስማተኛ በጥብቅ የሚፈለግበት ሰዓት ቢኖር ሴት ልጅ በምጥ ላይ ስትሆን ነው:: በምጥ ሰዓት የሚጠራው አስማተኛ ዋና ተግባሩ ልጁ ቶሎ የሚወጣበትንና የሴቷም ሕመም የሚታገስበትን «ተዐምር» መሥራት እንደነበር ሲታወቅ ይኸንንም የሚያከናውነው ሴቷ በምጥ ወደምትጨነቅበት ክፍል በመግባት «በራሱ ቋንቋ» እየተንጕራደደ ሲፀልይ ቆይቶ ከብብቱ አንዲት ጠጠር አውጥቶ በመጣል ነው:: ከዚያ በኋላ የሴቷ የምጥ ጭንቀት እንደሚቃለል ልጁንም በደህና እንደምትገላገል ሁሉም ያምናል::

ከታሪክ እንደምንረዳው በጥንት ዘመን አብዛኛዎቹ የበሽታ ፈውሶችም ሆኑ የችግር መፍትሔዎች የሚፈለጉት ከአስማተኛ ነበር:: ሰውነቱን በእከክ የተወረሰ ሰው ተወርዋሪ ኮከብ እየተመለከተ ፊቱን ቢታጠብ እከኩ ከሰውነቱ ላይ ይረግፋል ተብሎ ይታመናል:: እከኩ ካልጠፋ ሰውየው ተወርዋሪ ኮከቡን ለመመልከት አልፈጠነም ማለት ነው:: በመካከለኛው ዘመን የነበሩ ሰዎች ጠላታቸውን ለመግደል ሲፈልጉ ምስሉን ከንብ ሰም ይሠሩና በጦር ይወጉት ነበር ይባላል:: ጠላታቸውም በዚያ ቅፅበት ባለበት ቦታ ይሞታል ብለው ያምናሉ:: (በእኛ ሃገር ጥላ ወጊ ከሚባለው ጋር በመጠኑ ይመሳሰላል::) ዛሬ ድረስ ታዲያ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች የሚጠሉትን ሰው ምስል ከሰም ሰርቶ ማቃጠል



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ሰውዬውን ይገድለዋል ተብሎ ይታመንበታል:: ፔሩዎች ይህን ድርጊት ሲፈፅሙ «ነፍስን ማቃጠል» (burning the soul) በማለት እንደሚጠሩት ሬናክ በመጽሐፉ አስፍሮታል::

ብዙዎች አስማትን የሳይንስ አባት ነው ይላሉ:: አስማተኛው አስማቱን በሚያደርግበት ወቅት ካልተሳካለት መከራው በእሱ ላይ ዞሮ መምጣቱ አይቀሬ ነው፤ ይሁንና ከአብዛኛው የአስማት ሥራ በአጋጣሚ የሚሳካው አንዱ ብቻ ሲሆን ይኸም እጅግ ከበዛው አለመሳካት ይልቅ ጐልቶ የመሰማት ዕድል እንደሚያገኝ በጉዳዩ ዙሪያ የረዥም ዓመታት ጥናት ያደረጉት ምሁራን ይናገራሉ:: እንደምሁራኑ አስተያየት አብዛኞቹ አስማተኞች የአንድን ነገር ምክንያትና ውጤት ለመረዳት ከዚያም አልፎ የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት የሚሞክሩት ተፈጥሮአዊ ዘዴ በአስማታዊ ድርጊታቸው ውስጥ ጥበብን የማግኛ መንገዳቸው ይሆን ነበር:: በዚህም ጥበባቸው የአማልክትን ሥራ በምድር ላይ እንደሚቆጣጠሩ ተደርገው ይወሰዱ እንደነበር ከታሪክ ስንረዳ ከብዙዎቹ አስማተኞች ውስጥም አንዳንዶቹ ተዐምር አድራጊዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሕክምና ባለሞያዎች ሌሎቹ ደግሞ የከዋክብትና የጠፈር ሳይንቲስቶች ለመሆን በቅተዋል:: ዊል ዱራንት "The Pleasure of Philosophy" በሚለው መጽሐፉ ይኸንኑ ሲገልፅ:- «የዛሬዎቹ የዓለማችን ሳይንቲስቶች የምርምር ውጤት በትናንቱ አስማተኞች ግኝት ላይ የተመሠረተ ነው... ስለዚህም ሃይማኖትና ሳይንስ የፈለቁት ከአስማት ምድር ነው» ይሉናል:: በዱራንት አባባል መሠረት የጥበብ መጀመሪያ አስማት መሥራት ሊሆን ነው::

ስለፀሐይና ጨረቃ፣ ስለምድርና በላይዋ ላይ ስለሰፈረው ፍጡር... በማሰብ ነገሮችን ሁሉ ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር ለማቆራኘት የጥረቱ ጀማሪዎችና መሠረት ጣዮች አስማተኞች ነበሩ::

ከዚህ በመነሳት በአንዳንድ ሃገሮች የሚገኙ አስማተኞች ጥበባቸውና ችሎታቸው እጅግ ገኖ የወጣ ከመሆኑ የተነሣ አምላካቸውን ለማሸነፍ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ሙከራ አድርገው ባይሳካላቸው እንኳን ከእነሱ ደካማነት ሳይሆን ከአምላካቸው ግትርነት ተደርጐ ይወስዱላቸው እንደነበር ጥንታዊ ታሪክ ይነግረናል:: በአውሬ አደን ላይ የተሰማሩ ግሪካውያን ወጣቶች አደናቸው አልሰምር ሲል ወደአስማተኛ በመሄድ ለአምላካቸው ምስል አድርገው የሠሩትን ቅርፅ እንዲገርፍላቸው ያደርጉ ነበር ይባላል:: በዚህም አምላካቸው ግርፊያው ተሰምቶት የአደን አውሬ እንደሚጠራላቸው ያምኑ ነበር:: የጣሊያን አሣ አጥማጆች ደግሞ ወጥመዳቸው ባሕሩ ውስጥ ተልኮ ባዶውን ከተመለሰ በአካባቢው አንዲት ድንግል ሴት ይፈልጉና ቅርጿን ከጭቃ በመሥራት ወደ ባህሩ ይጥሉ እንደነበር ሀብስ የተባለው ፈላስፋ "Morals in Evolution" በተባለው መጽሐፉ አስፍሮት እናገኘለን::

ጥንታዊ ቻይናውያን ደግሞ ከድንጋይ ሰርተው የሚሰግዱለት አምላካቸው (orisons) ፀሎታቸውን አልሰማ ሲል አውራ ጐዳና ላይ እየጐተቱ ያወጡትና:- «አንተ የውሻ መንፈስ... የሚያምር ቤተመቅደስ ሰርተን አስቀመጥንህ፣ ጣፋጭ ምግቦችን ሰርተን አመጣንልህ፣ መስዋዕትህን ዕለት ዕለት አቀረብን... አንተ ግን ምስጋና ቢስ ነህ» በማለት ሲሰድቡት፣ ሲያንቋሽሹትና በድንጋይም ሲወግሩት ይውላሉ::

እንግዲህ የጥንቱ ሰው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ማለፍ የግድ እየሆነበት ሲመጣ ነገሮችን ሁሉ በአጋጣሚ ወይም በዕድል መተርጐም ጀመረ:: ይኸንንም ግሪኩ *Moira* ይለዋል:: ይኸ ሁኔታ በግሪክ ሃይማኖት የልዩነት ድንበር መሠረተና አማልክትና ሰው ለሁለት ተከፈሉ:: በዚህም አንዱ ወገን ወደአምላኩ ጉዞውን ሲጀምር የቀረው ደግሞ ጉዞውን ወደሳይንስ አቀና::

እንግዲህ በዚህ አካሄድ ስንመዝነው አስማት (Magic) ለሳይንስና ድራማ ብቻ ሳይሆን ለሃይማኖታዊ አምልኮ፣ ለመስዋዕትና ለፀሎትም በሩን የከፈተና እንዲያውም እነዚህ ድርጊቶች የተወሰዱት ከአስማተኝነት ልምምዶች ለመሆናቸው ማረጋገጫ ይሆነናል:: ለምሳሌ አሁን በየትኛ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ውም ሃይማኖት ሲከናወኑ የምናያቸው የበሉት ልምምዶች የተወሰዱት የጥንት ሰው አስማትን ለማከናወን ከሚያደርገው እንቅስቃሴና ንግግር ጋር በእጅጉ የተመሳሰለ ሆኖ እናገኘዋለን:: ዊል ዱራንት ይህንኑ አስመልክቶ እንዳሰፈረው:- «መልካም የሆንና ወደእኔ ይመጣል ብለህ የምታስበው ማንኛውም ዕቃ ወይም ጣዖት (Talismans)፣ በአፍህ የምታደርገው ቡራኬ (Benediction)፣ እንዲሁም እርግማን (Malediction)... ወዘተ በሙሉ የጥንቱ አስማት ውጤቶች ናቸው» ብሏል::

እያንዳንዱ ትውልድ በእያንዳንዱ ዓመት የሚያስጨንቀው ነገር ቢኖር የተሻለ የእህል ምርትን መሰብሰብ ነው:: የጥንቱም ሰው ይኸው ሐሣብ ሲያስጨንቀው እርሻውን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን ዕውቀቱም አጋጣሚውም ስላልነበረው ዓመታትን ያስቆጠረው በአስማት መሬትን በማባበል ነበር:: በዚህም ዘር የሚዘራበትን ወቅት ጠብቆ «የወንድ ብልት የማምለኪያ ፌስቲቫል» (Phallic Festival) ያደርግ ነበር:: ይህን ፌስቲቫል የሚያደርግበት ዋነኛ ምክንያት የወንዱ ብልት ዋነኛ የመራቢያ መሣሪያ ሆኖ ስለሚታመን መሬትም እንዲሁ ዘሯን ትሰጠናለች በሚል እምነት ላይ ተመስርቶ ነው::

የሰው ልጅ የሕይወቱ መሠረት ለሆነችው መሬት ያደርግ የነበረው አስማታዊ አምልኮ ከጥንታዊ የሃይማኖት አምልኮዎች ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነበር:: በዚህም ጥንታዊ አምልኮ መሬት የሕፃን ወይም የወጣት ደም መስዋዕት ይቀርብላት ነበር፤ በመቀጠል ደግሞ የሽማግሌ ደም ሲፈስላት ዓመታት ተቆጠሩ፤ ይኸም ደግሞ ሲቀር የእንስሳት ደም ማፍሰስ ተጀመረ:: ይኸ ሁሉ ድርጊት እንግዲህ «ለመሬት መንፈስ» መሆኑ ነው:: በዚህም ተደስታ መሬት ታበቅላለች ማለት ነው::

ለምሳሌ በኢክዋዶር የሚገኙ ሕንዶች እህል የሚዘሩበት ወቅት ሲደርስ በመካከላቸው ዕጣ ይጥሉና ዕጣው የወጣበትን ሰው በማረድ ደሙንና ልቡን ለምድር መንፈስ ያቀርቡ እንደነበር የተለያዩ የታሪክ መፃሕፍት ዘግበዋል:: የቤንጋል ሕንዶች ደግሞ ለምድር መስዋዕት



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

በማድረግ ያቀርቡ የነበረው የወንጀለኛን ሰው ደም ነበር:: የጥንት አቴናውያን በመካከላቸው ወረርሽኝ በሽታ ሲገባ አሊያም ድርቅ ሲከሰት ሁለት ወንጀለኞችን በማረድ ወንዱን የነገዱ ወንዶች፤ ሴቷን ደግሞ የነገዱ ሴቶች ወኪል በማድረግ መስዋዕት ያቀርቡ እንደነበር ሲታወቅ ይኸም የአንዱን ኃጢአት የማስተሰርይ (vicarious attonement) ሐሣብ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንደመጣ እንረዳለን::

ለምሳሌ ኃጢአትን የማስተሰረይ አምልኮ በጥንታዊቷ የአቴና ታርጂኒያውያን ዘንድ የሚከናወነው ሁለት ፍየሎችን ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ በማቆም ኃጢአት የሰራ ሰው በድንጋይ እንዲወግራቸው በማድረግ ሲሆን ፍየሎቹ ሲሞቱም የሰዎቹ ኃጢአት አብሮ እንደሞተ ያምኑ ነበር:: ዊል ዱራንት ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፉ «በአንዳንድ የዓለማችን ክፍሎች ከጥንት ጀምሮ የሰው ሥጋን መብላትና ደሙንም መጠጣት ኃጢአትን ያስተሰርያል በሚል እምነት ይከናወን እንደነበር ሲታወቅ በተለይ በጥንታዊ የሜክሲኮ ዘሮች ይህ ለዓመታት ሲከናወን ቆይቶ ከጊዜ በኋላ ግን ድርጊቱን ለማስቀም ከስንዴ ሊጥ የተሰራ አምላክ አቁመው አስማተኛው ለእሱ ከደገመለት በኋላ ይበሉት ነበር...» በማለት አስፍሯል::

ዱራንት በሰነዘረው ሐሣብ የአስማትን ጉዳይ ላብቃ:- «የሰው ልጅ አስፈሪው ኋላቀርነቱ አልፎ ከሰው መስዋዕት ወደ እንስሳ መስዋዕት ሲሸጋገር ለማየታችን መልካም ምሳሌ የሚሆነን አብርሃም ይስሐቅን ለመስዋዕት ካዘጋጀ በኋላ በበግ መተካቱ ነበር» ብሏል::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# የነፍስ ሙዚቃ የሥጋ ልምምድ ውጤት ነው

ከሞት በኋላ የሚኖረን «ሕይወት» የሚያሳስበን ስንቶቻችን እን... ቢያንስ ከሞት በኋላ የሥጋ ጉዳይ እንደሚያከትምለት የጋራ ግ... ይኖረናል ብዬ አምናለሁና የሚያነጋግረን ቀሪ ጉዳይ ነፍስ ትሆናለች... በዚህ ምዕራፍ ደግሞ በፈላስፎቹ ዓይን ነፍስን እንመልከታት:: ነ... (Soul) አንዳንድ ጊዜ መንፈስ (spirit) በሚል መጠሪያም ትታወቃለች... መገኛዋም ሕይወት ባለው ነገር ውስጥ ብቻ ነው ይላሉ:: በዚህ አካ... ሥጋ አለ፤ ሥጋው ሕይወት አለው፤ ሕይወት ደግሞ በውስጡ ነ... ይዟል:: የሰውን አፈጣጠር ከመጀመሪያው እንመርምር:-

*«እግዚአብሔርም አለ:- ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአ... እንፍጠር»* (ዘፍጥ. 1:26)

በዚህ አካሄድ እግዚአብሔር መልክ ነበረው፤ የእግዚአብሔር መ... ደግሞ መንፈስ ነው:: ስለዚህም ሰው መንፈስ ነበር:: እግዚአብሔር ግ... የፈጠረውን መንፈስ በዚያው በቃህ አላለውም:: ከአፈር አቡክቶ አ... የሰጠውን ቅርፅ ሰራና በዚያ ውስጥ አኖረው::

*«እግዚአብሔርም አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው...»* (ዘፍጥ. 2...)

ነገር ግን ሰው አሁንም ለእግዚአብሔር ተሰርቶ ያላለቀ ዕቃ ሆነበ... ምክንያቱም ሰው ሕይወት አልነበረውምና::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

«የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት...» (ዘፍጥ. 2:7)

ሰው እንደዚህ በብዙ ድካም ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ትሞታለህ ተባለ:: ሲፈጠር ጀምሮ ዘላለማዊነትን በልቡ ያኖረው ሰው «በአንተ መልክ ተፈጥሬ ከሞትኩማ የአንተን ዘላለማዊነት ጥርጣሬ ውስጥ ትከተዋለህ...» አለ::

እግዚአብሔርም እኔን የሚመስለው ነገርህ ብቻ አይሞትም አለ:: ስለዚህም ይኸች የማትሞተው ነገር አነጋጋሪ ሆነችና ዛሬ ወደ እሷ አቀናን::

አንድ ሕይወት ያለው ነገር በሕይወቱ ማብቂያ ሰዓትና ከሞተ በኋላ በሥጋው ላይ «ምንም» ለውጥ አያመጣም:: ነገሩን ግልፅ አድርጐ ለማስቀመጥ «አንድ ሰው በጠዋት ቢሞት ከሰዓት በኋላ (ነፍሱም ብትወጣ) ቅፅበታዊ ለውጥ አይመጣም::» ምክንያቱም ነፍሱ ሌላ ቦታ ብትሄድም፤ ሥጋው ግን አልሄደምና:: «ስለዚህ» ይላል ፕሌቶ «ነፍስ ለእኛ እምብዛም አስፈላጊ ያልሆነች (immaterial) ነገር ነች» ካለ በኋላ ይኼንኑ ሲያብራራ «የነፍስ አላስፈላጊነት ዋነኛ ምክንያት የምትሞት ነገር አለመሆኗ ነው» ይለናል:: የእሱ ደቀመዝሙር አሪስቶትል ደግሞ «ነፍስ ከሥጋ ተለይታ ወደ ሌላ ዓለም ተሸጋግራ መኖሯን መቀበል አስቸጋሪ ነገር ነው» ብሏል::

ከ85e-86D ከኖረው ሲሚያስ ፍልስፍና በመነሳት የነፍስ ጉዞ እንጀምር:-

ሲሚያስ:- «ሶቅራጥስ ሆይ:- አንድን የሙዚቃ መሣሪያ ክሮች ብትመታቸው (ብትጫወታቸው) የምትሰማው የተዋበ (መለኮታዊ) ድምፅ ነው:: ይኸ ድምፅ አይታይም፤ ነገር ግን ከሚታይ፣ ከሚነካ፣ ከሚጠፋ ምድራዊ ነገር ወጥቶ መጣ:: (በሥጋ /አፈር/ ውስጥ ያለ ነፍስ እንደማለት ነው::) ነፍስም እንዲሁ ነች::»

ሶቅራጥስ:- «አሁን የሙዚቃ መሣሪያው ተሰበረ፣ ወይም ክሮቹ ተበጠሱ እንበል:: በአንተ መላምት መሠረት 'መሣሪያው ቢጠፋም ድምፁ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

አይጠፋም እያልከን ነው? ነገር ግን የሙዚቃ መሣሪያው ሲሰበር ወይም ክሮቹ ሲበጠሱ ያ ድምፅ አብሮ ጠፋ:: ድምፁ ዘላለማዊ ቢሆን ኖሮ ጠፊ (ሟች) ከነበረው የሙዚቃ መሣሪያ ባህርይ ባልተጋራ ነበር:: ምክንያቱም ድምፁ የኖረው መሣሪያው እስከኖረ ድረስ ብቻ ነው...»

ሲሚያስ:- «እዚህ ላይ እኛ የፓይታጐረስ ተማሪዎች የሆንነው (ፓይታጐረስ ከሶቅራጥስ ዘመን በፊት 570?- 495? BC የኖረ ታላቅ ፈላስፋ ነበር) አንድ የምናምነው ነገር እንዳለ ደግሞ አትዘንጋ:: እንደምታውቀው ሥጋችን በሙቀትና ቅዝቃዜ፣ በእርጥበትና ድርቀት... ወዘተ ጫፎች መካከል ተወጥሮ የተያዘ ነገር ነው:: ነፍሳችን ደግሞ የሁለቱ ጫፎች ማዕከል ሆና የምታያይዝ (adjustment) ነች:: እንግዲህ ሥጋችን የተወጠረበትን ሁለት ጫፍ የምታያይዝ ነፍስ ስትሆን ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ከሙቀቱ ቅዝቃዜው አይሎ ሥጋችን ደንዝዞ ይቆይና ወደ ነበረበት ሲመለስ ነፍሳችን ግን አለች::»

ሶቅራጥስ:- የሙዚቃ ድምፅ የምትሰማው የሙዚቃ መሣሪያ ሲኖር ነው::

ሲሚያስ:- ትክክል::

ሶቅራጥስ:- በነገሮች መካከል መስማማት ይኖር ዘንድ ደግሞ በመጀመሪያ የሚስማማው ነገር መኖር የግድ ነው::

ሲሚያስ:- አዎን፤ እስማማለሁ::

ሶቅራጥስ:- ስለዚህ ነገሩ (ሥጋና ነፍስ) መስማማትን ይቀድማሉ እንጂ አይከተሉትም?

ሲሚያስ:- ልክ ብለሃል::

ሶቅራጥስ:- የአንዱ ነፍስ ከሌላው ነፍስ ይበልጣል ብለህ ታምናለህ?

ሲሚያስ:- አላምንም::

ሶቅራጥስ:- ነገር ግን የአንዱ ነፍስ ደግነትና እውቀት የሌላው ደግሞ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ስንፍናና ክፋት ሞልቶበታል?

ሲሚያስ:- እውነት ነው::

ሶቅራጥስ:- ነፍስ በሥጋ ውስጥ የሚገኝና ከሥጋ ጋርም ተስማምቶ (Harmony) የሚኖር ነገር ከሆነ በውስጡ ክፋት ወይም ደግነት እንዴት ይገኝበታል?

ሲሚያስ:- አልገባኝም::

ሶቅራጥስ:- በዚህ መንገድ ተመልከተው:: የሙዚቃው መሣሪያ ላይ ያሉት ክሮች በሚገባ ተደርድረው ሲመቱ ጥሩ ሙዚቃ ይወጣል:: እንደማይገባ ሲመቱ ደግሞ ሙዚቃው (ድምፁ) የተበላሸ ይሆናል:: ቅንነት የሞላበት ነፍስ ውስጥ የምንሰማው ድምፅ ያማረ ሲሆን፣ ክፋት የሞላበት ነፍስ ደግሞ እንደተበላሸ ሙዚቃ ክፋትን እንሰማበታለን::

ሲሚያስ:- ትክክል

ሶቅራጥስ:- ነገር ግን የአንዱ ነፍስ ከሌላው ነፍስ እንደማይበልጥ ተስማምተን ነበር እኮ?

ሲሚያስ:- በእርግጥ አይበላለጥም::

ሶቅራጥስ:- ስለዚህ በጥሩም ይሁን በመጥፎ የተቃኘ ሙዚቃ አንዱ ከሌላው ልዩነት የለውም ማለት ነው?

ሲሚያስ:- እውነት ነው::

ሶቅራጥስ:- እንግዲህ በዚህ ሁኔታ መጥፎም ሆነ ጥሩ የምንለው ሙዚቃ የለም ማለት ይሆናል?

ሲሚያስ:- ይመስለኛል::

ሶቅራጥስ:- ታዲያ በዚህ ከተስማማን መጥፎ ሙዚቃ የክፋት፤ ጥሩ ሙዚቃ ደግሞ የደግነት አድርገን በነፍስ ውስጥ እንመልከተውና ጥያቄ እናንሳ:: እንዴት አንዲት ነፍስ ከሌላው ነፍስ የበለጠ ክፋት ወይም ደግነት ልትይዝ ትችላለች?

ሲሚያስ:- የሚቻል አይመስልም::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ሶቅራጥስ፡- አንተ የምትለው ግን በተቃራኒው ነበር፡፡ 'የትኛውም ነፍስ ደግነት ካለበት ክፋት ሊኖርበት አይችልም፤ ምክንያቱም ጥዑም ዜማን ስንሰማው ጥዑም የሚያደርገው በውስጡ የተበላሸ ነገር ስለሌለ ነው' የሚል ነበር፡፡

ሲሚያስ፡- ልክ ብለሃል፡፡

ሶቅራጥስ፡- እንግዲህ ነፍስም «ነፍስ» ከሆነች ክፋት በውስጧ ሊገኝ አይችልም ማለት ነው?

ሲሚያስ፡- በተነጋገርነው መሠረት ከሆነ ትክክል ነህ፡፡

ሶቅራጥስ፡- በነፍስ ተፈጥሮ ውስጥ ሁሉም ነፍስ እኩል ከሆነ የሰው ሁሉ ነፍስ በእኩል ደረጃ ጥሩ ነው ማለት ይሆናል፡፡

ሲሚያስ፡- ይመስለኛል፡፡

ሶቅራጥስ፡- ግን ይኸ አመለካከት ትክክል ይመስልሃል? ነፍስ እንደ ጥዑም ዜማ ወይም እንደተበላሸ ድምፅ ነች ከሚለው መላምት ባንነሳ ኖሮ እኮ እዚህ መደምደሚያ ላይ አንደርስም ነበር፡፡

ሲሚያስ፡- አሁንም ትክክል ነህ፡፡

ሶቅራጥስ፡- ነገር ግን ከነፍሱ ውጭ በሌላ ነገር የሚመራ ሰው አይተህ ታውቃለህ?

ሲሚያስ፡- በፍፁም አላውቅም!

ሶቅራጥስ፡- እንግዲህ ነፍስ የሥጋን ስሜት ትታዘዛለች ወይስ ትቃረናለች? ለምሳሌ አንድ ሰው ለመጠጣት ተጠምቶ ነፍሱ ግን እንዳይጠጣ ትገፋዋለች፤ ተርቦም እንዳይበላ ታደርገዋለች (በዘመናችን እንደፆም መሆኑ ይሆን?)፤ ስለዚህ ነፍስ የሥጋን ፍላጐት ስትቃወም ታያለህ? ነገር ግን የሙዚቃውን መሣሪያ ስትመታው የተመታውን ነገር ድምፅ እንጂ እሱን ተቃርኖ ሌላ ድምፅ አያወጣም፡፡ ድምፁ ክሩን አያዝዘውም፤ ነገር ግን ድምፁ የክሩ ውጤት ይሆናል፡፡

ሲያሚስ፡- አሁን እየገባኝ ነው፡፡

ሶቅራጥስ፡- ነገር ግን ነፍስ በተቃራኒው ደግሞ ስትሰራ እናያለን፡፡



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

የተቃኘችበትን መሣሪያ ትመራዋለች፤ መምራት ብቻም አይደለም ታዝዘዋለች፤ በሕይወት አቅጣጫ ሁሉ ትቃወመዋለች፤ አንዳንድ ጊዜም ከፋ ትሆንበታለች:: ስለዚህም ነፍስን እንደተቃኘ ሙዚቃ የከሩ ውጤት አድርገህ አትመልከታት... ብዙ ጊዜ ሥጋም በነፍስ ይቃኛልና...

* * *

የሶቅራጥስ ደቀመዝሙር የነበረው ፕሌቶ መልካም ነፍስ ከክፋ ነፍስ ይልቅ እንደተቃኘች ሙዚቃ ናት ይላል:: ምክንያቱም የነፍስ ቅኝት ራስን ከመግዛት ይጀምራልና:- «የሰው ነፍስ በብቃት ደረጃ እኩል ነው፤ ነገር ግን አንዱ ነፍሱን ለክፋ ሲያስለምዳት ሌላው ደግሞ ለበጐ ያስለምዳታል:: ስለዚህም የነፍስ ሙዚቃ የሥጋ ልምምድ ውጤት ነው» ይለናል::

ጥንታውያን የግሪክ ፈላስፎች የሰው ልጅ ዕጣ በአማልክት እጅ ውስጥ ነው በሚለው ሐሣብ እስከተወሰነ ደረጃ ይስማሙበት ነበር:: ይኸውም አማልክት (በጊዜው ብዙ አማልክት ነበሩ) በሰው ነፍስ የሚያገባቸው ሰውዬው እስከ ሞተ ድረስ ብቻ ነበር:: ለዚህም ይመስላል «የሰው ልጅ ዕጣ በአማልክት እጅ መሆኗን የሚያሳዩን አማልክቱ ሞትን ለማስቆም ፍቃደኛ ባለመሆን ነው» የሚሉን::

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ750 ይኖሩ የነበሩ ግሪካውያን ሙታኖቻቸውን የሚቀብሩበት ወግና ባህል ነበራቸው:: ይኸውም አንድ ሰው ከመካከላቸው ሲሞት ጠለቅ ያለ ጉድጓድ ቆፍረው በመቅበር ከላዩ አፈር በደንብ ያለብሱት ነበር ይባላል:: የኦሊምፐስ አማልክት ሙታንን በቅርብ ካዩ ይቆጣሉ፤ በምድርም ላይ መዓት ያመጣሉ የሚለው የመጀመሪያው ጠንካራ እምነታቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ነፍስ ወደታችኛው የሙታን ዓለም እንዲወርድ ከተፈለገ ጠለቅ ብሎ ሊቀበር ይገባል የሚለው ሌላው የጊዜው እምነት ነበር::

የአቴናውያኑ የሌላ ወገን እምነት ደግሞ ለሙታን የነበራቸው



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ክብር ከፍ ማለቱ ላይ ሲሆን በዚህም ነፍስ ከሥጋ ብትለይም ማልቀስ ተገቢ አይደለም፤ ምክንያቱም ነፍስ የለቅሶ ድምፅ ከሰማች ተመልሳ ሥጋ ውስጥ ትገባለች በማለት ያምኑ ስለነበረ ነው:: ነገር ግን ሬሳው ይታጠብና ያጌጠም ልብስ ያለብሱትና ወስደው ይቀብሩታል፤ በመቃብሩ ዙሪያም ጥሩ ጥሩ ምግብና መጠጥ ያስቀምጡለታል:: ነፍስ በመቃብሩ ዙሪያ ለጥቂት ቀናት ስታንዣብብ ቆይታ ስለምትሄድ (ምናልባት እስከሳልስት ይሆናል) መሰናበቻዋን ተደስታ ትሸኝ በማለት ነበር:: ነገር ግን እስከዛሬ አብዛኞዎቹ ፈላስፎች በነፍስ ዙሪያ የሚያነሱት ጥያቄ የምትሄድበትን በማወቅ ላይ ያተኮረ ሳይሆን የምትገኝበትን ማወቅ እንደሆነ ቀርቷል:: የነፍስን አድራሻ በሌሎች ምዕራፎች እንመረምራለን::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# ቁጣ እብደት ብቻ ሣይሆን ውበትም ነው

የፕሌቶ ደቀመዝሙር የነበረው አሪስቶትል ቁጣን ሲገልፀው፡- «ማንም ሰው መቆጣት ይችላል፤ መቆጣት ቀላል ነውና:: ነገር ግን ተገቢውን ሰው፣ በተገቢው ደረጃ፣ በትክክለኛው ሰዓት፣ ለትክክለኛው ዓላማ፣ በትክክለኛው መንገድ መቆጣት ግን በማንም ሰው ውስጥ የሌለ ችሎታ ብቻ ሳይሆን የማይቻልም ነው» ብሎታል::

ታላቋ አሜሪካ እንኳን በራሷ ቀርቶ እሷን በተወዳጁትም ይደርሳል ብላ የማትጠብቀው በትር ሴፕቴምበር 11/2001 ባረፈባት ማግሥት አንድ አሜሪካዊ ወጣት፡- «አንድ ወይም ሁለት ሃገር ድምጥማጡን ልናጠፋ ይገባል» በማለት በንዴት የተንገበገበ አስተያየት በቴሌቪዥን ሲሰጥ ተደመጠ:: ነገር ግን ወጣቱ ድምጥማጥ የሚጠፋትን ሃገሮች ስም አልጠቀሰም:: የሮማው ጳጳስ ደግሞ «ፍርድ እንጂ በቀል አያስፈልግም» በማለት የአሜሪካን ቁጣ ለማብረድ ሞከሩ:: ጳጳሱ ይህን ቢሉም በፍርድና በበቀል መካከል ያለውን ልዩነት እንዲያብራሩ የጠየቃቸው ሰው አልነበረም፤ እሳቸውም ሊያብራሩ አልሞከሩም::

በዘመናችን የቁጣና የእብደት ልዩነት ብዙም የሚጋነን አይደለም የሚሉ የሳይኮሎጂ ምሁራን በብዛት እየወጡ ነው:: ይሁንና ለዛሬ ቁጣን ለይተን እንዴ በተገጠመልን የጥበብ መነፅር እንድናየው እወዳለሁ::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

መነሻችን አሜሪካዊው የሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ምሁር ዊሊያም ሀሪስ በቅርቡ:- "Restraining Rage: The Ideology of Anger Control in Classical Antiquity" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን ይኸ ምሁር «ቁጣ እብደት ብቻ ሳይሆን ውበትም ነው» ይለናል:: «ለነገሩ የቁጣ ምንጭ ሰይጣን ወይም እግዚአብሔር አይደሉም:: ለምን ቢሉ ሁለቱም ይቆጣሉና:: ስለዚህም የእኔ መቆጣት ሰይጣንንም ሆነ እግዚአብሔርን አይወክልም» ይላል ሀሪስ::

ሀሪስ በመጽሐፉ ስለቁጣ የመጀመሪያ ምሳሌው አድርጎ ያስቀመጠው ሴኔካን ነው:: ሮማዊው የስቶይሲዝም ፍልስፍና አራማጅና የንጉሡ የኔሮ መምህር የነበረው ሴኔካ ቁጣን ሲገልፅ:- «አንድን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ የሚያስነሳ ነገር ቢኖር ቁጣ ብቻ ነው» ይላል:: «ቁጣ በአንድ ሕዝብ ላይ መከራን ያመጣ ጠላት ለመበቀል የሚያነሳሳ ኃይል ነው... በአንዲት ሴት ፍቅር ተይዞ የተሰቃየ ሕዝብ የለም... ተስፋውን በገንዘብና በሀብት ላይ በአንድ ልብ የመሠረተ ሃገርም አይገኝም፣ ምክንያቱም የሀብት ምኞትም ይሁን የሴት ፍቅር ግላዊ ነውና:: ነገር ግን ቁጣ የሕዝብ የጋራ ሀብቱ ነው:: ስለዚህም የሕዝብ ቁጣ አንድና በአንድ ላይ የሚገለፅ ነው» ብሏል::

ሀሪስ በመግቢያው ይህን ካሳየን በኋላ የቁጣን ውስጣዊ ምንነት ሊያሳየን የሚነሳው በምዕራባውያን የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ላይ ተመስርቶ ነው:: «የምዕራባውያንን የሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ስንመረምር» ይላል ሀሪስ «ቁጣ በድርሰታቸው ቅድሚያውን ቦታ የሚሰጠው ሆኖ እናገኘዋለን:: ሆሜር በኢሊያድ ድርሰቱ የፀሎቱ መጀመሪያ ያደረገው «<u>የአኪለስ ቁጣ፣ ዘምሪ፣ አምልኪ</u>» በማለት ነበር ይለናል:: ስለዚህም የሥልጣኔአችን የመጀመሪያ ድርሰት የመጀመሪያው ቃል ቁጣ ሆኗል» ብሏል:: በዚህ ቁጣ ላይ የተመሰረተው የሆሜር ድርሰትም የተዋጣ ሆነ::

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ900. ዓ.ዓ. አቅራቢያ እንደተወለደ የሚገመተው አይነ ስውሩ የግሪክ ባለቅኔና ፈላስፋ ሆሜር በትክክለኛነቱ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ዓለም የተቀበለውና ተፅፎ የሚገኝ ታሪክ የሌለው ሰው ነው:: ከሄሬዶትስና ከፕሉታርክ ተፅፎ የተገኘ ነው የተባለው ባለሁለት ይዘት ያለው ታሪኩም ቢሆን በኋላ ዘመን በተደረገው ምርመራ በእነዚሁ ሰዎች እንዳልተሰራ ለማወቅ ተችሏል::

ቁጣን በድርሰቱ ለማሳየት የመጀመሪያው ሰው ነው የሚባለው ሆሜር በኢሊያድ ድርሰቱ ውስጥ በሚያሳየን የአኪለስ ቁጣ ዙሪያ ያለውን ታሪክ ሀሪስ በመጽሐፉ በሰፊው አስፍሮታል:: በመጠኑ ልቀንጭብላችሁ:-

«...ትሮይ በወቅቱ ስማቸው ገናና የሆነ ታላላቅ ጀግኖች የሚገኙ ብት ብርቱ የሆነ ጦር የነበራት ከተማ ናት:: የግሪክ ሰዎች ይቺችን ከተማ ሊወጉ እንደመጡ በዙሪያዋ የነበሩ የእስያ ሃገራት ሲሰሙ ሊረዷት ወደ እሷ መጡ:: ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት የትሮይ ንጉሥ የፕሪያም ልጅ የግሪክ ንጉሥ ሚስት የነበረችውን እሌኒ የተባለችውን ሴት ነጥቆ በመውሰዱ ምክንያት በግሪክና በትሮይ ብሎም በዙሪያዋ በነበሩ ወዳጆቿ መካከል የቆየ ቂም በመኖሩ ነበር::...

«...ጦርነቱ ተጀምሮ አንድ ጊዜ ግሪኮች እየገፉ የትሮይ ከተማ እስከምትገኝበት ግንብ ድረስ የትሮይን ጀግኖች ሲያባርሩ በሌላ ጊዜ ደግሞ ድሉ የተገላቢጦሽ ለትሮይ ሲሆን ጦርነቱ አሥር ዓመት ቆየ፤ በአሥረኛው ዓመት ግን ዩሊስ የሚባለው የግሪክ አርበኛ የትሮይን ግንብ ለመጣስ የሚያስችል መላ አመጣ:: ይኸውም በእንጨት የተቀረፀ ትልቅ ፈረስ ሰርቶ ጦር ሠራዊቱን እዚያ ውስጥ መክተት ነበር...

«...በዩሊስ እቅድ መሠረትም ፈረሱ ተሠርቶ በሌሊት የግሪክ አርበኞች ወደትሮይ ግንብ ተጠግተው በሩን እየከፈቱ ከገቡ በኋላ እንቅልፍ ወስዷቸው የተኙትን የትሮይን ሕዝቦች ፈጇቸው፤ ከተማይቱንም በእሳት አቃጠሉ::»

**ሆሜር በኢሊያድ ድርሰቱ የትሮይን መውደቅና መቃጠል ብቻ ሳይሆን በተለይ በጦርነቱ 10ኛ ዓመት ላይ የግሪኩን ጀግና የአኪለስን**



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

የቁጣ ታሪክ ሊያሳየን እንደሞከረው ሀሪስ ይነግረናል:: «ሆሜር በግጥሙ የአኪለስን ቁጣ ምንጭ ከግሪኩ የጦር አዛዥ ከአጋሜኖን ድርጊት ጋር የተያያዘ የቁጣ በቀል ነው ይለናል:: አጋሜኖን በአኪለስ ላይ ለፈፀመው ስህተት አኪለስ የግሪክን ጦር በሜዳ በትኖት እንዲሸሽ አደረገው:: የጀግና መሪው የአኪለስ ከጦር ሜዳው መውጣት ያስደነገጠው የግሪክ ጦርም መበተን ጀመረ...

«...በሽሽቱ የገፋው የግሪክ ጦርን ለማዳን አኪለስ አልፈለገም፤ ፍፃሜውን ከሩቅ ሆኖ ግን መጠበቅ ጀመረ:: የግሪክ ጦር እየተበተነ ወደ መርከቡ ለመውጣት በሚሞክርበት ጊዜ የትሮይ ሰዎች አንዱን መርከብ አቃጠሉት:: በዚህ ጊዜ ለማምለጥ መንገዱ ሁሉ የተዘጋበት የአኪለስ የልብ ጓደኛ ፓትሮክለስም በትሮይ ልዑል ሄክቶር እጅ ተገደለ::

«...የጓደኛውን መገደል የተረዳው አኪለስ በዚህ ሰዓት በትሮይ ሰዎች ላይ ቁጣው ነደደ፤ ለበቀልም ተነሣ:: የአኪለስን ወደጦር ሜዳ መመለስ የተመለከተውና በሽሽት ላይ የነበረው የግሪክ ጦርም ተበራታ... የትሮይ ሰዎችንም ማሳደድ ጀመረ:: የአኪለስ የቁጣ በቀል በመጀመሪያ ያረፈችውም በጓደኛው በፓትሮክለስ ገዳይ በልዑል ሄክቶር ላይ ነበር:: አኪለስ የጓደኛውን ደም ልዑሉን ገድሎ በመበቀል ብቻ አላቆመም:: ነገር ግን የልዑሉን ሬሣ በጓደኛው መቃብር ላይ ሦስት ጊዜ በማዞር ጣለው::» ሀሪስ በመጽሐፉ ይህን ያቀረበበት ዋነኛ ምክንያትን ሲገልፅ አሁን እስከአለንበት ዘመን ድረስ የግሪኮች ቁጣ መሠረትና ምንጭ የአኪለስ ቁጣ ተደርጐ ስለሚታመንበት እንደሆነ ያትታል::

እንደሀሪስ:- «ግሪኮች ከጥንት ጀምሮ ለአኪለስ ቁጣ እጅግ ከፍተኛ ግምት ይሰጡታል:: በአንደኛው ክ.ዘ. በሃገራት መካከል የሚነሱ ጦርነቶችና በሰው ልጅ ላይ የሚደርሱ እልቂቶችም በአኪለስና በአጋሜኖን ቁጣ ይመሰሉ ነበር» ብሏል:: አኪለስ በቁጣው ብቻ ሳይሆን በጀግንነቱም ወደር የማይገኝለት ተምሳሌት ነበር:: አኪለስን ድል ለማድረግ ፈፅሞ የማይታሰብ በነበረበት በዚያ ዘመን ታዲያ መራር የሽንፈትን ፅዋ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

እንዲጋት ያደረገው ድክመቱ በጠላቶቹ ዘንድ በመታወቁ ሲሆን የአኪለስ ድክመትም የተረከዝ ሕመሙ ነበር:: እነሆ እስከዛሬ ድረስ "Achilles Heel" የሚል ቃል በእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት ላይ ሰፍሮ ይገኛል:: "Achilles Heel" አንድ ሰው በተፈጥሮው ላለበት ድክመት መገለጫ ሆኖ እስከዛሬ ድረስ እየተጠቀምንበት እንገኛለን::

ሀሪስ በመጽሐፉ:- «የግሪኮች ብቻ ሣይሆን የጣሊያን ጥንታዊ ሥነ ጽሑፎችም መነሻቸው ቁጣ ነበር» ይለናል:: «ቁጣው የሰው ልጅ ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር፤ ነገር ግን መደምደሚያው በቀል ነበር» በማለት ሀሪስ በአውሮፓ ጥንታዊ ከሚባሉት የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች አንዱ በሆነው ዩሪፒደስ ውስጥ ቁጣን ይገልፅልናል:: «ንጉሥ ሂፖሊተስ ለሚያመልካት ለአርጤሚስ ሕይወቱን በመቀደስ ሰጥቷል፤ ከዕለታት አንድ ቀን ለአምላኪቷ ቀድሶ የሰጣትን ሕይወቱን ወሰደና አጉደፋት፤ በዚህም ሥራው የአርጤሚስ ቁጣ ወረደበትና በራሱ ፈረሶች ተረጋግጦ ሞተ:: የአማልክት ቁጣ መገለጫ እንግዲህ ይህን ይመስል ነበር::» ይላል::

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ60 ዓ.ዓ. የኖረው ጠቢቡ ሲሴሮ ስለቁጣ ሲናገር «በንግሥና ዙፋን ተቀምጦ በቁጣ ቀንበር ሥር እንደሚሰቃይ ንጉሥ የሚያሳዝን የለም» ይላል:: ለዛሬ የስቶይሲዝም ፍልስፍና አራማጅ በነበረውና በመግቢያዬ ላይ በጠቀስኩት በሴኔካ የንጉሥ ፒሶ ታሪክ ልሰናበት:-

«ግኔስ ፒሶ በጣም አድርጌ የማስታውሰውና በሐሣቤ ሲመጣም ቆጡነትንና ግትርነትን ከአስተዋይነት መለየት የተሳነው ሰው አድርጌ እቀርፀዋለሁ:: አንድ ቀን አንድ ወታደር ለአሰሳ ከወጣበት ሲመለስ አብሮት የወጣውን የመቶ አለቃ ትቶት ብቻውን ይመለሳል:: ይኸን የሰማው ፒሶ ወታደሩ እንዲገደል ትዕዛዝ ሰጠ:: ለሞት ፍርዱም ምክንያት:- «ወታደሩ መቶ አለቃውን ገድሎት ሊሆን ይችላል፤ ባይገድለውም ደግሞ አለቃውን ትቶ መምጣቱ በራሱ ብቻ ያስገድለዋል»



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

የሚል ነበር:: ገዳዩም ወታደሩን ለመግደል ወደ አንድ ከፍታ ቦታ ይዞት ይጠጣና ሰይፉን ሲመዝ የመቶ አለቃው ድንገት ከተፍ አለ:: ገዳዩ በዚህ ጊዜ ደስ ተሰኝቶ ሰይፉን ወደቦታው መልሶ ወታደሩንና የመቶ አለቃውን ይዞ ወደ ቤተ መንግሥት ይገሰግሳል:: ይኸን ጊዜ በቤተ መንግሥቱ ደስታ ይሆናል:: ነገር ግን ፒሶ ሦስቱን ሰዎች ሲመለከት ቁጣው ነደደ:: ወዲያውኑ ሦስቱም ተይዘው እንዲገደሉ አዘዘ:: ፒሶ ለዚህ ምክንያቱን ደግሞ ሲናገር:- «የመጀመሪያው እንዲሞት አስቀድሜ ስለፈረድኩበት ይሞታል፤ ሁለተኛው ወታደሩን እንዲገድል ትዕዛዝ ከሰጠሁት በኋላ ትዕዛዜን ባለመፈፀሙ ይሞታል፤ ሦስተኛው የመቶ አለቃ ደግሞ ለወታደሩ ሞት ምክንያት በመሆኑ እሱም ይሞታል...» በማለት ፈረደ:: ሴኔካ የቁጣን ውበት ከገለፀባቸው የቁጣ ታሪኮች አንዷ እንግዲህ ይኸች ነበረች:: «ከቁጣው» ይሰውረን::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ከጠገበ አሳማ የራበው ሰው ይሻላል

«የጠገበ አሳማ ከመሆን የራበው ሰው መሆን እጅግ የተሻለ ነው... የጠገበ ሰነፍ ሰው ከመሆን ደግሞ የተራበ ሶቅራጥስ መሆን በጣም ይሻላል:: አሳማውም ሆነ ሰነፉ ሰው የሚኖራቸው የራሳቸው ሐሣብ ብቻ ነው::... በአንፃሩ ያሉት ግን በሁለቱም ወገን ያለውን ሐሣብ በሚገባ ያውቁታል...::» ጆን ስቴዋርት ሚስ ሄዶኒስት ነበር:: በሄዶኒዝም ደግሞ የሰው ልጅ ዋነኛ ግብ ደስታ መመኘት ነው:: እንደስቴዋርት እምነት ይኸ ደስታ በዓይነት (qualitatively) የሚወሰን ነው:: «ከአንዲት ሴት ጋር ተኝተህ የምታገኘው ደስታና አንድ መጽሐፍ ጽፈህ የምታገኘው ደስታ እኩል አይሆንም:: ምክንያቱም የሁለቱም ደስታ በዓይነት ስለሚወሰን ነው» ይሰናል::

«ስለዚህም የጠገበ አሳማ ከሚያገኘው ደስታ ይልቅ የራበው ሰው ደስታ እጅግ ይበልጣል... ለምን ቢባል ሰው እየራበውም ቢሆን ማሰብ ይችላልና:: እንደማሰብ ደግሞ ደስታ የሚያተርፍልህ ነገር የለም» በማለት ስቴዋርት ሚል ይናገራል::

ሄዶኒዝም የሞራል የፍልስፍና ፈርጅ ሆኖ አትኩሮቱ «ደስታ» ላይ ነው:: የዚህ ፍልስፍና አራማጆች ደግሞ ሄዶኒስት ይባላሉ:: ቀጥሎ ከእነሱ ባህር ጥቂት እንጨልፋለን::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner